አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3545 | ቅዳሜ ጥቅምት 22 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# ኢትዮጵያ

- የባህር በሯን ያጣችበት መንገድ ህጋዊ መሠረት እንደሌለው ተገልጿል
- መልሳ ለማግኘት መልክዓ ምድራዊ ቅርበቱና ታሪካዊ መሠረቱ እንደሚፈቅድላት ተጠቁሟል
- ወደብ አልባ መሆን የአንድ ሀገር የውጭ ንግድ መጠንን እስከ 43 በመቶ ሊቀንሰው እንደሚችል ተመላክቷል

3



ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በ6ኛው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ በኢትዮጵያ የባህር በር ፍላጎት ዙሪያ ማብራሪያ ሰጥተዋል

# ነገን ዛሬ የመስራት ማሳያ

- የኮሪደር ልማት የትውልድ ስነ ልቦና ስብራትን እያረቀ ያለ ስራ መሆኑ ተመላክቷል

በመለሰ ተሰጋ

ታዋቂዋ የከተማ ልማት ባለሙያ ተባባሪ ፕሮፌሰር ማሪቼላ ሴፔ በአውሮፓ፣ በሰሜን አሜሪካ እና በእስያ ከተሞች ላይ ያደረጉትን ጥናት ዋቢ በማድረግ እ.ኤ.አ ጥቅምት 10 ቀን 2022 ጤናማ እና ለኑሮ ምቹ ከተሞችን መንደፍ (Designing Healthy and Liveable Cities) የተሰኘ ጥናታዊ መፅሐፍ አሳትመዋል፡፡

ፕሮፌሰሯ በመፅሐፋቸው እንዳስቀመጡት በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የከተሜነት መለኪያ የተደራረቡ የሕንፃ ጫካዎች ክምችት አይደለም። ይልቅ ከሰው ልጆች ነፍስና ስጋ ጋር የተወዳጁ፣

ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ- ከገፀ ድር

ከጋርመንት ፉሪ በሚዘልቀው መስመር ላይ ከተከናወነው የኮሪደር ልማት ስራ መካከል አንዱ

# "በሩብ ዓመቱ ለ96 ሺህ 210 ዜጎች ቋሚ የስራ ዕድል ፈጥሬአለሁ"

የአዲስ አበባ ስራና ክህሎት ቢሮ

- የተፈጠረው የሥራ ዕድል ከታቀደው የ18 ሺህ 710 ብልጫ አለው

በደረጀ ታደሰ

በመንግስት ልዩ ትኩረት ከተሰጣቸው ሀገራዊ አጀንዳዎች መካከል ለዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል ፈጠራ ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህንንም መሰረት በማድረግ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያለውን ፀጋ በመጠቀም ለመዲናዋ ሥራአጥ ዜጎች የሥራ ዕድል

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

## የተወዳዳሪነት አቅም የሚጨምር እውቅና

5



ፎቶ- ከገፀ ድር

ተቋሙ በትምህርት ዘርፍ ባበረከተው አስተዋፅኦ የልዩ ተሸላሚ እውቅና ባገኘበት ወቅት

## ልጆች፤ የማንበብ ልምዳችሁ እንዴት ያለ ነው?

21



ፎቶ በገነት ወንድሙ

ልጆች የንባብ ባህላቸውን ከሚያዳብሩበት መንገዶች መካከል ቤተ መጽሐፍት አንዱ ነው

## የሁለገቡ ከያኒ አበርክቶ ሲታወስ

20




ፎቶ- ከገፀ ድር

ከያኒ ሥዩም ወልዴ ከሚታወስባቸው ስራዎች አንዱ




አድራሻ +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## የባህር በር ጉዳይ የብሄራዊ ጥቅማችን አስኳል ነው!

ባህር በር የአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ የጀርባ አጥንት ነው፡፡ ለኢኮኖሚ እድገትና ለብሔራዊ ደህንነት መረጋገጥ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ ከባህር መቅረብ የገዘፈ ትሩፋት የማስገኘቱን ያህል መራቅም ዘርፈ ብዙ ጫና ይዞ እንደሚመጣ አያጠራጥርም፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያን ለዚህ በማሳያነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ በስልጣኔያቸውና በእድገታቸው በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱት ተርታ ተሰልፋ እንደነበር ታሪክ ማስረጃ፣ የዘርፉ ምሁራንም ምስክር ናቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ ከዓለም ጋር የሚያገናኟት፣ ከውጭ የሚያስፈልጋትን ዕቃዎች የምታስገባባቸውና የምታስወጣባቸው እንደ አዱሊስ፣ ዘይላ፣ በርበራ፣ ምፅዋና አሰብ አይነት አማራጭ የባህር በሮች እንደነበሯት መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

ኢትዮጵያ ምክንያታዊ ባልሆነ መልኩ የባህር በር ካጣችበር ጊዜ ጀምሮ መጻኢ ጉዞዋ ላይ ሳንካ እየፈጠረ ቀጥሏል። በሌላ በኩል ደግሞ የእድገት ፍላጎቷን ለማሳካት፣ እየጨመረ የመጣውን የህዝብ ቁጥሯን በአግባቡ ለመጠቀም የባህር በር ማግኘት የህልውና ጉዳይ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ከጂኦግራፊያዊ ቅርበት፣ ከታሪካዊ መሠረት እና ከዓለም አቀፍ ህጎች አንጻር ይህን የማግኘት እድል መኖሩን በውል መረዳት ያስፈልጋል፡፡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እ.ኤ.አ በ1994 "የተባበሩት መንግስታት የባህር ህግ ስምምነት" በሚል የባህር ሕግን ስራ ላይ አውሏል፡፡ በዚህ በ168 ሀገራት በተፈረመው በዚህ ህግ አንቀጽ 69 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 5 ላይ የባህር በር የሌላቸው ሀገራት በአካባቢያቸው ካለው ባህር እኩል የመጠቀም መብት እንዳላቸው በግልፅ ማመላከቱ የጉዳዩን ፍትሃዊነት በግልጽ የሚያመላክት ነው፡፡

አሁን ላይ ኢትዮጵያ ከመሸኮርመም ወጥታ ጥያቄዋን ለዓለም ማስተጋባት፤ የተሻለ መረዳት እንዲኖር ማድረግ ችላለች፡፡ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 6ኛ ዙር፣ 5ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ የምክር ቤት አባላት ላቀረቡላቸው ጥያቄዎች ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት፣ "የቀይ ባህር ጉዳይ ህጋዊ፣ ታሪካዊ፣ መልከዓ ምድራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄ ነው ብለን እናምናለን። ይህንን በተረጋጋ መንገድ ማየት ያስፈልጋል። የኢትዮጵያን የቀይ ባህር የማጣት ውሳኔ ማን ወሰነ? ብለን ስንፈልግ ተቋማት አልገቡበትም። ይህን የሚያህል የህልውና ጉዳይ ማን እንደወሰነ መጠየቅ ተገቢ ነው። ኢትዮጵያ ተዘግቶባት መኖር አትችልም። ለጎረቤቶቻችን መናገር የምንፈልገው ኢትዮጵያ ስታድግ ለቀጣናውም ልማት ምንጭ ትሆናለች። የምንፈልገው በትብብር ማደግ ነው" ማለታቸው በጉዳዩ ላይ ያለንን የማያወላዳ አቋም እንዲሁም ያጣንበት መንገድ ኢፍትሃዊ መሆኑን በግልጽ የሚያመላክት ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን በጋራ ስንቆም እንቆቅልሾቻችንን መፍታት እንደምንችል ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሁነኛ ማሳያ ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) በግድቡ ምረቃ ላይ ስለቀጣይ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ሲዘረዝሩ የባህር በርን መጥቀሳቸው በአብሮነት የመቆም አስፈላጊነቱን አጽንኦት ለመስጠት ጭምር እንደሆነ በውል መረዳት ያስፈልጋል። የተረከብናትን የታፈረችና የተከበረች ሀገር ለቀጣዩ ለትውልድ ለማስረከብ ሁላችንም ብሄራዊ ጥቅሞቻችን በሆኑ ጉዳዮች ላይ በጋራ መቆማችንን አጠናክረን ማስቀጠል ይጠበቅብናል፡፡ ለዚህ ደግሞ ይህን እንዳናሳካ አጀንዳ እየሰጡ እርስ በእርስ ሊያባሉን የሚዳዳቸው ጠላቶቻችን ጆሮ መንፈግ እና እኩይ ዓላማቸው እንዲጨነግፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ የባህር በር ጉዳይ የብሄራዊ ጥቅማችን አስኳል መሆኑን በመረዳት የራሳችንን አሻራ ማሳረፍ ይጠበቅብናል!

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## ለተማሪዎች ውጤታማነት የወላጆች ድርሻ

**በዳንኤል ተሾመ ከገርጂ**

ለተማሪዎች ውጤትና የባህሪ ዕድገት የወላጆች ተሳትፎ፣ ክትትልና ድጋፍ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ልጆች የነገ የሀገሪቱ አዲስ ትውልዶች እንደመሆናቸው ከመውለድ ባሻገር ወላጆች የልጆቻቸውን የነገ ህይወት ስኬት የሚወስነው ዕለት በዕለት በሚያደርጉት ክትትልና ቁጥጥር መሆኑ ለአፍታም ሊዘነጋ አይገባም። "ልጅ የሚበላው፣ የሚለብሰው አስፈላጊውን የጤና እንክብካቤ ከተደረገለትና ወደ ትምህርት ቤት ከተላከ ሌላ ምን ይፈልጋል?" የሚለው አባባል ዛሬ ከምንገኝበት ማህበረሰባዊ ሥነ ልቦናው ሁኔታ ተቀባይነት የለውም፡፡

በርካታ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት መላካቸውን ነው እንጂ ምን እንደተማሩ በመከታተል ድክመቱንና ጥንካሬውን አስመልክቶ መረጃ የላቸውም፡፡ በተወሰኑት ጊዜያት ወደ ትምህርት ቤት ሄደው ስለልጆቻቸው የትምህርት ሁኔታ፣ ባህሪ፣ ሥነ ምግባርና ውጤት ከመምህራን ጋር መረጃ የመለዋወጥ ባህል በወላጆች ዘንድ አልጎለበተም። በተማሪዎች የትምህርት ቤት ውሎ ብቻ ሳይሆን ከትምህርት ቤት እስከቤት ድረስ ያሉበት ሁኔታ መረጃ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የጥናት ጊዜውን በመምህራን የሚሰጡ የተለያዩ የቤት ውስጥ ሥራዎችን ተከታትሎ የማሰራት ልምድ አላዳበርንም፡፡ እነዚህ ችግሮች ደግሞ በትምህርት ጥራት ብቻ ሳይሆን በተማሪዎች አካዳሚክ ውጤት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳረፉ አይቀሬ ነው።

በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ወላጆች በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተሳትፎአቸው መጠናከር የትምህርት ቤት ውሎአቸውንና የቤት ውስጥ የጥናት ክትትል እና ድጋፍ መጎልበት በ6ኛ እና በ8ኛ ክልል አቀፍ እንዲሁም በ12ኛ ብሔራዊ ፈተናዎች ውጤቶች ላይ በግልጽ ታይቷል፡፡

ወላጆች የልጆቻቸውን ትምህርት ክትትልና ድጋፍ አስመልክቶ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት ወላጆች በመጀመሪያ፣ በሦስተኛና በአምስተኛ ክፍል የትምህርት ደረጃዎች የሚያደርጉት ድጋፍ መጠናከር የልጆች የማህበራዊ ክህሎት የመቀበልና ኃላፊነትን የሚቀበሉ እንደሚያደርጋቸው ታውቋል፡፡ የወላጆች ልጃቸውን በቤት ሥራዎቻቸው የማገዝ ከትምህርት ቤት መምህራን ጋር የሚያደርጓቸው ግንኙነቶችና ትምህርት ቤቶች የሚያዘጋጇቸው ኮንፈረንሶች ላይ የሚያደርጉት ተሳትፎ ልጆቻቸው አዋኪ ባህሪ እንዳይኖራቸው ለማድረግ ጠቃሚ መሆኑ የጥናት ሰነዶች ያረጋግጣሉ፡፡

የልጆቻቸውን ትምህርት በቤት ውስጥ ብቻ ሳይሆን ትምህርት ቤት ድረስ በመሄድ በቅርብ የሚከታተሉ ወላጆች አሉ፡፡ የእነዚህ ትጉ ወላጆች ተማሪዎች የትምህርት ውጤትና ሥነ ምግባር ሁሌም በአርአያነት የሚጠቀስ ነው፡፡

ለሀገራችን የትምህርት ጥራት ኃላፊነት ካለባቸው ወላጆች፣ መንግስትና ማህበረሰብ ውስጥ የወላጆች ድርሻ ከፍተኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በቤት ውስጥ የሚኖረው የወላጆችና የተማሪ ልጆቻቸው ግንኙነትና የቅርብ ክትትል የተማሪን ውጤት ብቻ ሳይሆን ባህሪውን፣ ሥነ ምግባርን እና ማህበራዊ እሴትን ለማሳወቅ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡

ወላጆች ከስራ መልስ የልጆቻቸው የዕለት ውሎ የመከታተል፣ የቤት ስራዎቻቸውን እንዲሰሩ መከታተል ጥሩ ዜጋ እና ስራ ወዳድ አድርጎ ለመቅረፅ የሚያጠፉት ጊዜ በተማሪዎች የነገ ማንነት ላይ በውጤት የሚገለፁ ናቸው፡፡ መሰል የቅርብ የወላጆች ክትትልና ድጋፍ ደግሞ የተማሪዎችን ትምህርት ማቋረጥን ይቀንሳል፤ ተማሪዎችን በትምህርት ቤት የመገኘትና ትምህርታቸውን የመከታተል ሂደትን ያጠናክራል፡፡ በተማሪዎችና በመምህራን መካከል ያለውን ግንኙነትም ያጠናክራል፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜልባ ፕሪንቲንግ ፐብሊሺንግ ኤንድ ፓኬጂንግ ሼር ካምፓኒ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ለይላ መሀመድ
አብርሃም ገብሬ
ፋንታነሽ ተፈራ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
ይግለጡ ጓዴ
ሄለን ጥላሁን

**ዋና አዘጋጅ**
ተካልኝ አማረ
Tekalignteke123@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር B91/17

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# ኢትዮጵያ

- የባህር በሯን ያጣችበት መንገድ ህጋዊ መሠረት እንደሌለው ተገለጿል
- መልሳ ለማግኘት መልክዓ ምድራዊ ቅርበቱና ታሪካዊ መሠረቱ እንደሚፈቅድላት ተጠቁሟል
- ወደብ አልባ መሆን የአንድ ሀገር የውጭ ንግድ መጠንን እስከ 43 በመቶ ሊቀንሰው እንደሚችል ተመላክቷል

**በተካልኝ አማረ**

ኢትዮጵያ ረጅም እድሜ ያስቆጠረች ሀገር እንደመሆኗ በበርካታ ውጣ ውረዶች ውስጥ አልፋ ዛሬ ላይ ደርሳለች። በታሪኳ የከፍታም ሆነ የዝቅታ ዘመናት እንደነበሯት ታሪካዊ ድርሳናት ይመሰክራሉ፡፡ በአክሱማይት ስርወ መንግስት ዘመን በዓለም ላይ ከነበሩ አራቱ ኃያላን ሀገራት መካከል አንዷ እንደነበረች ኤድመንድ ጄ. ኬለር የኢትዮጵያን ሀገረ መንግስትና ፖለቲካዊ ህልውና ቀጣይነት ሁኔታ አስመልክተው (The Politics of State Survival: Continuity and Change in Ethiopian Foreign Polic) በሚል ርዕስ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1987 ያሳተሙት ጥናታዊ ፅሑፍ ያስነብባል። ሀገሪቷ በዘመናት ሂደት ደጋግመው በገጠሟት ውስጣዊና ውጫዊ ፈተናዎች ሳቢያ ኢኮኖሚዋ ተዳክሞ የድህነት ምሳሌ ተደርጋም ታውቃለች፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በ6ኛው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ በኢትዮጵያ የባህር በር ፍላጎት ዙሪያ ማብራሪያ ሰጥተዋል

የውስጥ ሽኩቻዎች እና የውጭ ወረራዎች ክፉኛ ያጎሳቆሏት ሀገር ናት ኢትዮጵያ። ከውስጥ በዘመነ መሳፍንት፣ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት እና በሌሎች ጊዜያትም የገጠሟት ሁኔታዎች የሚታወሱ ናቸው፡፡ ከውጭ ደግሞ የግብፅ፣ የጣሊያን፣ የሱዳን፣ የሶማሊያን ወረራዎች መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ ሀገራት ግዛትን የማስፋፋትና የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ሀብት የመቆጣጠር ዓላማ አንግበው ተደጋጋሚ ትንኮሳዎችን አድርገውባታል፡ ፡ ቀደምት አያቶቻችን በተባበረ ክንድ የእነዚህን ሀገራት ትንኮሳዎችን እና ወረራዎችን ቀልብሰዋል። ሆኖም እነዚህ ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች ተደማምረው በርካታ ኪሳራዎችን በሀገር ላይ አስከትለዋል። ለአብነትም ሀገሪቷን የባህር በር አልባ አድርገዋታል፡፡

ኢትዮጵያ በጥንት በአክሱም ዘመነ መንግስትና ከዚያ በኋላም የነበሩ ስልጣኔዎች መሰረታቸው ከባህር ጋር የተቆራኘ ነው። ባህር ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ምንጭ፣ የህልውና መጠበቂያ አቅም፣ በዓለም አቀፍ ደረጃም የፖለቲካ ሚዛን ማስጠበቂያ እንዲሁም ከውጭ ዓለም ጋር ለሚደረጉ የንግድ ልውውጥ ማሳለጫ በመሆን ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ኢትዮጵያ ከባህር በር እየራቀች በመጣች ቁጥር የኢኮኖሚ፣ የዲፕሎማሲና ራስን የመጠበቅ አቅሟ እየተዳከመ እንደመጣ የታሪክ ባለሙያዎች ያሳያሉ፡፡

በቅርቡ ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጋር ቆይታ ያደረጉት በአሜሪካ ኮርኔል ዩኒቨርሲቲ እና በሀገር ውስጥ በተለያዩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የታሪክ መምህርና ተመራማሪ ሆነው የሰሩት አየለ በከሬ (ፕ/ር)፣ ባህር ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ተፈጥሯዊ አካል እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

አየለ በከሬ (ፕ/ር) በዓለም ላይ ዋነኛው የንግድ ልውውጥ መስመር ባህር ሲሆን፣ ኢትዮጵያ የባህር በር በነበራት ጊዜ በስልጣኔና እድገት ወደፊት ሄዳ እንደነበር አውስተው፣ ከውጭ የሚያስፈልጋትን ዕቃዎች የምታስገባውና የምታስወጣባቸው አማራጭ ወደቦች በብዛት እንደነበሯት ጠቁመዋል፡፡ ከእነዚህም አዱሊስ፣ ዘይላ፣ በርበራ፣ ምፅዋና አሰብ እንደሚጠቀሱ ገልፀዋል፡፡

ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ በገጠማት የውጭ ወራሪዎች ጥቃት እና የሀገር ውስጥ የባንዳ ክህደት ሳቢያ በጊዜ ሂደት ወደቦቿን አንድ በአንድ እያጣች መጥታለች፤ በ1983 የመጨረሻው ክህደት ተፈፅሞባታል፤ በጫካ ህግ አንጡራ ሀብቷን ለማጣት ተገድዳለች፡፡ ለ30 ዓመታትም ይህን ጉዳይ ማንሳት እንደ ነውር ሆኖ ይቆጠር ነበር፤ ይህን አይነኬ ሆኖ የቆየ ጉዳይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ኢትዮጵያ የባሕር በር እንደሚያስፈልጋት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት “ከጠብታ ውሃ እስከ ባህር ውሃ” በተሰኘው መድረክ አነሱ፤ ይህም የባህር በር ጉዳይ ዳግም እንዲነሳ እና ዜጎች ለኢትዮጵያ የህልውና ጉዳይ መሆኑን እንዲረዱ አድርጓል፡፡

ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ተገቢነት በጎደለው መንገድ ከሶስት አስርት ዓመታት በፊት ከእጇ የወጣውን የባህር በር ባለቤትነት መልሳ ለማግኘት በሰላማዊ መንገድ ጥረቶችን ስታደርግ ቆይታለች። ጥረቷ መልካም ውጤት እያስገኘላት ስለመሆኑም የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ በሕዝብ ተወካዮች እና ፌዴሬሽን ምክር ቤቶች የ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን የመክፈቻ ሥነ ሥርዓት ላይ መናገራቸው ይታወሳል፡፡

ለመሆኑ ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነቷን ያጣችበት ሂደት ከዓለም አቀፍ ህግ አንፃር እንዴት ይታያል? ከታሪካዊ ባለቤትነት እና መልክዓ ምድራዊ ቅርበት አንፃርስ መልሳ የማግኘት ዕድሏ ምን ያህል አስተማማኝ ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን አንስቶ ማብራራት ያስፈልጋል፡፡

ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነቷን ያጣችበት ሂደት ግልፅ አለመሆኑ ተደጋግሞ ይነሳል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በ6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ይህን ጉዳይ አንስተው አብራርተዋል፡፡ በማብራሪያቸውም፣ የኢትዮጵያን የቀይ ባሕር ድንበርተኝነት ያሳጣው ውሳኔ በማን እንደተወሰነ የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ አለመገኘቱን ጠቅሰው፣ ውሳኔው ሕጋዊ እንዳልሆነ አመላክተዋል፡፡

ታድያ እንዲህ ያለው ጉዳይ ከህግ አግባብ እንዴት ይታያል ያልናቸው የህግ ባለሙያው አቶ ኪያ ፀጋዬ፣ በወቅቱ የነበረው የሽግግር መንግስት እንደመሆኑ የባህር በርን በሚያህል ጂኦ እስትራቴካዊ ጉዳይ ላይ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን የለውም፡፡ ስለዚህ ውሳኔው ህጋዊ መሠረት የለውም በማለት ጉዳዩን ማብራራት ጀምረዋል፡፡

የህግ ባለሙያው በማብራሪያቸው፣ እንዲህ ያለውን ውሳኔ ለማሳተለፍ የሚችል ህጋዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስት ባልተመሰረተበት ሁኔታ ነው ኢትዮጵያ የባህር በሯን ያጣችው፤ ተቀባዩም ሆነ ሰጪው ከጫካ የመጡ የጋራ ዓላማ የነበራቸው ናቸው፡፡ ኢትዮጵያዊ ውግንና ቢኖራቸው ኖሮ በሺህ ኪሎ ሜትሮች የሚቆጠር ርዝመት ያለው የባህር በር ያላትን ሀገር በአንድ ጀንበር ዝግ አያደርጓትም ነበር፡፡ ስለዚህ ህዝብ ተወያይቶ ያልደረሰበት ስምምነት እና በህዝብ የተመረጠ መንግስት በሌለበት የተላለፈ ውሳኔ በመሆኑ ህጋዊ መሠረት ያሳጣዋል ብለዋል፡፡

የባር በሩ የሄደበት መንገድ ቀርቶ ኤርትራ ራሷም የተገነጠለችበት መንገድ ሲፈተሽ ህጋዊ መሰረት የለውም ያሉት የህግ ባለሙያው፣ ሁኔታው ከድርጊቱ ጀርባ አንዳች ድብቅ ዓላማ መኖሩን ጠቋሚ ነው፡፡ ኢትዮጵያን በር አልባ የማድረግ ደባ ነው የተፈፀመው፡፡ ምክንያቱም በጉዳዩ ውስጥ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች እጅ አለበት ሲሉም አክለዋል፡፡

ለዚህም እንደማስረጃ ያቀረቡት በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ያሳለፉት በትጥቅ ትግል ላይ የቆዩ አካላት ሲሆኑ ኤርትራ በኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ውስጥ ነች ብለው የሚያስቡ ከመሆናቸውም በላይ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላት ከሆነችው ግብፅ ጋር እጅና ጓንት ሆነው ሲሰሩ የቆዩ መሆናቸውን ነው፡፡

የኢትዮጵያን የባህር በር የተወሰደበት ሂደት የተሳሳተና ደባ የተሞላበት መሆኑ አሁን ለማስመለስ እየተደረገ ላለው ጥረት ትልቅ ህጋዊ አቅም እንደሚሰጥ የህግ ባለሙያው ጠቁመዋል፡፡ ኢትዮጵያ የባህር በሯን መልሳ ለማግኘት ጂኦግራፊያዊ ቅርበቱ፣ ታሪካዊ መሠረቱ እና ዓለም አቀፍ ህጎች እንደሚፈቅዱላት ገልፀዋል፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እ.ኤ.አ በ1994 “የተባበሩት መንግስታት የባህር ህግ ስምምነት” (United Nations Convention on the Law of the Sea) የተሰኘ የባህር ሕግን ስራ ላይ አውሏል። ይህ ሕግ በ168 ሀገራት የተፈረመ ነው። ይህም በጣም ተቀባይነት ካላቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አንዱ ተደርጎም ይወሰዳል፡፡

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የባህር ሕግ አንቀጽ 69 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 5 የባህር በር የሌላቸው ሀገራት በአካባቢያቸው ካለው ባህር የተፈጥሮ ሀብት እኩል የመጠቀም መብት እንዳላቸው በግልፅ ያስቀምጣል፡፡ በዚሁ ሕግ በአንቀጽ 125 ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተቀመጠው የባህር በር የሌላቸው ሀገራት በአካባቢያቸው ያለውን ባህር የመጠቀም እና የመሸጋገር ዓለም አቀፍ መብት እንዳላቸውም በጉልህ ሰፍሯል፡፡

ታዲያ ይህ መብት የባህር በር በሌለው ሀገር፣ የባህር በር ባለቤት በሆነው ሀገር እና በቀጣናው መካከል በሚደረግ ስምምነት ሊፈጸም እንደሚገባም በንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ተቀምጧል፡፡ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ ደግሞ እነዚህ የባሕር በር የሌላቸው ሀገራት በሰምምነት ከተደረገ የተለየ የአገልግሎት ክፍያ ከሌለ በስተቀር ለተገለገሉበት ባህር ምንም ዓይነት የትራፊክ ታክስ ወይንም ሌላ ክፍያ እንደማይጠየቁም መደንገጉን የህግ ባለሙያው አቶ ኪያ ፀጋዬ ገልፀዋል፡፡

በዓለም ላይ ካሉ 195 ሀገራት መካከል 44 ሀገራት ወደ ባህር መውጫ በር የላቸውም፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 32ቱ ከበድ ያሉ ፈተናዎች ያሉባቸው አዳጊ ሀገራት መሆናቸውን የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም መረጃ ያመላክታል። ኢትዮጵያ የባህር በሯን በግፍ ከተነጠቀችበት ጊዜ ጀምሮ ለበርካታ ውስብስብ ችግሮች ተዳርጋ ቆይታለች። ከውጭ የምታስገባው እቃዎች ሁሉ ተፈትሸው እንዲያልፉ ስለምትገደድ የደህንነት ጉዳይ አደጋ ላይ ወድቋል፡፡ ድህነትን ለማሸነፍ የሚደረገው ጥረትም ተጠባቂውን ውጤት ሳያስገኝላት ቀርቷል፤ ምክንያቱም የባህር በር እጦት በጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት ላይ ቀላል ያልሆነ ተፅዕኖ አለውና፡፡ ዶክተር ያዕቆብ ኃይለማርያም ‘አሰብ የማን ናት?’ በሚለው መጽሐፋቸው ይህን ጉዳይ በበቂ ደረጃ አብራርተውታል፡፡

ወደብ ያለው ሀገር ኢኮኖሚውን በእጥፍ ለማሳደግ 24 ዓመታት እንደሚፈጅበት የሚያትተው የዶክተር ያዕቆብ መፅሐፍ፣ ወደብ አልባው ሀገር ኢኮኖሚውን በእጥፍ ለማሳደግ 36 ዓመታት እንደሚወስድበት አብራርተዋል፡፡ ወደብ አልባ መሆን ብቻ የአንድ ሀገር የውጭ ንግድ መጠንን ከ33 በመቶ እስከ 43 በመቶ ሊቀንሰው እንደሚችልም አመላክተዋል፡፡

ከ120 ሚሊዮን በላይ ህዝብ ይዞ የባህር በር የሌላት ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ ነች ያሉት የህግ ባለሙያው፣ “በዚያ ላይ የነበራትን ነው ያጣችው፡፡ አሁን ላይ የባህር በር የህልውና ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ የዓለም ማህበረሰብ እና ጎረቤት ሀገራት ይህን ጉዳይ በቅጡ አጢነውት ተገቢውን ምላሽ ሊሰጡን ይገባል፡፡ አለበለዚያ ይዞት የሚመጣው ጦስ ለሁሉም ይተርፋል” ሲሉ አሳስበዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የባህር በርን መጠየቅ ነውርና ትክክል ያልሆነ አድርጎ የሚመለከት ትርክት እንዳለ ጠቁመው፣ ኢትዮጵያ ባህር እንደሚያስፈልጋት እና ከኤርትራ ጋር ሰላም በተፈጠረበት ወቅት የኤርትራው ፕሬዝዳንት ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ በሚሊኒየም አዳራሽ ማንሳታቸውን ተናግረዋል፡፡ ወደ ኤርትራ በተጓዙበት ወቅትም ወደብ ዋነኛ ጉዳይ እንደነበር አውስተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ኢትዮጵያ የባህር በር የማግኘቷ ጉዳይ አይቀሬ መሆኑን አንስተው፣ ቅድሚያ የምንሰጠውም ሰላም እና ንግግር ስለሆነ ሀገራት መፍትሔ እንዲያመጡ ጥሪ አቅርበዋል። ማንም ፈለገም አልፈለገም ኢትዮጵያ ተዘግታ እንደማትኖር እርግጠኛ ነኝ ብለው፣ ትልቅ ሀገር የሆነችው ኢትዮጵያ ስታድግ ሌሎችን የምታግዝ እንጂ ስጋት እንደማትሆን አረጋግጠዋል።

# ነገን ... ከገጽ 1 የዞረ

አምራችና ጤናማ መሆንን የሚያበረታቱ የመሆናቸው ምስጢር ነው የከተሜነት ከፍታው፡፡

በመሆኑም ባለንበት ዘመን ከተማ መገንባት ማለት በቀላሉ የሚታይ እሳቤ አይደለም፡፡ ለአብነትም ከተማ ስንገነባ የኮሪደር ልማትን ማሰብ ግድ ይላል፡፡ የኮሪደር ልማት ማለት ደግሞ ትራንስፖርትን፣ የሕዝብ መናፈሻ ቦታን፣ መዝናኛን፣ መኖሪያ ቤትን፣ ንግድን እና ማህበራዊ አገልግሎቶችን የሚያዋህዱ ባለብዙ ተግባር ዞኖችን ማቀድን የሚያካትት ነው፡፡ በመሆኑም የኮሪደር ልማት ጤናማ፣ ንቁ እና ውጤታማ ትውልድን ለማሳደግ ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል ይላሉ የከተማ ልማት ባለሙያ ተባባሪ ፕሮፌሰር ማሪቼላ ሴፔ፡፡

አዲስ አበባ ከተማም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በዘመን ብዛት የተጎሳቆለ መልኳን በልማት ወዝ አድምቃ እና የወየበ ልብሷን እንደ በረዶ አንፀታ፣ እርጅናዋን እንደ ንስር አድሳ፣ እንደ ጥቅምት አበባን ለብሳ፣ ደግሞም ጥር በሰርግ እንደሚደምቅ እሷም በኮሪደር ልማት ተውባ ትታያለች። ይህ ውበቷ ደግሞ ብዙ ትርጉሞች አሉት። ለአብነትም ባሳለፍነው ማክሰኞ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የኮሪደር ልማቱን አስመልክቶ ያነሱትን ሀሳብ እንጥቀስ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲህ አሉ "የኮሪደር ልማት የቦታና ጊዜ ምልከታን የሚቀይር ነው። ለአብነትም በአዲስ አበባ ብቻ ከአንድ ሺህ በላይ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ተገንብቷል። በርካታ ወጣቶች ወደ ስፖርት እየተመለሱ ነው። ይህም ማህበረሰብን የመገንባት ስራ ነው። የትውልድ ስነ ልቦና ስብራትን እያራቀ ያለ ስራም ጭምር ነው። ይህን ማንም ሰው የሚያየው፤ ማንም ሰው የሚናገረው ጉዳይ ነው።"

በኮሪደር ልማቱ ምክንያት ከተጎሳቆለ ኑሮና አካባቢ መውጣት የቻሉ የመዲናዋ ነዋሪዎችም ለዚህ ምስክር ናቸው። ለአብነትም ወይዘሮ ሮማን ጌታቸው በአራዳ ክፍለ ከተማ ፒያሳ በተለምዶ ዶሮ ማነቂያ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ለ40 ዓመታት ኖረዋል፡፡ ትዳር ይዘው ልጆች ወልደው በኖሩበት መንደር ጠንካራ ማህበራዊ ትስስር ቢኖርም መታጠቢያ ቤት፣ መፀዳጃ ቤትም ሆነ በቂ የማብሰያ ክፍል እንዳልነበራቸው ያስታውሳሉ።

የሚኖሩበት ቤት ለስሙ ቤት ቢባልም የቤትነት መስፈርትን ያላሟላ እንደነበር ያወሳሉ፡፡ በአንዲት ጠባብ ክፍል ቤት ስምንት የሚሆኑ የቤተሰብ አባላት ልክ እንደዶሮ ቆጥ ላይ እያደሩ በስቃይ ኑሮን ሲገፉ ቆይተዋል፡፡ ይህ የትናንቷ ዶሮ ማነቂያ ሰፈር ውስጥ የነበረ የብዙዎች የኑሮ መልክ ነው፡፡

ከ15 የማያንሱ አባወራዎች በጋራ የሚጠቀሙት መፀዳጃ ቤትም ቢሆን አብዛኛው ተጠቃሚ ለማፅዳት ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ከአጠቃቀም ችግር ጋር ተዳምሮ ተጨማሪ የጤና ስጋት ይፈጥርባቸው ነበር፡፡ ክረምት ሲመጣ ደግሞ ችግሩ ከፍ ይል እንደነበር የሚያስታውሱት ወይዘሮ ሮማን፣ አሁን በኮሪደር ልማት የተሰጣቸው ምትክ ቤት ግን የተሻለ የመኝታ፣ ሳሎን፣ መፀዳጃና መታጠቢያ ክፍሎችን ጨምሮ ደረጃውን የጠበቀ መውጫና መግቢያ ያለው በመሆኑ የሳቸውንም ሆነ የቤተሰቦቻቸውን ጤና ጠብቀው ለመኖር እንደሚያስችላቸው መስክረዋል፡፡

የሰው ልጅ ስጋና መንፈሱ፣ ቤቱና መንደሩ፣ ውሎና አዳሩ ምቹ ከሆኑለት ምርትና ምርታማነቱ መጨመሩ አይቀሬ ነው፡፡ በተለይም ከተሞች ከዘመኑ ጋር ሲወዳጁ ምንዳቸው ከፍ ይላል፡፡ ምክንያቱም ከተሞች የሀገራት ልብ ምት፣ የስልጣኔ መግቢያ በር፣ የምጣኔ ሀብት ርካብ፣ ቀን ነፍስና ስጋን ማስደሰቻ፣ ማታ ደግሞ ጨለማውን መርቻ የድል መቅረዝ ናቸው፡፡

የከተማ ኑሮ መሻሻል ምርታማነትን፣ ባህልን እና የሰው ልጆችን ደስታ ከፍ በማድረግ ትልቅ ሚና እንደሚጫወት በከተሞች ኢኮኖሚና መሰል ጉዳዮች ዙሪያ በመቶዎች የሚቆጠሩ ጥናታዊ ጽሑፎችን እና መፅሐፍትን ያሳተሙት ፕሮፌሰር ኤድዋርድ ግሌዘር እ.ኤ.አ በጥር 31 ቀን 2012 'ትሩምፌ አፍ ዘ ሲቲ' (Triumph of the City) በተሰኘው ጥናታዊ መፅሐፋቸው ገልፀውታል፡፡

በጂማ ዩኒቨርሲቲ የአካባቢ ጤና ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ክፍል ፕሮፌሰር ሰይድ ትኩ በአዲስ አበባ ከተማ እየተከናወነ ያለውን የኮሪደር ልማት በተለይም ከህብረተሰቡ ጤና ጋር የሚያያዝ እንደ "ጽዱ ጎዳና - ኑሮ በጤና" ባሉ ንቅናቄዎች በከተማዋ የተሰሩ ዘመናዊ መፀዳጃ ቤቶች ጤናማና አምራች ትውልድን ለመገንባት ያላቸው ድርሻ ከፍ ያለ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

> **የከተማ ኑሮ መሻሻል ምርታማነትን፣ ባህልን እና የሰው ልጆችን ደስታ ከፍ በማድረግ ትልቅ ሚና ይጫወታል**



ፎቶ- ከገፀ ድር

የኮሪደር ልማቱ የትውልዱን ስነ ልቦና በማነጽ ረገድ የላቀ ድርሻ አለው

በጎዳና ላይ ከሚታዩ ችግሮች መካከል የንፅህና ጉድለት አንዱ መሰረታዊ ችግር ነው፡፡ ክብር ያለው የንጽህና ባህል እና የተቀናጀ የንፅህና አጠባበቅ ስርዓት መፍጠር ባለመቻላችን ምክንያት በማህበረሰቡ ጤና ላይ የተለያዩ ችግሮች እንደሚፈጠሩ የገለፁት ፕሮፌሰር ሰይድ፣ ለአብነትም የመተንፈሻ አካላት ችግር አንዱ ነው። ይሄውም በደረቅም ሆነ በሌሎቹም ቆሻሻዎች ምክንያት የሚፈጠረው ብናኝ አየሩን በመበከል ወደሰዎች የመተንፈሻ አካል በቀላሉ በመግባት ከፍተኛ የጤና ችግር እያስከተለ መሆኑን እና በአዲስ አበባ ከተማ እየተከናወነ ያለው የኮሪደር ልማት ይህንን ችግር ለመቅረፍ የሚያግዝ ስለመሆኑም ጠቁመዋል፡፡

አክለውም በቆሻሻ ዙሪያ መቀመጥ፣ ማለፍም ሆነ ማሰብ ጤናን ብቻ ሳይሆን ምቾትንም ይነሳል፡፡ ይህም በከተሞቻችን በስፋት የሚስተዋል ችግር ነው፡፡ ይህም የቆሻሻ አወጋገድ ባህላችን አለመዘመኑ፣ መንገዶቻችን ባለመስፋታቸውና የፍሳሽ ማስወገጃዎችን ታሳቢ አድርገው ባለመሰራታቸው የመጣ ነው፡፡ ይህም ክፍተት ከማህበረሰቡ ጤና መጓደል ጋር ትልቅ ትስስር አለው ብለዋል፡፡

የከተማ ንፅህና አጠባበቅ በህብረተሰቡ ጤና ላይ ሊያስከትለው የሚችለውን ችግር አስመልክቶ የተለያዩ ጥናቶችን እንዳደረጉ የጠቆሙት ፕሮፌሰሩ በግኝቱም የመፀዳጃ ቤት በበቂ መጠን አለመኖር፣ ባሉትም በአግባቡ ያለመጠቀምና የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓታችን ባለመዘመኑ ምክንያት በማህበረሰቡ ላይ የተለያዩ ችግሮች እየተከሰቱ ነው፡፡

ለአብነትም በምግብ ሰንሰለቱ ላይ የሚስተዋለውን ችግር የጠቀሱት ፕሮፌሰር ሰይድ፣ በተለያዩ ከተሞች በተደረጉት ጥናቶችም በቆሻሻ ስፍራ እና ባልታከመ ውሃ የሚያድጉ እንደ ቲማቲም፣ ቆስጣ፣ ጎመንና መሰል አትክልቶች ከፍተኛ የሆነ የበሽታ አምጭ ህዋሳት ተገኝቶባቸዋል፡፡ ይህንንም ችግር ለመቅረፍ አሁን እንደ ሀገር የተጀመረው የኮሪደር ልማት ትልቅ ለውጥ የሚያመጣ መሆኑን ጠቁመው፣ ለዚህ ደግሞ በአዲስ አበባ እየታየ ያለውን ለውጥ በአብነት አንስተዋል፡፡

በርግጥም አዲስ አበባ ከስምና ክብሯ ጋር በሚመጥን የልማት ጉዞ ላይ እንደምትገኝ ብዙዎች በመመስከር ላይ ናቸው፡፡ ዕድሜና ወዝ፤ ለዛና ደርዝ ያላት ይህች ከተማ በረዣዥም ሕንፃዎች ጥግ የተጠለሉ ደሳሳ ጎጆዎች፣ በአንድ በኩል ምቹ በሌላው ደግሞ ለኑሮ አስቸጋሪ የሆኑ መሰናክሎች የበዙባትም ከተማ እንደነበረች ተደጋግሞ ተዘግቧል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይህንን ጉራማይሌነት ልክና መልክ ባለው መልኩ በመለወጥ በርግጥም ከተማዋ 'አበባ' ትመስል ዘንድ በርካታ ልማቶች እየተከናወኑ ናቸው፡፡ ከከተማዋ ውበትና ዝመና ባሻገርም የብዙ ወጣቶች ችግር የሆነውን የስራ ባህል ዝንፈት ማስተካከል የሚችሉ ተጨባጭ ማስተማሪያ የሚሆኑ ልማቶችንና ሰራተኞችንም በቅርብ ጊዜ ማፍራት እንደተቻለም መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ አሁን አዲስ አበባ ቀንም ሌሊትም የሚሰራባት ከተማ ሆናለች። ይህ ደግሞ የኮሪደር ልማቱ የከፈተው አዲስ በር ነው፡፡

በዚህ ሀሳብ የሚስማሙት በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት ትምህርት ክፍል ተባባሪ ፕሮፌሰር ይንገስ አለሙ (ዶ/ር) ከተማን ማዘመን (ስማርት ማድረግ) ያለንን ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም ያግዛል፡፡ ከተማን ስማርት ማድረግ የመሰረተ ልማት ለሁሉም ተደራሽ እንዲሆን ይረዳል፡፡ መሬትን ምጣኔ ሀብታዊ አዋጭነት መሰረት ባደረገ መልኩ በአግባቡ ለመጠቀም ያግዛል፡፡ ይህ ደግሞ ያለንን ውስን የመሬት ሀብት ለተለያዩ ዘርፎች ማካፈል እንድንችል ይረዳል፡፡

በተጨማሪም፣ ለማህበረሰቡ የተለያዩ አገልግሎቶችን በቀላሉ እና በፍጥነት ለመስጠት ያግዛል፣ የሀገርን ገፅታ ያማረና የተዋበ በማድረግ ዓለም ዓቀፍ እይታን ይስባል፡፡ ይህም በቱሪዝም ሆነ በሌሎች ዘርፎች ያለውን እንቅስቃሴ ያሳድግል። ከዚህ አንፃር ስንመለከተው በኮሪደር ልማትም ሆነ በሌሎች ተግባራት አዲስ አበባን ስማርት ለማድረግ እየተከናወኑ ያሉ ልማቶች ጤናማና አምራች ማህበረሰብን ለመገንባት የሚያግዙ በመሆናቸው በምጣኔ ሀብት እሳቤ ትልቅ ጠቀሜታ አላቸው ብለዋል፡፡

# የተወዳዳሪነት አቅም የሚጨምር እውቅና

**በስንታየሁ ምትኩ**

መገናኛ ብዙሃን በአንድ ሀገር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወትና እንቅስቃሴ ውስጥ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፡፡ መገናኛ ብዙሃን ህብረተሰብን በማስተማርና በማነፅ፣ የመንግስትን የልማት ትልሞች በማሳወቅ፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ነቅሶ በማውጣትና መፍትሔዎችን በማመላከት፣ በመንግስትና ህዝብ መካከል ድልድይ በመሆን አይተኬ ሚና እንደሚጫወቱ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

በየጊዜው ተደራሽነቱን እያሰፋ፣ የነዋሪዎችን ፍላጎት ለማርካት እየተጋ የሚገኘው አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክም ለህብረተሰቡ በተለያዩ የሚዲያ አማራጮችና ቋንቋዎች ወቅታዊ፣ የህዝብን ችግሮች ነቅሶ በማውጣት መፍትሔ የሚያመላክቱ፣ አስተማሪና አዝናኝ መረጃዎችን እያደረሰ ይገኛል፡፡ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ሜትሮፖሊታን ሚዲያ እንደመሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችን ፍላጎት በማርካት፣ ተወዳዳሪና ቀዳሚ የመረጃ ምንጭ ለመሆን በይዘት ፈጠራ፣ በአሰራር፣ በቴክኖሎጂ፣ በሰው ሀይል ልማትና በተለያዩ መስኮች ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው፡፡

ሚዲያው እያሳየ ባለው እድገትና እየፈጠረ ባለው ተፅዕኖ በከተማ አስተዳደሩ ተቋማትና በሀገር አቀፍ ደረጃ በተለያዩ ጊዜያት እውቅና እና ሽልማት ተበርክቶለታል፡፡ ከሰሞኑም የትውልድ ድምፅ የሆነው አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በትምህርት ዘርፉ ላበረከተው አስተዋፅኦ ልዩ ተሸላሚ ሆኗል፡፡ የከተማ አስተዳደሩ "የላቀ ትጋት ለትምህርት ጥራት" በሚል መርህ በ2017 የትምህርት ዘመን የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከ500 በላይ ውጤት ላስመዘገቡ ተማሪዎች የእውቅና መርሃ ግብር ባካሄደበት ወቅት በዘርፉ አስተዋጽኦ ላደረጉ ተቋማት እውቅና ሲሰጥ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክንም እውቅና ሰጥቶታል፡፡ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክም በዕውቀት የተገነባ ትውልድ ለመፍጠር ባደረገው አስተዋፅኦ ነው በከተማ አስተዳደሩ ልዩ ተሸላሚ መሆን የቻለው፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ጋር በመተባበር በአዲሱ የAMN PLUS የቴሌቪዥን ቻናሉ የቴሌቪዥን ትምህርት ስርጭት ዝግጅቶችን እያቀረበ የሚገኝ ሲሆን የቴሌቪዥን ትምህርት ዝግጅቶችን ከ4ኛ ክፍል እስከ 8ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች፣ የሂሳብ ትምህርት በአማርኛ፣ በአፋን ኦሮሞ፣ በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርትን ሳምንቱን ሙሉ ተደራሽ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በቅርቡ መስከረም 2018 ዓ.ም መጨረሻ ላይ በኃይማኖቶች መካከል መቻቻል እና መከባበር እንዲሰፍን ብሎም አንድነት እንዲጠናከር ላበረከተው አስተዋፅኦ የአዲስ አበባ የኃይማኖት ተቋማት ጉባኤ እውቅና ሰጥቶታል፡፡ ሚዲያው ተቋሙ የሚያከናውናቸውን ስራዎች ከህዝብ ዘንድ በማድረስ ከፍተኛ አበርክቶ የተጫወተ ሲሆን፤ የተለያዩ ኃይማኖታዊ በዓላትን በጥራት በቀጥታ ስርጭት እና በዜናና ፕሮግራም ሽፋን በመስጠት ኃላፊነቱን በመወጣቱ ነው እውቅና ያገኘው፡፡



ፎቶ ከገፀ ድር

ተቋሙ በትምህርት ዘርፍ ባበረከተው አስተዋፅኦ የልዩ ተሸላሚ እውቅና ባገኘበት ወቅት

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ተጠሪ ከሆኑ ተቋማት አንዱ ሲሆን፤ ለምክር ቤቱ ተጠሪ የሆኑ ተቋማት በ2017 በጀት ዓመት ላሳዩት የላቀ አፈጻጸም እውቅና በተሰጠበት ወቅት ልዩ ተሸላሚ ሆኗል፡፡ የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ካሳሁን ጎንፋ የተሰጠውን የምስክር ወረቀትና ሽልማት በተረከቡበት ወቅት እንደተናገሩት "አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየሰራ ባለው ስራ በየጊዜው ትላልቅ እውቅናዎችን እያገኘ ነው፡፡ ብለዋል። በአዲስ አበባ ምክር ቤት የተሰጠውን እውቅናን በተመለከተም፤ "እውቅና ተጨማሪ አደራ ማለት ነው፡፡ የተለየ ስራ ለመስራት፣ የተሻለ ውጤት ለማምጣት፣ ብዙ መስራት እንደሚጠበቅብንም የሚያሳይ ነው። እውቅናው አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክን ወደፊት የሚያስፈነጥር፣ እውነተኛ ተወዳዳሪና ተመራጭ ሜትሮፖሊታን ሚዲያ የመሆን ህልማችንን ለማሳካት መነሳሳት ይፈጥርልናል፡፡ በጣም ደስ ብሎናል" ብለዋል፡፡

በቅርቡ የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክን የ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት አፈፃፀምን የገመገመው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት የፍትህና መልካም አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴም ሚዲያው የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ እየተወጣ እንደሚገኝ ገልጿል፡፡ በዕለቱ በቀረበው ሪፖርት እንደተመላከተው አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በይዘት ተደራሽነት፣ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ በዲጂታል ሚዲያ እና የገቢ እድገት እንዲሁም በሽያጭ የተሻለ ውጤት አስመዝግቧል፡፡

> **"እውቅናው አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክን ወደፊት የሚያስፈነጥር፣ እውነተኛ ተወዳዳሪና ተመራጭ ሜትሮፖሊታን ሚዲያ የመሆን ህልማችንን ለማሳካት መነሳሳት የሚፈጥር ነው"**

የምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በሁሉም ዘርፍ ቀዳሚ የመረጃ ምንጭ ለመሆን የሚያደርገው ጥረት የሚበረታታ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ በምክር ቤቱ የፍትህና መልካም አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ መሀመድ ገልማ (ዶ/ር)፣ ተቋሙ በአደረጃጀቱ እና በውስጥ አሰራሩ የተሻለና ዘመናዊነትን የተላበሰ ሆኖ እንዳገኙት ገልጸዋል፡፡ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የሚያቀርባቸውን የይዘት ሥራዎችም አዝናኝ እና አስተማሪ መሆናቸውንና ለማህበረሰብም ተመራጭ ሚዲያ እየሆነ መምጣቱን ተናግረዋል፡፡

ከሶስት ወራት በፊትም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ2017 በጀት ዓመት የተሻለ አፈፃፀም ላመጡ ተቋማት እውቅና የሰጠ ሲሆን አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክም በበጀት ዓመቱ ባመጣው ስኬት ልዩ ተሸላሚ በመሆን እውቅና ተሰጥቶታል። አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች እንዲመለሱ እና ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር ያሉ ችግሮች መፍትሔ እንዲያገኙ ህዝብና አመራሩ በቀጥታ የሚወያይባቸው እንደ "ዋርካ" እና "አገልጋይ" የተሰኙ ፕሮግራሞችን በመቅረፅ፤ ነዋሪውና አስተዳደሩን በማገናኘት ረገድ ስኬታማ ተግባር ማከናወኑንና ይህም ለእውቅና እንዳበቃው የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ ተናግረዋል፡፡

"እውነቱን ለመናገር ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በጋራ የሚሰሩ ሚዲያዎች ብዙ ናቸው፡፡ ሚዲያዎች የሰራናቸውን ስራዎች ለህዝብ ጆሮ በማድረስና የተዛቡ መረጃዎችን በመመከት አብረውን እየሰሩ በመሆኑ ሁሉንም እናመሰግናለን፡፡ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ግን የከተማው ሚዲያ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን የዋርካ እና አገልጋይ ፕሮግራሞች የተለየ ነጥብ እንዲያገኝ ያደርጉታል፡፡ በ"አገልጋይ" ፕሮግራም ነዋሪው ያለምንም ገደብ በቀጥታ ስልክ በመግባት ጥያቄውን በማቅረብ በአመራሩ ቀጥታ ምላሽ ይሰጠዋል፡፡ በ"ዋርካ" ፕሮግራም ደግሞ ህዝብና አመራሩ ፊት ለፊት ተገናኝተው፣ ህዝብ በነፃነት ጥያቄውን የሚያቀርብበትና አመራሩ ምላሽ በመስጠት መግባባት የሚደረስበት መንገድ ፈጥሯል" ብለዋል ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ፡፡

የፕላንና ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ አደም ኑሪ በበኩላቸው፣ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ህዝብና መንግስትን በማገናኘት፣ በሳምንት ሰባት ቀን እና 24 ሰዓት በመስራት፣ በተለያዩ ቋንቋዎች ፕሮግራሞቹን ተደራሽ በማድረግ፣ ለዓለም አቀፍ ማህበረሰብ የከተማዋን በጎ ገፅታ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ቋንቋዎች ይዘቶችን በማሰራጨት፣ የከተማውን ነዋሪ ጉዳዮች በተለያየ መንገድ ለአስፈፃሚው በማድረስ መፍትሔ በማሰጠት ተፅዕኖው ከፍ እያለ የመጣ ተቋም በመሆኑ ልዩ ተሸላሚ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ካሳሁን ጎንፋ በበኩላቸው፣ ሚዲያው የከተማዋን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ለነዋሪው ተደራሽ እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ በይዘት፣ በአቀራረብ፣ በቴክኖሎጂ፣ በሰው ሀይል እና መሰል ዘርፎች እያደረገ ባለው እንቅስቃሴ ተመራጭ እና ተወዳዳሪ ሚዲያ እየሆነ መጥቷል፡፡ ለሚዲያው የተሰጠው እውቅናና ሽልማትም ሰራተኛውና አመራሩ እጅ ለእጅ ተያይዞ በመስራቱ የተገኘ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ "ሚዲያ ወደ ህዝብ በመውረድ የህዝብን ስሜት ማዳመጥ አለበት፡፡ በአስፈፃሚውና ህዝብ መካከል አገናኝ ድልድይ በመሆን ማገልገል አለበት፡፡ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በዚህ ረገድ በተጨባጭ ሚናውን እየተወጣ ነው፡፡" ብለዋል፡፡

እውቅናው አመራሩና ሰራተኛው የሚያደርገውን ጥረት በእጥፍ ወደፊት እንዲያሳድግ መነቃቃትን የሚፈጥር ነው ያሉት ዋና ስራ አስፈፃሚው፤ አዳዲስ ሀሳቦችን በማመንጨትና ፈጠራ በተሞላበት መንገድ በመስራት፣ ህዝብን በማሳተፍ፣ ድምፅ ለሌላቸው ድምፅ በመሆን ሚዲያው ይበልጥ ተወዳዳሪ እንዲሆን አመራሩና ሰራተኛው በመቀናጀት እንደሚሰሩ ማንሳታቸው ይታወሳል፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከላይ ካነሳነው በተጨማሪ በቅርብ ጊዜ በተለያዩ የከተማ አስተዳደሩና የፌዴራል ተቋማት እውቅናዎችን ማግኘቱ ይታወሳል፡፡

# ፓርላማው በውሎው፡-

- **መንግስት ግጭቶችን ለመፍታት ሰላማዊ መፍትሔን እንደሚያስቀድም ተገልጿል**
- **መጪውን ሀገር አቀፍ ምርጫ ለማከናወን መንግስት በቂ አቅም እንዳለው ተጠቁሟል**

**በስንታየሁ ምትኩ**

ያለፈው 2017 በጀት ዓመት ኢትዮጵያ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉልህ ፋይዳ ያላቸው ልማቶችንና ስራዎችን ያከናወነችበት ነው፡፡ "ይቻላሉ" ተብሎ የማይታሰቡ ጉዳዮች እውን የሆኑበት ዓመት ነው፡፡ የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት ታዬ አፅቀሥላሴ መስከረም 26 ቀን 2018 ዓ.ም የህዝብ ተወካዮች እና የፌሬሽን ምክር ቤቶች የጋራ መክፈቻ ስብስባ ላይ ያደረጉት ንግግር ይህንን ሀሳብ ያጠናክራል፡፡


ፎቶ- ከገፀ ድር
ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ተገኝተው ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት

በ2017 በጀት ዓመት የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በማድረግ የመንግስትን ገቢና የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በማሳደግ፣ የግብርና ምርታማነትን በማሳደግ፣ የማዕድንና የቱሪዝም ሀብቶችን በማልማት፣ የአረንጓዴ አሻራን ግብን በማሳካትና በሌሎችም መስኮች በተከናወኑ ስራዎች ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

የ2018 ዓ.ም መባቻ የዘመናት የቁጭት ምክንያት እና የትብብርና አንድነት ማሳያ የሆነው የታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ የተመረቀበት፣ በወርሃ መስከረም መጀመሪያ ደግሞ የተፈጥሮ ጋዝ መውጣት የጀመረበት፣ የማዳበሪያ ፋብሪካ ግንባታና ሌሎች ትላልቅ ፕሮጀክቶች መሰረት የተጣለበት በኢትዮጵያ ታሪክ የሚወሳ አዲስ ምዕራፍ የተከፈተበት እንደሆነ ማንሳታቸው ይታወሳል፡፡

ፕሬዝዳንቱ መንግስት በ2018 በጀት ዓመት ነፃና ገለልተኛ ተቋማትን በመገንባት፣ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ በመፍታት፣ የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥን እና የፍትህ ስርዓቱን በማዘመን በትኩረት እንደሚሰራ መጠቆማቸው አይዘነጋም። የስራ ዕድል በመፍጠር፣ የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን፣ የማዳበሪያ ፋብሪካ ግንባታውን በማፋጠን፣ የአምራች ኢንዱስትሪውን በመደገፍ፣ የቱሪዝም መዳረሻዎችን በማልማት እንዲሁም በሌሎች መስኮችም በርካታ ስራዎችን በማከናወን በጥቅሉ በኢኮኖሚ ረገድም የ9 በመቶ እድገት ለማስመዝገብ እንደሚሰራ ማንሳታቸው ይታወሳል፡፡

ጥቅምት 18 ቀን 2018 ዓ.ም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባካሄደው 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ፤ ፕሬዝዳንት ታዬ አጽቀሥላሴ ለሕዝብ ተወካዮች እና የፌዴሬሽን ም/ቤቶች የጋራ ስብሰባ ባቀረቡት የመንግስት የ2018 በጀት ዓመት የመንግስት የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ በመንተራስ የተለያዩ አስተያየትና ጥያቄዎችን ሰንዝረዋል። የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

## ሰላምና ፀጥታ

የምክር ቤት አባላት መንግስት ግጭቶችን ለመፍታት ቅድሚያ ለሰላም በመስጠት የሚሰራው ስራ የሚደነቅ መሆኑን አንስተው በሌላ በኩል አሁንም የሰላምን ጥሪ ባለመቀበል ህዝብን ለስቃይ እየዳረጉ ያሉ ሀይሎችን ለማስቆም ምን እየተሰራ ነው? የሚል ጥያቄ አንስተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሰጡት ምላሽም፤ ኢትዮጵያ ደካማ ሆና እንድትኖርና በሁለት እግሯ መቆም እንዳትችል የሚሰሩ ሀገራት አሉ፡፡ ኢትዮጵያውያን ብሔራዊ ጥቅምን በሚጎዳ መልኩ የፖለቲካ ፍላጎትን ለማሳካት ከእነዚህ አካላት ጋር የሚሰሩ ከሆነ የተሟላ ሰላም ማምጣት እንደሚያስቸግር ጠቁመዋል፡፡

"በአፍሪካ በመሳሪያ አፈሙዝ በማሸነፍ ስልጣን የያዙ ሀይሎች ቢኖሩም አንዳቸውም ለሀገራቸው ሰላምና ልማትን ማረጋገጥ አልቻሉም" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፣ በኢትዮጵያም ኢህአዴግ በሀይል አሸንፎ ስልጣን ቢይዝም ለሰላሳ ዓመታት ሰላም የነበረበትን አካባቢ እንኳን ሳይቀር ከስንዴ እርዳታ ማውጣት አልቻለም ብለዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) እንደገለፁት፤ መንግስት ሰላምን ለማረጋገጥ ጥያቄ ካላቸው ሀይሎች ጋር ውይይትን በማስቀደም ችግሮችን ለመፍታት እየሰራ ይገኛል፡፡ ለአብነትም በኦሮሚያ ክልል ከሚንቀሳቀሰው ሸኔ ጋር በሰላማዊ መንገድ በመነጋገር ከፊሉ ሀይል ወደ ሰላም እንዲመጣ ማድረግ ተችሏል፡፡ በትግራይም ካሉ ወገኖች ጋር በመወያየት ሰላም እንዲፈጠር በማድረግ ከፊሎቹ ስልጣን ተሰጥቷቸው እየሰሩ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ከምንም በፊት ከግል ይልቅ የሀገር ጉዳይን በማስቀደም እየተሰራ እንደሆነ አንስተዋል፡፡

በኦሮሚያም ሆነ አማራ ክልል የሰላምን ጥያቄ ባለመቀበል እየተንቀሳቀሱ ያሉ ሀይሎች "ተላላኪና ዓላማ የሌላቸው ናቸው" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) "መንግስት አሁንም ጥያቄ አለን ከሚሉ ሀይሎች ጋር ለመወያየት በሩ ክፍት ነው፡፡ ማንም ሰው ሰላማዊ መንገድን መርጦ፣ ህግና ስርዓት አክብሮ የሚመጣ ከሆነ ለመታረቅ ብቻ ሳይሆን አብረን ለመስራት ዝግጁ ነን" ብለዋል፡፡

ያደሩና አሁን መፈታት የማይችሉ ችግሮችን ደግሞ አካታች የሆነ ሀገራዊ ምክክር በማድረግ እየተሰራ እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አብራርተዋል። ከውይይትና ምክክር ባሻገር የቆዩ በደሎችንና ቁስሎችን በሽግግር ፍትህ አማካኝነት በእርቅና ፍትህ ለመፍታት እየተሰራ እንደሚገኝ አንስተዋል። የታጠቁ ሀይሎችን ደግሞ ትጥቅ ለማስፈታትና መልሶ ለማቋቋምና ወደ ሰላማዊ ህይወት ለማስገባት ሀብት ተመድቦ እየተሰራበት ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ከታጠቁ ሀይሎች መካከል ለመደራደር ለመንግስት ጥያቄ የሚያቀርቡና የሚነጋገሩ አሉ፡፡ ይሁን እንጂ በውጭ የሚኖሩ፣ አዲስ አበባ ጭምር የሚገኙና መንግስት "እንዲታረቅ" የሚጠይቁ ሀይሎች ሳይቀሩ "እንዳትደራደሩ" በሚል እንደሚያደናቅፉና ይህም አሳዛኝ እንደሆነ አንስተዋል፡፡ "አሁንም ለሰላማዊ ትግል በራችን ክፍት ነው፤ ካልተደመርንና ካልተጋገዝን በስተቀር የኢትዮጵያን ችግር ባጠረ ጊዜ መፍታት አይቻልም" ሲሉ የሀገርን ውስብስብ ችግሮችን ለመፍታት መተባበር አስፈላጊ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

በሰሜን ኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት በፌዴራል መንግስትና ህወሓት መካከል የተደረሰውን የፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት ወደጎን በማድረግ የህወሓት ቡድን ከውጭ ሀይሎች ጋር በመሆን ዳግም ጦርነት ለመክፈት እየተንቀሳቀሰ በመሆኑ የትግራይን ክልል ሰላማዊ ለማድረግ ምን እየተሰራ ነው? የሚል ጥያቄም ከምክር ቤት አባላት ተነስቷል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሰጡት ምላሽም፤ በፕሪቶሪያ ስምምነት ሕወሓት ያካሄደው ህገ ወጥ ምርጫ እንዲሰረዝ፣ ምርጫውን መሰረት በማድረግ የተቋቋመው ህጋዊ ያልሆነው መንግስት እንዲፈርስና ምክር ቤቱ እንዲበተን፣ ጊዜያዊ አስተዳደር እንዲቋቋም፣ የታጠቁ ሀይሎች ትጥቅ እንዲፈቱ፣ የተፈናቀሉ ወገኖች ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ፣ የውጭ ግንኙነት፣ የፀጥታና መከላከያ ጉዳዮችን የሚመለከተው የፌዴራል መንግስትን ብቻ እንደሆነ መግባባት መደረሱን አብራርተዋል፡፡

በአማራና ትግራይ ክልሎች "የይገባኛል ጥያቄ" የሚቀርብባቸው አከራካሪ አካባቢዎችን በተመለከተም በህገ መንግስቱ መሰረት በህዝብ ወሳኔ ምላሽ እንደሚያገኝ ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፣ የህወሓት ቡድን በጦርነቱ የተፈናቀሉ ወገኖች ወደቀያቸው እንዳይመለሱ በማድረግ እየፈጠረው ያለው ቀውስ ህዝብ ላይ ችግር እየፈጠረ ነው።

የወልቃይት ጉዳይ በሰላማዊና በህጋዊ መንገድ ካልተፈታ ዘላቂ የሆነ ሰላምን ማምጣት እንደማያስችል ተናግረዋል፡፡

ሕወሓት በሰከነ መንገድ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አክብሮ በመንቀሳቀስና ትክክለኛ ጉባኤ በማድረግ ህጋዊ ፓርቲ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህ ባሻገር ከውጊያ ይልቅ የትግራይ እናቶች የሚፈልጉትን ሰላም ማምጣት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም የፌዴራል መንግስቱ ዝግጁ እንደሆነና በትግራይ በኩል ያሉትም ይህንን በመገንዘብ መስራት እንዳለባቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) አንስተዋል፡፡

ከምክር ቤት የሀገራዊ ምክክሩ ሂደቱን በተመለከተ ለተነሳው ጥያቄም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) እንደገለፁት በአሁኑ ወቅት ከሞላ ጎደል የምክክሩ አጀንዳዎች ተሰባስበዋል፡፡ ሀገራዊ ምክክሩ ችግሮቻችን ለመፍታት መፍትሔ ይሆናል ያሉ አካላትም በሂደቱ ተሳትፈዋል፡፡ ሀገራዊ ምክክሩ "አያስፈልግም" ያሉት ደግሞ አልተሳተፉም፡፡ ሀገራዊ ምክክሩ በርካታ ጠቃሚ ግብአቶች የተገኙበትና ቀሪ ተግባራትም ሂደቱን ጠብቆ እንደሚከናወን ጠቁመዋል፡፡

ከመጪው 7ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ጋር በተያያዘም ያሉ የፀጥታ ሁኔታዎችን በማንሳት ምርጫ ላይደረግ ይችላል በሚል የሚነሱ ስጋቶችን በተመለከተም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሰጡት ማብራሪያ፤ ምርጫው በተያዘለት ጊዜ ይካሄዳል። ለዚህም መንግስት በቂ አቅም አለው። አማራጭ ድምፆች ያሉበት ምክር ቤት እንዲኖር መንግስት ከባለፈው ሀገር አቀፍ ምርጫ የተሻለ፣ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲኖር በኃላፊነት እንደሚሰራ ተናግረዋል፡፡

## ሪፎርም

ሌላው ከምክር ቤት አባላት የተነሳው ጥያቄ መንግስት መልካም አስተዳደርና ብልሹ አሰራሮችን ለመቅረፍ ምን እየሰራ ይገኛል? የሚል ሲሆን ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሰጡት ምላሽም፤ የህግ አስከባሪ ተቋማት ላይ ሪፎርም በማድረግ የተሻለ ቁመና እንዲኖራቸው ማድረግ ተችሏል፡፡ በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ የሚታየውን የህዝብን እሮሮ ለመቀነስም የተለያዩ አገልግሎቶች በአንድ ማዕከል የሚሰጡበት የመሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎት ተጀምሯል፡፡ አሁን ላይም 18 የመሶብ አንድ ማዕከላት ተቋቁመው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ በቅርቡ የሚጨመሩ ሶስት ማዕከላትን በመጨመር በዚህ ዓመት 100 ለማድረስ እየተሰራ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

በሪፎርሙ ዲጂታል ኢትዮጵያን ለመፍጠር በተሰራው ስራም ውጤት መገኘቱን ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንስተዋል። 2 ነጥብ 4 ሚሊዮን ወጣቶች በአምስት ሚሊዮን የኮደርስ ንቅናቄ ስልጠና በመውሰድ የምስክር ወረቀት አግኝተዋል። ይህም ለብዙ ስራዎች አጋዥ እንደሚሆን አብራርተዋል፡፡

## ማህበራዊ ጉዳይ

መንግስት የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ምን እየተሰራ ይገኛል? የሚልም ከምክር ቤት አባላት ጥያቄ የተነሳ ሲሆን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሰጡት ምላሽ፤ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ዋናው ቅድመ ልጅነት ላይ መስራት ስለሆነ በስፋት እየተሰራበት ይገኛል፡፡ ለመምህራን ስልጠና በመስጠት፣ በሸርቸዋል በማስደገፍ ትምህርትና ፈተና በመስጠት፣ መጽሐፍትን ተደራሽ በማድረግ፣ በትምህርት ለትውልድ ሀብት በማሰባሰብ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ በማሻሻል፣ አዋኪ ተግባራትን በመከላከልና በተማሪዎች ምገባ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል በሚሰራው ስራ ውጤት እየተገኘ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

ወደ ገጽ 25 ዞሯል

# የወንጀል ሕግ ምንነት፣ አላማው እና መከላከያ መንገዶቹ

(ክፍል አንድ)

ይነበብ ታምሩ (ዐቃቤ ህግ)

## ወንጀል ምንድን ነው?

ወንጀል የሚባለው ምን አይነት ድርጊት ነው የሚለውን ስንመለከት። የወንጀል ትርጉም አሁን ላይ ከማህበረሰብ ማህበረሰብ ወይንም ከሀገር ሀገር የሚለያይ እና ቋሚ የሆነ ትርጉም የሌለው በመሆኑ ዛሬ ወንጀል ተብሎ በሕግ የተደነገገ ድርጊት ከዚህ በፊት ወንጀል ላይሆን ይችላል፤ እንዲሁም ከዚህ በፊት በወንጀል ሕግ የተደነገገ፤ ነገር ግን አሁን ላይ እንደ ወንጀል የማይቆጠርበት ሊሆን ይችላል።

እንደ ሀገራችን የወንጀል ሕግ ስናየው ወንጀል ማለት በወንጀል ሕግ በዝርዝር ተለይተው የተከለከሉ ድርጊቶችን መፈፀም (commission) ወይንም እንዲፈጽሙ ትዕዛዝ ወይንም ግዴታ የተጣለባቸውን ድርጊት አለመፈፀም (omission) ነው። በዚህ መሰረት የወንጀል ሕጉ ኃላፊነትን የማያስከትል ተግባር የፈፀሙ ሰዎች በወንጀል እንደዳይጠየቁ ማድረጊያ፤ ወንጀል ያደረጉ ሰዎችም በሕጉ ከተመለከተው ቅጣት ውጭ በዘፈቀደ ኢ-ሰብአዊ በሆነ መንገድ እንዳይቀጡ መከላከያ መሳሪያ ነው። ለዚህ ትልቁ ማሳያ ደግሞ በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 19 እና 20 ላይ በትኩረት ተቀምጧል፡፡ በተለይም በአንቀጽ 20(3) ላይ በግልጽ ማንኛውም ወንጀል ሰርቷል ተብሎ የተጠረጠረ ሰው በፍርድ ሂደት ላይ እያለ እንደ ወንጀለኛ ያለመቆጠር እና በራሱ ላይ ምስክር ያለመሆን መብት አለው፡፡

## ወንጀል ከማህበረሰብ መልካም ስነ ምግባር ጥሰት በምን ይለያል?

ከላይ በመግቢያችን ላይ የተቀመጡትን ሁነቶች መሰረት አድርገን ልዩነቱን ስናየው፤ በመጀመሪያ ደረጃ አንድ ወንጀል በአንድ ሀገር ውስጥ ወንጀል ተብሎ ለመገለጽ እና እንደ ጥፋት የሚቆጠረው በሀገሪቱ የወንጀል ህግ ላይ በግልጽ እና በማያጠራጥር ሁኔታ ወንጀል መሆኑ ሲደነገግ ነው፡፡ ለምሳሌ አሁን በስራ ላይ ባለው የወንጀል ህግ ላይ ሰው መግደል፣ የሴት ልጅ ጠለፋ እና የመሳሰሉት በወንጀል ህግ አንቀጽ 539 እና 587 በተከታታይነት ወንጀል እንደሆኑ እና እነዚህን ጥፋቶች ተላልፎ የተገኘ ህጋዊ ሂደቱን ተከትሎ ቅጣቶችን የሚቀጣ መሆኑን በግልጽ ይደነግጋል፡፡

የማህበረሰብ የመልካም ስነ ምግባር ጥሰቶች የምንላቸው በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ እንደ ህግ የሚታዩ እና እነዚህን የማህበረሰብ መልካም የስነ ምግባር ህጎች ተላልፎ መገኘት በዛ ማህበረሰብ ውስጥ እንደ ትልቅ ነውር እና ጥፋት የሚቆጠር ሲሆን፤ አልፎም እነዚህን ህጎች የተላለፈ ከላይ የተጠቀሰውን



አይነት ጥቃት እንዲደርስ እንደመነሻ የሚወሰድ፡፡ ነገር ግን እነዚህ እንደ መልካም ስነ ምግባር የሚቆጠሩ ነገሮች ከማህበረሰብ ማህበረሰብ የተለያዩ ናቸው፡፡ ይህም ማለት አንድ አካባቢ ላይ እንደ ጥሩ ስነ ምግባር የሚቆጠሩ ነገሮች ሌላው ማህበረሰብ ዘንድ በመጥፎ ነገር ሊታወቁ ይችላሉ፡፡ ለዚህ ዋነኛ የመለያያ ምንጫቸው ደግሞ የማህረሰቡ ሀይማኖት፣ ባህል፣ አኗኗር ዘይቤ እና እሴት ጋር የተገናኘ ነው፡፡

በአንድ ማህበረሰብ ዘንድ እንደ መልካም ስነ ምግባር የተቀመጡ መገለጫዎችን ጥሶ መገኘት በወንጀል ህጉ በግልጽ ተደንግገው ካልተቀመጡ በስተቀር ሁሉም አያስቀጡም፡፡ ለምሳሌ በአብዛኛው በአገራችን ክፍል ታላላቆችን ማክበር፤ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሰው አይነት በየአካባቢው ትላልቅ አባቶች የሚወሰኑ ድርጊቶች እና ከፍ ያለ ቦታ መስጠት እንደመልካም ስነ ምግባር የሚታይ እና ይህንን የማያደርግ እሴቱን አንደጣሰ የሚቆጠርበት ሁኔታ አለ ነገር ግን ይህ ታላላቆችን አለማክበር ወንጀል ስለመሆኑ በወንጀል ህጉ ተደንግጎ ካልተቀመጠ ይህንን ተላልፎ መገኘት ወንጀል የሚሆንበት አግባብ የለም ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በአንዳንድ አካባቢዎች በተለይም በገጠሩ ክፍል እንደ ባህል እና መልካም ድርጊት ተቆጥረው በየጊዜው እየተከናወኑ የሚገኙ ለምሳሌ እንደ የሴት ልጅ ግርዛት፣ ያለ እድሜ ጋብቻና የመሳሰሉት ድርጊቶች የሴት እህቶቻችንን ብዙ መብቶች የሚገፍና ሴቶች ከወንዶች እኩል ሰርተው እና ተምረው ለራሳቸው ብሎም ለሀገራቸው አስተዋፅዖ እንዳያደርጉ እስካሁንም ድረስ ትልቅ ማነቆ የሆነ ወንጀል ሲሆን ይህንን ችግር ለመቅረፍ መንግስት ከተለያዩ አካላት ጋር በትብብር እየሰራበት ቢሆንም መቀነስ እንጂ ፈጽሞ ሙሉ ለሙሉ ማጥፋት ያልተቻለበት ሁኔታ ነው ያለው። ይህንን አሳሳቢ ችግር ለመቅረፍም መንግስት አንድ መፍትሔ አድርጎ የወሰደው በሀገሪቱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 565 እና 648 በማካተት ይህንን ተላልፎ የሚገኝ ግለሰብ ላይ ቅጣት እንደሚጣል በግልጽ አስቀምጧል፡፡

የህዝቦች ባህል እንዲከበር ሕገ መንግስቱ ይደነግጋል እንዲሁም ህዝቦች የማያምኑበት እና የማይደግፉት ሕግ ማውጣቱ ጥቅም የለውም፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ሕግ አውጭው ዘመናዊ ሕግ በማወጣት ህብረተሰቡን በማስተማርና በመምራት ከጎጂ ባህሎች ራሱን እንዲያላቅቅ ማድረግ እንደሚገባ በወንጀል ህግ የሚደገፍ ጉዳይ ነው፡፡

ከዚህ በዘለለ የወንጀል ህግን ተላልፎ የተገኘን ግለሰብ መንግስት የህብረተሰቡን ሰላም ለመጠበቅ ሲል ፖሊስ እና ዓቃቤ ህግን በመመደብ የወንጀል ድርጊት የፈፀመውን አካል ከራሱ ጥፋት እንዲማር እና ተጨማሪ ድርጊት ከመፈፀም እንዲታቀብ ሌላው የህብረተሰብ ክፍል ደግሞ ከወንጀል አድራጊዎች ተምሮ የወንጀል ህግ ተላልፎ እንዳይገኝ አስተማሪ በሆነ እና ሰብዓዊ መብቱን በጠበቀ መልኩ ቅጣት እንዲጣልበት ያደርጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ራሱን የቻለ መንግስታዊ ተቋም አለ። ነገር ግን በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ እንደ መልካም ስነ ምግባር የሚቆጠሩ ድርጊቶችን ተላልፎ የሚገኝን አካል ተከታትሎ የሚቀጣ አሰራር በተቋም ደረጃ የለም፡፡

## የወንጀል ሕግ አላማ

የወንጀል ሕግ እንደሌሎች ሕጎች ሁሉ ለአንድ ማህበረሰብ ሰላማዊ አኗኗር ብሎም ለሀገር እድገት አንድ መሰረት ነው። ሰላማዊ ህይወት መኖር እና የዜጎች መብት መከበር በአንድ ሀገር ላይ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ተቋማት ትልቁን ሚና ይጫወታሉ። እነዚህ ተቋማት ሕግ አውጭ፣ ሕግ ተርጓሚ እና ሕግ አስፈጻሚ ሲሆኑ ሦስቱም የራሳቸው ሚና ቢኖራቸውም አንዱ ያለአንዱ ግን ምንም ማለት ናቸው። ሕግ አውጭው የምንለው ከፍተኛው የሀገሪቱ የስልጣን ባለቤት በሀገሪቱ ውስጥ ምን ምን ድርጊቶችን መፈፀም ወንጀል እንደሆነ ወይም ደግሞ ምን አይነት ድርጊቶችን አለማድረግ በምን መልኩ ተጠያቂ እንደሚያደርግ እና ሕጉን ተላልፈው የሚገኙ አካላት በምን መልኩ ቢቀጡ ነው ከፈፀሙት የወንጀል ድርጊት ሊማሩ የሚችሉት እንዲሁም ከነሱ አልፎ ሌላውን ማህበረሰብ ሊያስተምር እና ተጨማሪ ወንጀል እንዳይፈጽም ሊያደርግ የሚችለው ቅጣት የትኛው ነው በሚለው ላይ በዝርዝር ሕግ ማውጣት ያስቀምጣል። ሕግ ተርጓሚውም በሕግ አውጭው የወጣውን ሕግ ተላልፈው በሚገኙ አካላት ላይ በሚቀርቡለት ማስረጃዎች እንዲሁም ሕጉን መሰረት አድርጎ ውሳኔውን ይሰጣል። ሌላው እና የመጨረሻው ሕግ አስፈጻሚው አካል ወንጀል እንዳይፈፀም ይከላከላል ተፈፅሞ ከሆነ ደግሞ ተጠርጣሪዎችን ይዞ ለፍርድ በማቅረብ ተገቢ የሆነ ቅጣት አግኝተው ከስህተታቸው ታርመው ወደ ቀደመ ሰላማዊ ህይወታቸው እንዲመለሱ ያደርጋል። ስለሆነም የሀገራችን የወንጀል ሕግ ዋነኛ አላማ አስቀድሞ የወንጀል አይነቶችን ለህብረተሰቡ አባላት በማሳወቅ ህብረተሰቡ ከጥፋት እንዲታቀቡ ይሰራል። ይህንን አውቀው ጥንቃቄ በማያደርጉ ላይ ደግሞ ሕጉ ተገቢነት እና ያስተምራል የሚለውን ቅጣት በመጣል ከጥፋታቸው እንዲማሩ ያደርጋል። በመሆኑም ሀገራችን ኢትዮጵያ ይህንን ግብ ከዳር ለማድረስ በተለያየ ጊዜ የወንጀል ህግ በተግባር ላይ አውላለች።

የመጀመሪያው እና በዘመናዊ መልክ በ1923 ዓ.ም. ላይ ከወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ጀምሮ አሁን በስራ ላይ እስካለው የወንጀል ሕግ ድረስ በተለያየ ጊዜ ሲሻሻል ቆይቷል፡፡ ለዚህ ደግሞ ዋነኛ ምክንያቱ የወንጀል ተለዋዋጭ ባህሪ እንዲሁም በሀገሪቱ ላይ በሚፈጠረው ፖለቲካዊ፤ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ለውጦች እንዲሁም በወንጀለኛ መቅጫው ላይ የሚታየው የቴክኖሎጅ ዕድገትና የዘመናዊ ኑሮ ውስብስብነት የወለዳቸውን ወንጀሎች አለማካተቱ እንዲሁም የኮፒውተር ወንጀል፣ በወንጀል የተገኘ ገንዘብን ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን የመሳሰሉት ህጎች ባለመካተታቸው እና ክፍተት በመፈጠሩ በ1997ዓ.ም. ከላይ የተጠቀሱትን የወንጀል አይነቶች እንዲሁም ሌሎች አዳዲስ ሕጎችን በማካተት በስራ ላይ ውሏል።

በ1997 ዓ.ም. የወጣው አዲሱ የወንጀል ሕግ ዋነኛ አላማዎቹ ተብለው በመጀመሪያው አንቀጽ የተጠቀሱት የሚከተሉት ናቸው፡፡

አንባቢዎቻችን ክፍል ሁለት በሚቀጥለው ሳምንት ይዘን እንቀርባለን።

# የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን

## የ7ኛው ዙር የ40/60 እና 1ኛ ዙር የካፒታል ፕሮጀክት (5 ሺህ ተገጣጣሚ) ንግድ ቤቶች ጨረታ ውጤት

የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የ7ኛው ዙር 40/60 እና የ1ኛው ዙር በካፒታል ፕሮጀክት የተገነቡ በ5 ሺህ ተገጣጣሚ ቤቶች ላይ የሚገኙ ንግድ ቤቶች ለተጠቃሚዎች ለማስተላለፍ ግልጽ ጨረታ ማውጣቱ ይታወቃል። በመሆኑም በጨረታው የተሳተፉ ተጫራቾች የአሸናፊዎች ዝርዝር (ከ1ኛ እስከ 3ኛ ደረጃ የወጡ ተወዳዳሪዎች) ዝርዝር  እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል፡-

| ተ/ቁ | የተጫራች ሙሉ ስም | ጾታ | የደረሰኝ ቁጥር | ክፍለ ከተማ | ሳይት | ብሎክ - የቤት ቁጥር | ተጫራቹ ያስገባው ዋጋ | ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Gemechu Gutu Terefe | M | 418144 | ቦሌ | ቦሌ ቡልቡላ ሎት1 | 2 - BBL1/B-02/SN/005 | 69,223.71 | 1 |
| 2 | LINA DEJENE TESFAYE | F | 316190 | ቦሌ | ቦሌ ቡልቡላ ሎት1 | 29 - BBL1 /B-29/SN/003 | 71,225.00 | 1 |
| 3 | zerfe Bekele Weldeyes | F | 628775 | ቦሌ | ቦሌ ቡልቡላ ሎት2 | 38 - BBL2 /B-38/SN/004 | 68,724.00 | 1 |
| 4 | Metadel Taye Nigatu | F | 421566 | ቦሌ | ቦሌ ቡልቡላ ሎት2 | 42 - BBL2 /B-42/SN/009 | 69,565.00 | 1 |
| 5 | Elias Eshetu Dejene | M | 448204 | ቦሌ | ቱሪስት | 4 - TOU/B-04/SN010 | 70,125.00 | 1 |
| | Henok Dessie Gebrtsadik | M | 478482 | ቦሌ | ቱሪስት | 4 - TOU/B-04/SN010 | 69,800.00 | 2 |
| | Sintayehu Abebe Desta | M | 949217 | ቦሌ | ቱሪስት | 4 - TOU/B-04/SN010 | 69,000.00 | 3 |
| 6 | kalkidan nardos yeshitela | F | 970015 | ቦሌ | ቱሪስት | 8 - TOU/B-08/SN009 | 86,230.00 | 1 |
| | Sewmahon Abebaw Yenesew | M | 252514 | ቦሌ | ቱሪስት | 8 - TOU/B-08/SN009 | 70,500.00 | 2 |
| 7 | Tadesse Degu Amedie | M | 131597 | ቦሌ | ቱሪስት | 8 - TOU/B-08/SN010 | 75,100.00 | 1 |
| | Habtu Demeke Haile | M | 120392 | ቦሌ | ቱሪስት | 8 - TOU/B-08/SN010 | 69,900.00 | 2 |
| 8 | Nahom GASHAW Gashaw | M | 275860 | ቦሌ | እህል ንግድ | 1 - EN/B-01/SN/008 | 84,307.55 | 1 |
| | Asnakech Gosaye Badblcha | F | 457174 | ቦሌ | እህል ንግድ | 1 - EN/B-01/SN/008 | 70,101.00 | 2 |
| | Aster Alebachew Yimer | F | 679361 | ቦሌ | እህል ንግድ | 1 - EN/B-01/SN/008 | 70,000.00 | 3 |
| 9 | አብድረህማን ነጅሙ አብደላ | M | 842757 | አዲስ ከተማ | አስኮ | 6 - AS/B-6/SN/G06 | 72,250.00 | 1 |
| 10 | ዋለልኝ admasu tegngne | M | 142909 | ለሚኩራ | ሰሚት | 4 - SUM/B-4/SN/004 | 68,601.00 | 1 |
| 11 | Bereket Gidey Aberha | M | 809852 | ለሚኩራ | ሰሚት | 8 - SUM/B-8/SN/101 | 101,000.00 | 1 |
| | Nega Yizengaw Mihret | M | 716875 | ለሚኩራ | ሰሚት | 8 - SUM/B-8/SN/101 | 70,700.00 | 2 |
| 12 | bereket gidey abrha | M | 243260 | ለሚኩራ | ሰሚት | 9 - SUM/B-9/SN/101 | 89,000.00 | 1 |
| | Asferaw Yizengaw Mihret | M | 798808 | ለሚኩራ | ሰሚት | 9 - SUM/B-9/SN/101 | 70,600.00 | 2 |
| | ጌትሽ አበራ ይትረፍ | M | 331131 | ለሚኩራ | ሰሚት | 9 - SUM/B-9/SN/101 | 70,590.00 | 3 |
| 13 | Getachew Wolie Yimam | M | 500709 | ለሚኩራ | መሪ ሎቄ | 1 - ML/B-01/SN/208 | 69,716.21 | 1 |
| 14 | Tizita Adbaru Endalew | F | 237341 | ለሚኩራ | መሪ ሎቄ | 3 - ML/B-03/SN/107 | 77,011.00 | 1 |
| | Mikael tesfu Tesfu Bekele | M | 912661 | ለሚኩራ | መሪ ሎቄ | 3 - ML/B-03/SN/107 | 71,010.00 | 2 |
| | ZARECON Constraction Plc PLC PLC | M | 214425 | ለሚኩራ | መሪ ሎቄ | 3 - ML/B-03/SN/107 | 68,519.19 | 3 |
| 15 | Endalk kassaw Birara | M | 236063 | ለሚኩራ | መሪ ሎቄ | 4 - ML/B-04/SN/006 | 69,000.19 | 1 |
| 16 | TESFACHEW TILAHUN DEGNEH | M | 755680 | ለሚኩራ | መሪ ሎቄ | 4 - ML/B-04/SN/201 | 72,600.00 | 1 |
| | girmay Kahsay Desta | M | 750632 | ለሚኩራ | መሪ ሎቄ | 4 - ML/B-04/SN/201 | 70,232.00 | 2 |
| | Eyob Asnake Derib | M | 795588 | ለሚኩራ | መሪ ሎቄ | 4 - ML/B-04/SN/201 | 68,600.00 | 3 |
| 17 | ይመር ንጋቱ አራጋው | M | 902674 | ለሚኩራ | መሪ ሎቄ | 6 - ML/B-06/SN/008 | 75,550.00 | 1 |
| 18 | Zelalem Assefa Werku | M | 314740 | ለሚኩራ | መሪ ሎቄ | 6 - ML/B-06/SN/012 | 68,601.00 | 1 |
| 19 | ብርሀን ዘሩ ሀይሌ | F | 442831 | ለሚኩራ | መሪ ሎቄ | 9 - ML/B-09/SN/012 | 73,100.00 | 1 |
| 20 | Samuel Asnakew Nigussie | M | 240574 | ለሚኩራ | መሪ ሎቄ | 11 - ML/B-11/SN/010 | 73,100.00 | 1 |
| | ደምሰው አለሙ አባተ | M | 999213 | ለሚኩራ | መሪ ሎቄ | 11 - ML/B-11/SN/010 | 71,200.00 | 2 |
| | Abosent Bewoketu Tequarie | F | 698713 | ለሚኩራ | መሪ ሎቄ | 11 - ML/B-11/SN/010 | 68,619.00 | 3 |
| 21 | ቀመርያ ከማል ጀዋር | F | 273317 | ለሚኩራ | መሪ ሎቄ | 13 - ML/B-13/SN/003 | 71,150.00 | 1 |
| 22 | Abiy Shewarega Sahelemichael | M | 866112 | ለሚኩራ | በሻሌ | 13 - BESH-B13/SN/007 | 75,101.00 | 1 |
| 23 | MARTHA Woldemedhin TADESSE | F | 848308 | ለሚኩራ | በሻሌ | 13 - BESH-B13/SN/211 | 73,000.00 | 1 |
| | Samuel Girma Assefa | M | 493450 | ለሚኩራ | በሻሌ | 13 - BESH-B13/SN/211 | 71,000.00 | 2 |
| 24 | Yedilfana Setarge Mekonnen | M | 770043 | ለሚኩራ | በሻሌ | 20 - BESH-B20/SN/109 | 68,651.00 | 1 |
| 25 | Tirwork Gezahagn Yitbarik | F | 402051 | ለሚኩራ | በሻሌ | 45 - BESH-B45/SN/101 | 70,000.00 | 1 |
| | Nayzgi Mamo Brhane | M | 830724 | ለሚኩራ | በሻሌ | 45 - BESH-B45/SN/101 | 68,621.13 | 2 |
| 26 | Asmarech Arega Kassa | F | 929356 | ለሚኩራ | በሻሌ | 13 - BESH-B13/SN/201 | 70,000.00 | 1 |
| 27 | Sewmahon Abebaw Yenesew | M | 257995 | ለሚኩራ | በሻሌ | 13 - BESH-B13/SN/102 | 69,500.00 | 1 |
| 28 | Belay Teferra Ketemaw | M | 572773 | ለሚኩራ | በሻሌ | 40 - BESH-B40/SN/002 | 75,755.00 | 1 |
| 29 | Kirsty Tsehaye Retta | F | 342608 | ለሚኩራ | በሻሌ | 2 - BESH-B02/SN/010 | 80,100.00 | 1 |
| | Tsadik Getachew Arega | M | 822348 | ለሚኩራ | በሻሌ | 2 - BESH-B02/SN/010 | 74,100.00 | 2 |

| ተ/ቁ | የተጫራች ሙሉ ስም | ጾታ | የደረሰኝ ቁጥር | ክፍለ ከተማ | ሳይት | ብሎክ - የቤት ቁጥር | ተጫራቹ ያስገባው ዋጋ | ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 30 | Meron Getachew Arega | F | 558404 | ለሚኩራ | በሻሌ | 3 - BESH-B03/SN/009 | 72,100.00 | 1 |
| 31 | Gebisa Tekle Edosa | M | 596813 | ለሚኩራ | በሻሌ | 6 - BESH-B06/SN/009 | 78,927.21 | 1 |
| | seada Ahmed Seid | F | 379250 | ለሚኩራ | በሻሌ | 6 - BESH-B06/SN/009 | 78,100.00 | 2 |
| | Habtamu Mekonnen Balderas | M | 290123 | ለሚኩራ | በሻሌ | 6 - BESH-B06/SN/009 | 70,000.00 | 3 |
| 32 | Stephanos Assefa Abadoyo | M | 619547 | ለሚኩራ | በሻሌ | 1 - BESH/B-01/SN/010 | 76,375.50 | 1 |
| | Berhanu Yegezu Beyene | M | 138098 | ለሚኩራ | በሻሌ | 1 - BESH/B-01/SN/010 | 70,655.65 | 2 |
| 33 | Asmarech Arega Kassa | F | 980141 | ለሚኩራ | በሻሌ | 9 - BESH-B09/SN/201 | 70,000.00 | 1 |
| 34 | Feysel Abas Serur | M | 176767 | ለሚኩራ | በሻሌ | 21 - BESH-B21/SN/107 | 70,059.00 | 1 |
| 35 | Helen Hailselassie Yishal | F | 167046 | ለሚኩራ | በሻሌ | 7 - BESH-B07/SN/109 | 70,550.00 | 1 |
| 36 | Smegnew ላመስግን Gashu | M | 693982 | ለሚኩራ | በሻሌ | 8 - BESH-B08/SN/108 | 169,121.00 | 1 |
| 37 | Mesfin Alemu Tekamo | M | 292103 | ለሚኩራ | በሻሌ | 12 - BESH-B12/SN/106 | 76,000.50 | 1 |
| 38 | Daniel Anbaye Worku | M | 504659 | ለሚኩራ | በሻሌ | 24 - BESH-B24/SN/104 | 79,500.00 | 1 |
| | NETSANET MILLION ZELEKE | F | 492994 | ለሚኩራ | በሻሌ | 24 - BESH-B24/SN/104 | 70,528.00 | 2 |
| | Helen Hailselassie Yishal | F | 483315 | ለሚኩራ | በሻሌ | 24 - BESH-B24/SN/104 | 69,121.00 | 3 |
| 39 | Abrham Sisay Guangul | M | 467633 | ለሚኩራ | በሻሌ | 49 - BESH-B49/SN/002 | 71,656.00 | 1 |
| 40 | Rehana Zeyne Muzeyin | F | 525549 | ለሚኩራ | በሻሌ | 1 - BESH/B-01/SN/004 | 75,777.00 | 1 |
| 41 | Asnika Nigate Guangul | F | 146587 | ለሚኩራ | በሻሌ | 8 - BESH-B08/SN/206 | 68,550.00 | 1 |
| 42 | Fikerte Adelle Enedalewu | F | 272152 | ለሚኩራ | በሻሌ | 38 - BESH-B38/SN/001 | 70,150.00 | 1 |
| | Habtamu Mekonnen Balderas | M | 490628 | ለሚኩራ | በሻሌ | 38 - BESH-B38/SN/001 | 70,010.00 | 2 |
| 43 | ዋለልኝ admasu tegngne | M | 350425 | ለሚኩራ | በሻሌ | 34 - BESH-B-34/SN/009 | 69,501.00 | 1 |
| 44 | Kenzu Abas Surur | M | 875573 | ለሚኩራ | በሻሌ | 20 - BESH-B20/SN/107 | 70,059.50 | 1 |
| 45 | Smegnew Lamesgen Gashu | M | 126367 | ለሚኩራ | በሻሌ | 16 - BESH/B-16/SN/010 | 69,121.00 | 1 |
| 46 | Mesfin Behayilu Habtemaryam | M | 900640 | ለሚኩራ | በሻሌ | 10 - BESH-B10/SN/207 | 69,111.00 | 1 |
| 47 | ስመኝው ላመስግን ጋሹ | M | 347728 | ለሚኩራ | በሻሌ | 9 - BESH-B09/SN/109 | 69,121.00 | 1 |
| 48 | Alemayehu Zeberga Tereda | M | 668022 | ለሚኩራ | በሻሌ | 11 - BESH-B11/SN/109 | 71,500.00 | 1 |
| 49 | Yihunbelay Teshome Sime | M | 728035 | ለሚኩራ | በሻሌ | 12 - BESH-B12/SN/108 | 75,025.00 | 1 |
| 50 | fitsum tilahun donka | M | 590378 | ለሚኩራ | በሻሌ | 11 - BESH-B11/SN/105 | 79,000.00 | 1 |
| 51 | Gebisa Tekle Edosa | M | 247217 | ለሚኩራ | በሻሌ | 4 - BESH/B-04/SN/009 | 78,927.00 | 1 |
| | Meron Getachew Arega | F | 252317 | ለሚኩራ | በሻሌ | 4 - BESH/B-04/SN/009 | 74,100.00 | 2 |
| 52 | ምህረት ወርቁ መገሻ | M | 969404 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 4 - BA2/B-04/SN/04 | 70,000.00 | 1 |
| | Abel Demisse Nigatu | M | 812828 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 4 - BA2/B-04/SN/04 | 68,856.00 | 2 |
| 53 | SHEGAW MISEGAN ZEMENE | M | 720542 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 6 - BA2/B-06/SN/09 | 69,112.00 | 1 |
| 54 | ተስፋዬ ደጀኔ ጥሩነህ | M | 751665 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 9 - BA2/B-09/SN/03 | 71,370.00 | 1 |
| 55 | ምህረት ወርቁ መገሻ | M | 782459 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 12 - BA2/B-12/SN/08 | 75,565.00 | 1 |
| | hilina Aklilu Darge | F | 562245 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 12 - BA2/B-12/SN/08 | 69,200.00 | 2 |
| 56 | Teklehaimanot Belete Addis | M | 172273 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 14 - BA2/B-14/SN/03 | 68,610.00 | 1 |
| 57 | Tesfaye Dejene Tiruneh | M | 795827 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 16 - BA2/B-16/SN/02 | 69,950.00 | 1 |
| 58 | በቀለ ባህሩ ይርዳ | M | 513055 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 16 - BA2/B-16/SN/05 | 68,600.00 | 1 |
| 59 | Bekele Bahiru Yirda | M | 435051 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 16 - BA2/B-16/SN/06 | 68,600.00 | 1 |
| 60 | Ahmed Muhammed Tuhar | M | 842602 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 16 - BA2/B-16/SN/09 | 70,220.00 | 1 |
| | Bekele Bahiru Yirda | M | 814741 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 16 - BA2/B-16/SN/09 | 68,650.00 | 2 |
| 61 | Tesfaye Dejene Tiruneh | M | 184248 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 18 - BA2/B-18/SN/03 | 74,550.00 | 1 |
| 62 | መኮንን ሽፈራው ወርቄ | M | 555393 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 18 - BA2/B-18/SN/06 | 72,250.00 | 1 |
| 63 | LIDIYA MELESE HAILE | F | 691796 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 21 - BA2/B-21/SN/03 | 73,975.00 | 1 |
| | ደረጄ አየለ አይችሉህም | M | 410867 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 21 - BA2/B-21/SN/03 | 73,620.00 | 2 |
| | ምህረት ወርቁ መገሻ | M | 928971 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 21 - BA2/B-21/SN/03 | 73,000.92 | 3 |
| 64 | አባየሁ ወርቄ ከበደ | M | 262299 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 21 - BA2/B-21/SN/10 | 82,555.00 | 1 |
| | Haymanot Mulukal Kasie | F | 707309 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 21 - BA2/B-21/SN/10 | 78,656.00 | 2 |
| | SAMUEL ASMAMAW MULUALEM | M | 766843 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 21 - BA2/B-21/SN/10 | 76,100.00 | 3 |
| 65 | ጋሻው ደምሴ ንጋቱ | M | 665052 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 22 - BA2/B-22/SN/03 | 76,858.00 | 1 |
| | YONAS ASMAMAW MULUALEM | M | 966588 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 22 - BA2/B-22/SN/03 | 73,999.00 | 2 |
| | shefraw bzbhe sisye | M | 319117 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 22 - BA2/B-22/SN/03 | 72,100.00 | 3 |
| 66 | አዳነች ተረፈ ደምሴ | F | 469893 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 22 - BA2/B-22/SN/10 | 82,200.00 | 1 |
| | ምህረት ወርቁ መገሻ | M | 739574 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 22 - BA2/B-22/SN/10 | 76,100.00 | 2 |
| | LIDIYA MELESE HAILE | F | 743929 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 22 - BA2/B-22/SN/10 | 75,999.00 | 3 |
| 67 | ምህረት ወርቁ መገሻ | M | 899836 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 27 - BA2/B-27/SN/02 | 72,100.00 | 1 |
| 68 | ምህረት ወርቁ መገሻ | M | 205575 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 27 - BA2/B-27/SN/03 | 70,000.00 | 1 |
| 69 | NAHUSENAY ASHENAFI ASNAKE | M | 955395 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 27 - BA2/B-27/SN/10 | 81,119.00 | 1 |

# ማስታወቂያ



| ተ/ቁ | የተጫራች ሙሉ ስም | ጾታ | የደረሰኝ ቁጥር | ክፍለ ከተማ | ሳይት | ብሎክ - የቤት ቁጥር | ተጫራቹ ያስገባው ዋጋ | ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 70 | ምህረት ወርቁ መገሻ | M | 558922 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 28 - BA2/B-28/SN/03 | 73,460.00 | 1 |
| | Haymanot Desalegne Alemu | F | 302337 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 28 - BA2/B-28/SN/03 | 73,030.00 | 2 |
| | Ahmed Muhammed Temam | M | 486239 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 28 - BA2/B-28/SN/03 | 71,260.00 | 3 |
| 71 | Muhamed Kasim Ahmed | M | 178573 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 28 - BA2/B-28/SN/09 | 81,560.00 | 1 |
| 72 | Tesfamaryam Yirga Nigatu | M | 554281 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 28 - BA2/B-28/SN/10 | 76,207.00 | 1 |
| | ምህረት ወርቁ መገሻ | M | 808343 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 28 - BA2/B-28/SN/10 | 74,850.00 | 2 |
| | Tiglu Nano Saibo | M | 641245 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 28 - BA2/B-28/SN/10 | 69,100.00 | 3 |
| 73 | Getachew Assefa Abate | M | 454408 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 31 - BA2/B-31/SN/03 | 87,100.00 | 1 |
| | ምህረት ወርቁ መገሻ | M | 220974 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 31 - BA2/B-31/SN/03 | 81,170.00 | 2 |
| | Tesfaye Dejene Tiruneh | M | 998510 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 31 - BA2/B-31/SN/03 | 79,570.00 | 3 |
| 74 | YONAS ASMAMAW MULUALEM | M | 569861 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 44 - BA2/B-44/SN/02 | 81,999.00 | 1 |
| | NAHUSENAY ASHENAFI ASNAKE | M | 111242 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 44 - BA2/B-44/SN/02 | 81,119.00 | 2 |
| | Habtamu Adugna Dugasa | M | 267688 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 44 - BA2/B-44/SN/02 | 74,988.00 | 3 |
| 75 | አበባየሁ ወርቄ ከበደ | M | 652250 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 32 - BA2/B-32/SN/03 | 77,560.00 | 1 |
| | እንዳልካቸው ጥላሁን ሀብተወልድ | M | 224108 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 32 - BA2/B-32/SN/03 | 74,500.00 | 2 |
| 76 | መኮንን ሽፈራው ወርቄ | M | 879622 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 34 - BA2/B-34/SN/02 | 76,100.00 | 1 |
| | ጀሚላ አሊ ኢብራሂም | F | 771035 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 34 - BA2/B-34/SN/02 | 75,350.00 | 2 |
| | ATSEDE HAGOS GEBREHIWET | F | 310257 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 34 - BA2/B-34/SN/02 | 72,827.00 | 3 |
| 77 | DESTA Admasu Kibret | M | 523395 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 34 - BA2/B-34/SN/10 | 72,110.00 | 1 |
| | ምህረት ወርቁ መገሻ | M | 624953 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 34 - BA2/B-34/SN/10 | 72,100.00 | 2 |
| 78 | አባየሁ ወርቄ ከበደ | M | 912006 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 35 - BA2/B-35/SN/11 | 86,565.00 | 1 |
| | መኮንን ሽፈራው ወርቄ | M | 676721 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 35 - BA2/B-35/SN/11 | 80,150.00 | 2 |
| | ሺፈራዉ ዘነበ ወንዳፈራዉ | M | 915363 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 35 - BA2/B-35/SN/11 | 80,000.00 | 3 |
| 79 | Tesfaye Dejene Tiruneh | M | 942650 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 37 - BA2/B-37/SN/01 | 81,700.00 | 1 |
| | ምህረት ወርቁ መገሻ | M | 397090 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 37 - BA2/B-37/SN/01 | 74,100.00 | 2 |
| | መኮንን ሽፈራው ወርቄ | M | 931873 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 37 - BA2/B-37/SN/01 | 70,150.00 | 3 |
| 80 | Tesfaye Dejene Tiruneh | M | 420708 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 37 - BA2/B-37/SN/02 | 75,600.00 | 1 |
| 81 | Tesfaye Dejene Tiruneh | M | 620623 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 37 - BA2/B-37/SN/10 | 71,700.00 | 1 |
| 82 | Tesfaye Dejene Tiruneh | M | 597905 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 37 - BA2/B-37/SN/11 | 78,900.00 | 1 |
| 83 | Tesfaye Dejene Tiruneh | M | 158485 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 38 - BA2/B-38/SN/01 | 75,600.00 | 1 |
| 84 | ሺፈራዉ ዘነበ ወንዳፈራዉ | M | 231684 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 38 - BA2/B-38/SN/11 | 86,000.00 | 1 |
| | SHEGAW MISEGAN ZEMENE | M | 510969 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 38 - BA2/B-38/SN/11 | 69,112.00 | 2 |
| 85 | ዘመን አያና አምቢ | M | 442461 | ለሚኩራ | ቦሌ አያት2 | 40 - BA2/B-40/SN/02 | 68,550.00 | 1 |
ሥዩም ወልዴን እንደ አንድ ግለሰብና እንደ ሁለገብ ከያኒ በሚገባ ለማወቅ በወርሃ ጥር፣ 1985 ዓ.ም 'ኩርፊያ የሸፈነው ፈገግታ' የተሰኘው መጽሐፉን ማንበብ የግድ ይላል፡፡ ይሄ መጽሐፍ የአርቲስት ስዩም ወልዴ ግለ ታሪክ (ኦቶባዮግራፊ) ነው፡፡ አርቲስቱ ግለ ታሪኩን ለትውልድ ትቶ ያለፈው፣ የአንድን ከያኒ የፈጠራ ሥራና ህይወት ከሀገር ታሪክ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እንደሚተሳሰር በመገንዘቡ ይመስላል፡፡ ይሄን የአርቲስቱ ግለ ታሪክ መጽሐፍ ስለ ሥዩም ወልዴ ከያኒነት፣ ሁለገብ ሙያተኛነትና ህይወቱ ምን ይመስል እንደነበር ለመረዳት እጅግ ወሳኝ ሰነድ ነው፡፡ ይሄን ጽሑፍ በምናዘጋጅበትም ጊዜ ይሄንን መጽሐፍ በዋና ምንጭነት ተጠቅመነዋል፡፡

ሥዩም ወልዴ ሰዓሊ ነው፡፡ ከኢትዮጵያ ዘመናዊ ሰዓሊያን መካከልም አንዱ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የሥነ ጥበብ ታሪክ ውስጥ እንደ ሁለተኛ ትውልድ ከሚታዩት የተከበሩት የዓለም ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ፣ ገጣሚና ሰዓሊ ገብረ ክርስቶስ ደስታ እና ከሰዓሊ እስክንድር ቦጎስያን ጋር የአንድ ዘመን ተጋሪ ከያኒ ነው፡፡

ስዕል የመሳል ትልቅ መሻትና ተሰጥኦ የነበረው ብላቴናው ሥዩም፤ ይሄንን መሻቱን በዘመናዊ ዕውቀት ለማስደገፍ ከሀገር ውስጥ ጨምሮ እስከ ሩሲያ (የዚያን ጊዜ ሶቪየት ሕብረት ትባል ነበር) ሞስኮ ድረስ ሄዶ ተምሯል፡፡ ከሞስኮ ከተመለሰም በኋላ ሥነ ጥበብን አስተምሯል፡፡

አርቲስት ስዩም የትምህርት ዕድል አግኝቶ ሞስኮ ከመሄዱ በፊት አዲስ አበባ ውስጥ የራሱን የሥዕል ዓውደ ርዕይ




ፎቶ ከገፀ ድር

ከያኒ ሥዩም ወልዴ ከሚታወስባቸው ስራዎች አንዱ

ማሳየት የቻለ አርቲስትም ነው፡፡ ስዩም በሀገር ውስጥ በግልና ከሌሎች ሰዓሊያን ጋር በመሆን ተደጋጋሚ የሥዕል ዓውደ ርዕዮችን ለጥበብ አፍቃሪያን አቅርቧል። ካቀረባቸው ኤግዚቢሽኖች መካከል በሐምሌ 1955 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሆቴል በግሉ ያቀረበው የሥዕል አውደ ርዕይ ይገኝበታል፡፡ ይሄ አውደ ርዕይ ለሥዩም የመጀመሪያው አውደ ርዕዩ ነው፡፡ እሱም የመጀመሪያው በመሆኑ በከያኒነት ሕይወቱ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው አውደ ርዕይ ነው፡፡ አውደ ርዕዩን መርቀው የከፈቱት በጊዜው የትምህርት ሚኒስቴር ረዳት ሚኒስትር የነበሩት ዶ/ር መንገሻ ገብረሕይወት ነበሩ፡፡ ስለዚህ ኤግዚቢሽን አርቲስት ሥዩም 'ኩርፊያ የሸፈነው ፈገግታ' በተሰኘው መጽሐፉ በገጽ 89 እንዲህ ሲል አስፍሯል፤ "በሐምሌ ወር አጋማሽ ኤግዚቢሽኑ ተከፈተ፡፡ በዱብ ዕዳ ሠዓሊ ተባልኩና ስሜ በየጋዜጣው፣ በየሬድዮውና በቴሌቪዥን ተደጋግሞ ተጠራ፡፡ ካዘጋጀኋቸውም አርባ ሥምንት ሥዕሎች መካከል ወደ ሃያ ስድስቱ ተሸጡ፡፡ ይሄ ለእኔ ትልቅ ስኬት ነበር፡፡"

ከዚህ አንጻር ስዩም ገና ከመነሻው ነው በሥዕል ጥበብ ዕውቅናን ያተረፈው። ከዚህ የሥዕል ዓውደ ርዕይ በኋላ በግሉ ሌሎች የሥዕል አውደ ርዕዮችን አሳይቷል። በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ከሌሎች ሰዓሊያን ጋር በመሆን በ1969 ዓ.ም እና በ1970 ዓ.ም አሳይቷል። ሥዩም ወልዴ በሀገር ውስጥ ብቻም ሳይሆን በውጭ ሀገራትም የሥዕል ዓውደ ርዕዮችን ማሳየት የቻለ ሰዓሊ ነው፡፡ ለአብነትም በሩሲያ ሞስኮ ተማሪ እያለ በ'ሞስኮ ስቴት ዩኒቨርሲቲ' በግሉ በ1966 ዓ.ም እና በ'ሞስኮ ፍሬንድሽፕ ሃውስ' በ1967 ዓ.ም የሥዕል ሥራዎቹን አሳይቷል፡፡

የዚህ አይነቱ የላቀ ተሰጥኦ የነበረው አርቲስት ሥዩም የሙሉ ጊዜ ሰዓሊ ግን አልነበረም፡፡ ከዚያ ይልቅ ከሌሎች ሙያዎች ጋር በጎን የሚያስቀጥለው ሙያ ነበር፡፡ የሚያስገርመው ነገር አርቲስት ሥዩም ምንም እንኳን ከፍተኛ የሥነ ጥበብ ተሰጥዖና ዝንባሌ ቢኖረውም ከሰዓሊነት በጊዜ ነው የተገለለው፡፡ ከዚያ በኋላ ሥነ ጥበባዊ ሥራዎችን ወደ መሄስ እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ሥነ ጥበብን ወደ ማስተማር ፊቱን አዙሯል፡፡

ሥዩም ወልዴ ሃያሲም ነው፡፡ ከኢትዮጵያ ፈርቀዳጅ ሃያሲያን መካከል እንደ አንዱ የሚታይ ሃያሲም ጭምር፡፡ ሥነ ጥበብን በዕውቀት በመሄስና ዘመናዊ የሃያሲነት ስልት ለኢትዮጵያ ካስተዋወቁ ታላላቅ ሰዎች መካከልም ይመደባል፡፡ ሥነ ጥበብን በዕውቀት በመሄስ ከገጣሚ ሰሎሞን ዴሬሳ ቀጥሎ የሚጠቀሰው ይኸው ሁለገቡ አርቲስት ስዩም ወልዴ ነው፡፡

ደራሲና ጋዜጠኛ ዲበኩሉ ጌታነህ ስለ አርቲስት ሥዩም ወልዴ ለዝግጅት ክፍላችን ባጋራን መረጃ፣ ስዩም ወልዴ ራምሴ ሁለገብ አርቲስት መሆኑን አጫውቶናል፡፡ በተለያዩ የጥበብ ዘርፎች ላይ ብቃቱን በሚገባ ማስመስከሩን በመግለጽ በተለይም ዘመናዊ የሂስ መንገድ አስቀድመው ከተለሙልን ቀደምት ከያኒያን መካከል አንዱ እንደሆነም ተናግሯል፡፡

ብዙዎች ስዩምን የሚያስታውሱት በሰዓሊነቱ ነው የሚለው ደራሲና ጋዜጠኛ ዲበኩሉ፣ ከዚህ ባሻገርም ስዩምን "ሥነ ጥበብን በማስተማርና ሥነ ጥበብን ለማሳደግ የሚያስችሉ የጥበብ ማህበራትን በመመስረት ሥነ ጥበብን ተቋማዊ ገፅታ እንዲይዝ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ከሁሉም በላይ ሥዩምን ስናስታውስ መዘንጋት የሌለበት አንድ ጉዳይ የሥዩም ወልዴ የሃያሲነት ብቃትን ነው፡፡ ሥዩም ወልዴ በየካቲት መጽሔትና በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ላይ ያደረጋቸው ሥነ ጥበባዊ ሂሶች ዛሬም ድረስ በተመራማሪዎች እንደማጣቀሻ የሚወሰዱ ናቸው፡፡ ሥነ ጥበብን መሄስ ትልቅ ንባብ፣ አስተውሎትና የመጻፍ ችሎታ እንደሚጠይቅ ለመረዳት የሥዩም ሂሳዊ መጣጥፎችን ማንበብ በቂ ነው። ከዚህ አንጻር ሥዩም በሃያሲነቱ፣ በሰዓሊነቱና በመምህርነቱ አንቱታ የሚገባው ታላቅ አርቲስት ነው" በማለት አጫውቶናል፡፡

ስዩም ወልዴ ጋዜጠኛም ነው፡፡ ወደ ጋዜጠኝነት የገባው ባጋጣሚ ቢሆንም የኋላ ኋላ ግን በጊዜው በሙያው እጅግ ከታወቁ ጋዜጠኞች መካከል አንዱ ለመሆን በቅቷል፡፡ ሥዩም በ1958 ዓ.ም ነበር 'ብሥራተ ወንጌል' ይባል በነበረው ሬዲዮ ጣቢያ በባህልና በልዩ ልዩ ፕሮግራሞች አዘጋጅነት የጋዜጠኝነት ሙያ መስራት የጀመረው፡፡

በሙያው በጊዜው ታላላቅ የመንግስት ባለሥልጣናትን ቃለ መጠይቅ ከማድረግ አንስቶ፤ የሕዝቡን ጥያቄ የሚመልሱ በርካታ የሬድዮ ፕሮግራሞችን ሰርቷል። በግለታሪክ መጽሐፉ በተደጋጋሚ እንዳሰፈረው በጊዜው የጋዜጠኝነት ሙያ ታላቅ አክብሮት እና ዕውቅና አስገኝቶለት እንደነበር ጽፏል፡፡

ከሙያው ጋር በተገናኘ በተደጋጋሚ ይገጥመው የነበረ ተደጋጋሚ ክስተት እዚህጋ እንጥቀሰው፡፡ በሬድዮ ድምጹንና የፕሮግራሙን ብስለት ያደመጡ ባለስልጣናት እንዲሁም ታዋቂ ሰዎች በአካል ለቃለ መጠይቅ ቀጥረውት ሲሄድ ተደጋጋሚ ገጠመኝ ገጥሞታል፡፡ በሬድዮ ድምጹንና ፕሮግራሙን የሚሰሙ ሰዎች ወጣቱን ስዩም በእድሜ እና በትምህርት የገፉ ትልቅ ሰው አድርገው ነበር የሚያስቡት፡፡ ቃለ መጠይቅ ሊያደርግ ሄዶ በተደጋጋሚ "ሥዩም ወልዴ እርሶ ሊሆኑ አይችሉም" ተብሎ መታወቂያ ተጠይቆ ያውቃል፡፡ ይሄ ሁሉ የሚያሳየው ሥዩም ወልዴ በጊዜው ዝነኛና ተወዳጅ ጋዜጠኛ እንደነበረ ነው፡፡ ሩሲያ ሞስኮ የትምህርት ዕድል አግኝቶ እስከሄደበት ጊዜ ድረስ በጋዜጠኝነት ሙያ አንቱታን አትርፎለታል፡፡ ከዚህ አንጻር ሥዩም ወልዴ ኹነኛ ጋዜጠኛም ነው፡፡

ሥዩም ወልዴ ሞስኮ ለሰባት ዓመታት ትምህርቱን አጠናቅቆ ወደ ሀገሩ ከተመለሰም በኋላ ስነ ጥበብን አስተምሯል፡፡ ከአርቲስት ሥዩም የቀድሞ ተማሪዎች መካከል በአሁኑ ሰዓት በሙያው አንቱታን ያተረፈው ሰዓሊና ቀራጺ በቀለ መኮንን (ተባባሪ ፕ/ር) አንዱ ነው፡፡ በአንድ ቃለ መጠይቁ ሰዓሊና ቀራጺ በቀለ መኮንን ስለ ቀድሞ መምህሩ እንዲህ ብሏል፤ "ስዩም ወልዴ ብቁ መምህር ነበር። ወደ መማሪያ ክፍል ሲገባ ተዘጋጅቶ በፍጹም ራስ መተማመን ያስተምር ነበር። መምህር ስዩም ሲያስተምረን ብዙ ጽሑፍ ያፅፈን ነበር። የፈላስፋዎችን ታሪክ እጃችንን እስኪያመን ድረስ ያፅፈን ነበር። አሁን ላይ ሳስበው ሰው የፃፈውን አይረሳምና እንድናስታውስ አድርጎናል። ስዩም በስራ ላይ ደራርቦ እየሰጠን ያጠነክረን ነበር" በማለት ምስክርነቱን ሰጥቷል፡፡

ከዚህ አንጻር ስዩም ወልዴ ከቀዳሚዎቹ ሰዓሊያን፣ ሃያሲያን፣ የሥነ ጥበብ ተመራማሪዎችና መምህራን መካከል አንዱ ያደርገዋል፡፡ አርቲስት ስዩም ከዚህ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ሠዓሊያንና በኢትዮጵያ ደራሲያን አንድነት ማህበራት በዋና ፀሐፊነትም ለዓመታት አገልግሏል።

## ሥዩም ወልዴ ራምሴ ማነው?

ሥዩም ወልዴ የፒያሳ ልጅ ነው። ለዚያውም አዲስ አበባ መሃል አራዳ ሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ጎን ነው ተወልዶ ያደገው፡፡ ሥዩም በ1935 ዓ.ም ነበር ይህን ዓለም የተቀላቀለው፡፡ ሥዩም መሃል አዲስ አበባ ተወልዶ ቢያድግም በዚያ ጊዜ ባህል መሰረት ከቤቱ አቅራቢያ ከሚገኘው የቄስ ትምህርት ቤት ሄዶ ተምሯል። የየኔታ አለንጋንም በደንብ ቀምሷል፡፡ እንዲያውም ስዩም በግለ ታሪኩ ይህንን አለንጋ እንደ መልካም ትዝታ ሳይሆን፤ እንደ መጥፎ ትውስታ ነው የጻፈው። በኋለኛው የዕድሜ ዕርከን ላይ የየኔታ አለንጋ ተጽዕኖ አድርጎበት ትምህርት ቤት አልሄድም ብሎ እስከማመጽና ትምህርት እስከመጥላት እንደደረሰም ጽፏል፡፡ የራሱን የልጅነት ልምድን መነሻ በማድረግ ልጆችን በዕውቀት ለመቅረጽ ከአለንጋ ይልቅ ጥበብ የታከለበት ብልሃት እንደሚያስፈልግም በግለ ታሪኩ ውስጥ አስፍሯል፡፡

ሌላው ስለ ስዩም ወልዴ የሚያስደንቀው ነገር አስተዳደጉ ነው። አስተዳደጉ ከስራ ጋር ጥብቅ ትስስር አለው፡፡ ስዩም ገና ከለጋ ልጅነቱ ጀምሮ ነው ከስራ ጋር የተዋወቀው፡፡ ከቤቱ ጎን ከሚገኘው የሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ውስጥ መጋረጃን የመክፈት የመዝጋት ሥራ እየተከፈለው ሰርቷል፡፡ መርካቶ ውስጥ እቃ ዘርግቶ ሸጧል፡፡ ከልብስ ሰፊነት አንስቶ የሰርግና የሀገር ባህል ልብሶችን ዲዛይን የማድረግ ስራ ሰርቷል።

አርቲስት ሥዩም የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ካጠናቀቀ በኃላ በሞስኮ ስቴት ዩኒቨርሲቲ የሥነ ጥበብ ታሪክ፣ የጥበብ ንድፈ ሃሳብና የሃያሲነት ትምህርቶችን በመማር በማስተርስ ዲግሪ ተመርቋል፡፡

ስዩም የአርበኛ ልጅ ነው፡፡ አባቱ አቶ ወልዴ ከ1928 እስከ 1933 ዓ.ም በቆየው የጣሊያን ወረራ ጊዜ ትግራይ ምድር ድረስ ተጉዘው ሀገራቸውን ከጠላት ወረራ ለመታደግ ዘምተዋል፡፡ በማይጨው ጦርነትም ተሳትፈዋል፡፡

አርቲስት ሥዩም ከላይ ከተጠቀሱት የጥበብ ዘርፎችና ሙያዎች በተጨማሪ፣ በኢትዮጵያ "የብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት" ይባል በነበረው ተቋም ውስጥ፣ በባሕል ጉዳዮች ዋና ኤክስፐርትነት ሆኖ ሀገሩን አገልግለዋል። በአዲስ አበባ ሥነ ጥበብ ትምህርት ቤት የሥነ ጥበብ ታሪክን አስተምሯል። ተወርዋሪው ኮከብ ሥዩም ወልዴ ራምሴ ከውልደቱ አንስቶ ሕይወቱ እስካለፈበት 1990 ዓ.ም ድረስ በተለያዩ መስኮች ሀገሩን አገልግሏል፡፡ ለትውልድ የሚጠቅም ሥራ በመስራቱ፤ ይኸው እኛም ከህልፈተ ሕይወቱ ሦስት አስርት ዓመታት በኋላ ታላቁ አርቲስት ሥዩም ወልዴ ራምሴን በዚህ መልኩ አስታወስነው፡፡

# ልጆች፤ የማንበብ ልምዳችሁ እንዴት ያለ ነው?

**በለይላ መሀመድ**

ልጆች ታነባላችሁ? ንባብ ስንል ከትምህርት ውጤት ማምጣት ጋር ብቻ የተያያዘ አይደለም፡፡ የነገ ሀገር ተረካቢ የሆናችሁ ልጆች ንባብ አስተዋይ፣ አሰላሳይ፣ ተመራማሪና የእውቀት አድማሳችሁ የሰፋ እንድትሆኑ ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም ከወዲሁ የንባብ ባህላችሁን ማሳደግ ይኖርባችኋል። እኛም በዛሬው ዝግጅታችን የንባብ ባህል ያላቸው ልጆች ልምድና ተሞክሯቸው ምን እንደሚመስል እንዲሁም የንባብ ጠቀሜታና እንዴት ማዳበር እንደሚችሉ የባለሙያ ምክር ይዘንላችሁ ቀርበናል፡፡



ፎቶ በገነት ወንድሙ
ልጆች የንባብ ባህላቸውን ከሚያዳብሩበት መንገዶች መካከል ቤተ መጽሐፍት አንዱ ነው

ሙሳ ሀሰን እባላለሁ፡፡ ጥናቴን ካጠናቀቅኩ በኋላ የተረት እና የስነ ምግባር መጽሐፍትን አነባለሁ፡፡ ከትምህርት ውጪ ያሉ መጽሐፍትን የማንበብ ልምድ ማዳበሬ የምማረውን ትምህርት አቀላጥፌ ለማንበብ ጠቅሞኛል፡፡ የማነበው በትምህርት ቤታችን በሚገኘው ቤተ መጽሐፍት በመሄድ እና እቤቴ ውስጥ በመሆን ነው፡፡ የማንበብ ልምድ ላዳብር የቻልኩት በመምህራንና ወላጆቼ እገዛ ነው፡፡

ስሜ ይዲዲያ አበባው ይባላል፡፡ በየቀኑ የምማረውን ትምህርት አጠናለሁ። የምማረውን ትምህርት ካጠናሁና የቤት ስራየን ሰርቼ ከጨረስኩ በኋላ ሌሎች ከትምህርት ውጪ የሆኑ መጽሐፍትን የማንበብ ልምድ አለኝ፡፡ በአብዛኛው የማነበው የተረት፣ የግጥም እና ታሪክ ነክ መጽሐፍትን ነው፡፡ የማነብበት ጊዜ በትምህርት ሰዓት ከሆነ በእረፍት ጊዜ ነው፡፡ እቤቴ ሲሆን ደግሞ ከላይብረሪ በመታወቂያየ መጽሐፍ በመዋስ እሁድ ቀን የምጫወትበትን ሰዓት በመቀነስ ነው። ንባብ የተለማመድኩት በእናቴ እና በመምህሬ ጥረት ከኬጂ ጀምሮ ነው፡፡ በማንበቤ በትምህርቴ ውጤታማ መሆን ችያለሁ፡፡ የማንበብ ልምድ የሌላችሁ ልጆች ጨዋታ ቀንሳችሁ ለንባብ ጊዜ መስጠት አለባችሁ፡፡

መሪም አረብ እባላለሁ፡፡ ተጨማሪ መጽሐፍትን የማነበው በሳምንት ሶስት ቀናትን መድቤ ነው፡፡ ይኸውም ከምሳ ሰዓት በኋላ እና የእረፍት ጊዜየን በመጠቀም ነው። የማነበውም የተረትና የታሪክ መጽሐፍት ናቸው፡፡ ከታሪክ መጽሐፍት የሰዎችን ታሪክ እንዳውቅ አድርጎኛል፡፡ ማንበብ በራስ የመተማመን ችሎታየን አዳብሮልኛል። በአሁኑ ወቅት የ4ኛ ክፍል ተማሪ ስሆን የማንበብ ክህሎት ያዳበርኩት ከ2ኛ ክፍል ጀምሮ ነው፡፡

ይስሀቅ አብርሀም እባላለሁ፡፡ ማንበብ የጀመርኩት ከ8 ዓመቴ ጀምሮ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ የጀመረው የማንበብ ፍላጎት አሁን ብዙ ከመጫወት ማንበብ ያስደስተኛል፡፡ ትንሽ ከተጫወትኩ በኋላ ንባብ ላይ አተኩራለሁ። ይህም የማንበብ ክህሎቴን አዳብሮልኛል፡፡ ማንበብ የምወደው የተረት መጽሐፍትን ነው።

ኢልሀም ረሻድ እባላለሁ፡፡ ማንበብ ለትልቅ ደረጃ እንደሚያደርስ ስለማምን ማንበብ እወዳለሁ፡፡ ብዙ ጊዜ የታሪክ እና የስነ ምግባር መጽሐፍትን ከቤተ መጽሐፍት እየተዋስኩ ነው የማነበው፡፡ እናትና አባቴ እንዲሁም መምህሬ እንዳነብ ያበረታቱኛል። ማንበብ የማይችሉ ልጆች የሚማሩትንና በፈተና ወቅትም መምህራኖቻቸው እንዲረዷቸው ሲያስቸግሩ አያለሁ፡፡ እኔ ግን በራሴ አንብቤ የመረዳት ችሎታየን ስላዳበርኩ የምማረውን እረዳለሁ፤ በፈተናም አልቸገርም፡፡ ስለዚህ ሁላችሁም የማንበብ ክህሎታችሁን ማዳበር አለባችሁ።

ህያውቃል ተስፋዬ እባላለሁ፡፡ የልጆች ሁለንተናዊ እድገት ባለሙያ ነኝ፡፡ ልጆች ንባብ በጽሁፍ የቀረበን መልእክት፣ ሀሳብ የምናገኝበትና የምንረዳበት መንገድ ነው፡፡ ልጆች ንባብ ብዙ ጥቅሞች አሉት፡፡ ጥቂቶቹን ልንገራችሁ፡፡ ንባብ የማስታወስ ችሎታችሁን ያዳብርላችኋል። አካባቢያችሁንና ህይወትን የመረዳት አቅማችሁን ያሳድግላችኋል፡፡ ከእናንተ በፊት ይኖሩ የነበሩ ሰዎች በምን ሁኔታና እንዴት ይኖሩ እንደነበር ታሪክ ይነግራችኋል፡፡ ምክንያታዊ አስተሳሰብ እንዲኖራችሁም ያደርጋችኋል፡፡ እናንተ ከምታውቁት በላይ እውቀት ሰፊ መሆኑን በተለይም የሰው ልጅ አሁን የደረሰበት ስልጣኔ፣ እውቀትና ደረጃ ለመድረስ የሄደባቸውን መንገዶች ለማወቅ ይረዳችኋል፡፡

የቃላት እውቀታችሁን ያሳድግላችኋል። ስታነቡ ብዙ ቃላትን፣ አባባሎችን እና የሰዋሰው ህጎችን እንድታውቁ ስለሚያደርግ በራስ የመተማመን ብቃታችሁን ያጎለብ ትላችኋል። በመደበኛ ትምህርታችሁ ላይም ውጤታማ እንድትሆኑ ያደርጋችኋል። ስታነቡ የምታገኟቸው እውቀቶች ከትምህርቶቻችሁ ጋር ታዛምዷ ቸዋላችሁ። የማንበብ ልምዳችሁ እየዳበረ ሲሄድ የምትማሩትን ለመረዳት አትቸገሩም። ሌላው ችሎታችሁንና ዝንባሌያችሁን እንድትረዱም ያደርጋችኋል። የሚያስደስታችሁን እንድትለዩ ይመራችኋል፡፡

ልጆች እድሜያችሁን የሚመጥኑ፣ የንባብ አቅማችሁንና ደረጃችሁን እየለያችሁ ብታነቡ የማንበብ ባህላችሁ ይዳብራል። የንባብ ባህላችሁ እንዲዳብር ቀስ በቀስ ማለማመድ አለባችሁ፡፡ በቀን አንድ ገጽም ሆነ ግማሽ ገጽ በማንበብ ማዳበር ይኖርባችኋል፡፡ ዓለም ላይ ለውጥ ያመጡ ታላላቅ ሰዎች ያነባሉ፡፡ እሚያነብ ሰው መሪ ይሆናል፡፡ በህይወት የተሻለ እድል እንድታገኙ ያደርጋችኋል፡፡ ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ ለማንበብም ሞክሩ፡፡ እንደምታነቡት የታሪክ አይነት ድምጻችሁን እየቀያየራችሁ ብታነቡም የተሻለ ነው። በድራማ መልክ ለጓደኞቻችሁ ታሪኩን ለመንገርም ሞክሩ፡፡ ልጆች ንባብ የሚዳብር ክህሎት በመሆኑ የንባብ ክህሎታችሁን በማዳበር ለራሳችሁም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ህይወት ጠቃሚ መሆን ይጠበቅባችኋል፡፡

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ሆዷን ሞልታ የቀረውን በሾኋ ሰክታ**

መልስ፡- ለ. ጃርት

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ዞሮ ዞሮ እግሩን የማይታጠብ**

ሀ. ህፃን
ለ. ወንበር
ሐ. ዱላ

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ፡፡**

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# “ከሌሎች ተቋማት ጋር በቅንጅት በመሥራታችን ለመንገድ ሀብታችን ጠበቃና ባለቤት አግኝተናል”

**የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ኢንጂኒየር ሙህዲን ረሻድ**



ፎቶ ከመንገዶች ባለስልጣን
የውይይት መድረኩ ተሳታፊዎች



ፎቶ ከመንገዶች ባለስልጣን
ከባለድርሻ አካላት ጋር የስምምነት ፊርማ ሲካሄድ

**በላዋይሽ ቢተው**

የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፤ ሕዝብ የሚጠብቀውን አገልግሎት በብቃት መስጠት እንዲችሉ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት ውጤታማ ያደርጋቸዋል። ተቋማት በቅንጅት መስራታቸው የመንግስትን ሀብት ከብክነት በመታደግ የህዝብን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የልማት ሥራዎች አገልግሎት ለመስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

ዓመታዊ የመንገድ ዘርፍ ዕቅዶቹን ከሌሎች ባለድርሻ አካላት፣ ከሲቪክ ማህበራትና ተገልጋዮች ጋር በተቀናጀ መልኩ የሚተገብረው የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን የ2018 ዓ/ም የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የቅንጅታዊ ስራዎች አፈፃፀም የባለድርሻ አካላት ተወካዮች በተገኙበት ገምግሟል፡፡

የቅንጅት ስራዎች የተቋማትን የመፈፀም አቅም ለማሳደግ እንደሚያግዝ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ሙህዲን ረሻድ የውይይት መድረኩን በከፈቱበት ወቅት ተናግረዋል፡፡

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በመጀመሪያ ሩብ ዓመት 393 ነጥብ 1 ኪሎ ሜትር የመንገድ ግንባታ እና ጥገና ስራዎች ማከናወኑንና ይህም የሩብ ዓመት አፈፃፀም ስኬታማ እንደነበር በባለስልጣኑ ፕላን፣ በጀትና ስትራቴጂክ ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ አብነት ኤርገንዶ የቀረበው ሪፖርት ያሳያል፡፡

ከአዲስ ዓመት ጋር ተያይዞ የተከበሩ የአደባባይ በዓላት፣ የህዳሴ ግድብን ምረቃ ምክንያት በማድረግ የተከናወኑ የመንገድ ጥገናና ማስዋብ ሥራዎች እንዲሁም የ90 ቀን እቅድን መሠረት አድርገው የተከናወኑ ተግባራት ባለስልጣኑ ላስመዘገበው ውጤት አስተዋፅኦ ማድረጋቸውንም ነው አቶ አብነት የገለፁት፡፡

የሪፖርቱን መቅረብ ተከትሎ አስተያየታቸውን ከሰጡት መካከል የአዲስ አበባ አረጋውያን ማህበር ተወካይ የሆኑት አቶ ደረሰ መንግስቱ “ባለስልጣኑ በሩብ ዓመቱ ያስመዘገበው አፈፃፀም ተቀናጅቶ በመስራት ብዙ ማሳካት እንደሚቻል ማሳያ ነው” ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር ተወካይ ወይዘሮ ፎሊ ንጉሴ በበኩላቸው፤ በቅንጅት በመስራት የተመዘገበው ውጤት መልካም መሆኑን ገልፀው ባለስልጣኑ በስራ እድል ፈጠራ ወጣቶችን ተጠቃሚ ማድረጉንና በቀጣይም አጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባም ነው የተናገሩት፡፡

> **“ከደንብ ማስከበር ባለስልጣን ጋር በቅንጅት በመስራት በመንገድ ሀብቶች ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን እና ዝርፊያዎችን ለመቆጣጠር እየሰራን ነው”**

“መንገድ ለአንድ ከተማ የደም ስር ነው፤ መሬት ዋጋ እንዲኖረው መንገድ ያስፈልጋል” ያሉት ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማት አስተዳደር ቢሮ ተወካይ አቶ የኑስ አደም ናቸው፡፡ ባለስልጣኑ የመፈፀም አቅሙን ከፍ በማድረግ በትጋት ሊሰራ እንደሚገባም አሳስበዋል፡፡

ሌላኛው የመድረኩ ተሳታፊ አቶ እሸቱ ደሳለኝ የአዲስ አበባ አካል ጉዳተኞች ማህበር ተወካይ ናቸው፡፡ በኮሪደር ልማት መንገዶች ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ተደርገው በመገንባታቸው በመንገድ የሚደርስባቸው ጉዳት መቀነሱን እና ያለ ሰው ድጋፍ ለመንቀሳቀስ እንደቻሉ በመናገር የመንገዶች ግንባታን ሁሉን አቀፍ ለማድረግ በኮሪደር ልማት ላይ የተከናወነው ተግባር በሌሎች የመንገድ ስራዎች ላይ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

ከተሳታፊዎች ለቀረቡ አስተያየቶች ምላሽ የሰጡት የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ኢንጅነር ሙህዲን ረሻድ የቅንጅት ስራዎች የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመቅረፍ እና የህብረተሰቡን ፍላጎት መሰረት ያደረገ አገልግሎት ለመስጠት ያግዛሉ ሲሉ የቅንጅታዊ አሰራር ጠቀሜታን ተናግረዋል፡፡

“የመልካም አስተዳደር ችግር የተስተዋሉባቸውን የመንገድ ፕሮጀክቶች በጊዜ ለማጠናቀቅ ፕሮጀክቶችን ከኮንትራክተሮች በመረከብ በራስ ሀይል እየገነባን እንገኛለን” በማለት የመልካም አስተዳደር ጥያቄን ለመመለስ ባለስልጣኑ የወሰደውን እርምጃ የገለፁት ኢንጂነር ሙህዲን ከድሬኔጅ መስመር ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት ባለስልጣኑ የድሬኔጅ ማስተር ፕላን ጥናት እያካሄደ መሆኑንና ጥናቱ ሲጠናቀቅ ከድሬኔጅ መስመር ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ችግሮችን ሙሉ ለሙሉ ለመፍታት ያስችላልም ነው ያሉት፡፡

“ከሌሎች ተቋማት ጋር በቅንጅት መስራታችን ለመንገድ ሀብታችን ጠባቂ እና ባለቤት አግኝተናል” ያሉት የባለስልጣኑ መንገድ ሀብት አስተዳደር ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጅነር መሀመድ አወል ሰኢድ በበኩላቸው፤ የመንገድ መሰረተ ልማት ማስፋፋት ስራን ከሌሎች ተቋማት ጋር በቅንጅት መስራታችን ለመሰረተ ልማት ዝርጋታ የሚቆረጡ መንገዶችን በማስቀረት ለጥገና የሚወጣ ወጪን መቆጠብ መቻሉን አስታውቀዋል።

“ባለስልጣኑ ከደንብ ማስከበር ባለስልጣን ጋር በቅንጅት በመስራት በመንገድ ሀብቶች ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን እና ዝርፊያዎችን ለመቆጣጠር እየሰራን ነው ይህም በመንገድ መሰረተ ልማት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ አስተዋፆአው የላቀ ነው” ሲሉም ኢንጅነር መሀመድ አወል ሰኢድ ገልፀዋል፡፡

በመድረኩ ማጠናቀቂያ ላይ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ኢንጅነር ሙህዲን ረሻድ ከባለድርሻ አካላት ተወካዮች ጋር የስምምነት ሰነድ ተፈራርመዋል፡፡ ሰነዱ ቀጣይ ስራዎችን በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ሲሆን፤ የአዲስ አበባ ከተማ ውሃ እና ፍሳሽ ባለስልጣን፣ የግንባታ ፈቃድ እና ቁጥጥር ባለስልጣን፣ የአዲስ አበባ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ ኢትዮ ቴሌኮም ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ልማት ቢሮ እና በከተማ መስተዳድሩ የሚገኙ የሲቪክ ማህበራት የስምምነት ሰነዱን ከፈረሙት መካከል ተጠቃሽ ናቸው፡፡

**ከአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ**

# ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በሩብ ዓመቱ ምን ተገበረ?

- **በከተማ አስተዳደር ደረጃ በአምስት ክፍለ ከተሞች በግንባታ (ኮንስትራክሽን) እና ማዕድን ማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ አልሚዎችን መደገፍና ማበረታታት ተችሏል**

**በለይላ መሀመድ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በዋናነት ትኩረት አድርጎ የሚሠራባቸው ጉዳዮች የአካባቢ ብክለትን መከላከልና መቆጣጠር፣ የተስተካከለ የአየር ንብረት እንዲኖር ከማድረግ ጎን ለጎን ማዕድን ለሚያወጡ አካላት ፍቃድ መስጠት ተጠቃሽ ነው፡፡ ባለስልጣኑ እነዚህን የትኩረት መስኮች እና ተያያዥ ተግባራት ላይ በ2018 በጀት አንደኛ ሩብ ዓመት "ምን አቅዶ ምን አከናወነ?" የሚሉትን የመስሪያ ቤቱ ምክትል ስራ አስኪያጅ አቶ አሰግደው ኃይለጊዮርጊስ ማብራሪያ ሰጥተውናል፡፡

ምክትል ሥራ አስኪያጁ እንደገለጹት፤ ባለስልጣኑ በሩብ ዓመት ውስጥ ለማከናወን ከያዛቸው ተግባራት መካከል፡- የአካባቢ ጥበቃና ልማት ሥራ አካል የሆነው የአካባቢ ብክለት መከላከል ይጠቀሳል፡፡ የተለያዩ የብክለት አይነቶች ያሉ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ የድምጽ፣ የፍሳሽ፣ የፕላስቲክ እና የሌሎች የጽዳት አስተዳደር ብክለቶች ዋናዋናዎቹ ናቸው። ባለስልጣኑ ከተማዋን ከብክለት ለመከላከል እና ንፅህናዋን የተጠበቀ ለማድረግ የሚያስችለውን ሥራ የሚያከናውነው ብቻውን አይደለም። ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተለይም ከደንብ ማስከበር ባለስልጣን፣ ከደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ እና ሌሎች ተቋማት ጋር በቅንጅት በመሆን ነው፡፡ በ2018 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ላይ ሙዚቃ ቤትን ጨምሮ ሌሎች የድምጽ ብክለት በፈጸሙ አካላት ላይ በወረዳና በክፍለ ከተማ ደረጃ የመለየት ሥራ ተሠርቷል፡፡ በተለይም ችግሩ ከፍ ባለባቸው እንደ ቦሌ፣ ቂርቆስ፣ የካ፣ ለሚ ኩራና ልደታ ክፍለ ከተሞች ላይ ብክለት ያለባቸው አካላት ላይ ጠንካራ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ ችግሩን ማቃለል ተችሏል፡፡ ይህም በመዲናዋ የተካሄዱትን በርካታ ዓለም አቀፍ መድረኮች ጨምሮ ሌሎች ሁነቶች እና የዘውትር የነዋሪው እንቅስቃሴ የድምጽ ብክለት እንዳያጋጥማቸው አድርጓል፡፡

በ2017 በጀት ዓመት ደንብ ቁጥር 180/2017 የወንዝ ዳርቻ ልማትና ብክለት መከላከል ደንብ መውጣቱን ያስታወሱት የባለስልጣኑ ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ አሰግደው፤ የደንቡን ተግባራዊነት ለማረጋገጥ በሩብ ዓመቱ ትኩረት ተደርጎ መሠራቱን ተናግረዋል። በተለይም አምራቾች፣ አገልግሎት ሰጪዎችና ግለሰቦች ፍሳሻቸውን በከፍተኛ የመንግስትና የህዝብ ሃብት ወጪ ተደርጎባቸው ወደተሠሩ የልማት ሥራዎች እንዲሁም በለሙ ወንዝና ወንዝ ዳርቻዎች ላይ ሲለቁ የነበሩ አካላትን በመለየት ግንዛቤ ተፈጥሮላቸዋል፡፡ ከግንዛቤ መፍጠር ባለፈ፤ በተፈጠረላቸው ግንዛቤ መሰረት ከጥፋት ድርጊታቸው ያልታቀቡትን ወይም ችግራቸውን ያላስተካከሉትን ከደንብ ማስከበር ባለስልጣን ጋር በመሆን ተጠያቂ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ የፍሳሽ ማስወገጃ(ሴፍቲ ታንክ) የሌለው እንዲያዘጋጅ፤ ፍሳሹን ወደወንዝ የሚለቅ ደግሞ እንዲደፍንና እንዲያስተካክል ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ተሠርቷል፡፡

በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት በባለስልጣኑ የተከናወነው ሌላው ትልቁ ሥራ ከከተማዋ ልማት ጋር ተያይዞ በግንባታ(ኮንስትራክሽን) ማዕድን ልማት ላይ ለተሰማሩ አካላት ፍቃድ መስጠት እና ተከታታይነት ያለው ድጋፍ ማድረግ የሚጠቀስ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በከተማ አስተዳዳር ደረጃ በአምስት ክፍለ ከተሞች በግንባታ(ኮንስትራክሽን) ማዕድን ማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ አልሚዎችን መደገፍና ማበረታታት ተችሏል፡፡ በዚህም በከተማዋ ለሚሠራው ልማት ከፍተኛ መጠን ያለው ግብአት በማቅረብ ትልቅ ሚና ተወጥተዋል፡፡ ከእነዚህ አምራቾች ብቻ በሩብ ዓመቱ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊየን ሜትር ኪዩብ የግንባታ(ኮንስትራክሽን) ማዕድን ተመርተው በኮሪደር፣ በወንዝ ዳርቻ እና በሌሎች ሜጋ ፕሮጀክቶች ልማት ላይ እንዲውል ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡

ከማዕድን ማምረት በተጓዳኝ ማዕድን የወጣባቸውን ቦታዎች መልሶ ማልማት ስለሚገባ ማዕድን ለማውጣት ፍቃድ ያወጣው አካል መልሶ እንዲያለማ የተጠናከረ ክትትልና ቁጥጥር ተደርጓል። በዚህም በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 2 ሄክታር አካባቢ መልሶ ለምቷል። ወደዘርፉ የሚገቡ አዳዲስ አካላትን ፍቃድ በመስጠትና ወደስራ ከገቡም በኋላ የሚጠበቅባቸውን 3 በመቶ የኳይሪ (በማዕድን ዘርፍ ከተሰማሩ አካላት ከደረሰኝ የሚሰበሰብ ገቢ) ክፍያ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የመሰብሰብ ስራ ሰርቷል፡፡ በሩብ ዓመቱ 15 ሚሊየን ብር ለመሰብሰብ አቅዶ 15 ነጥብ 6 ሚሊየን ብር መሰብሰብ ችሏል፤ እንደ ምክትል ስራ አስኪያጁ ገለጻ፡፡

ምክትል ስራ አስኪያጁ አያይዘው እንዳብራሩት፤ የስነ ምህዳር እና ብዝሀ ህይወት መጠበቅን በተመለከተ ባለስልጣኑ ትኩረት አድርጎ የሚሠራበት ዘርፍ ነው፡፡ ከስነ ምህዳር አንጻር አጠቃላይ በከተማዋ የሚካሄደው የልማት ሥራ ስነ ምህዳሩን የጠበቀ እንዲሆን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል። በመዲናዋ በተለያዩ አካባቢዎች እየተሠሩ ባሉ የወንዝ ዳርቻዎች ልማት የአካባቢው ስነ ምህዳር በተጠበቀ መልኩ እንዲሆን የማረጋገጥና ሙያዊ እገዛ የማድረግ ሥራ በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራት ተሰርቷል፡፡ በዚህ ረገድ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ውስጥ የሚገኙት ከአመራር እስከ ባለሙያ ድረስ በጥናት የተደገፈ ሙያዊ ድጋፍ አድርገዋል፡፡ ከብዝሀ ህይወት ጋር በተያያዘም ሁሉም ህይወት ያላቸው አካላት እንዲጠበቁ ምቹ አካባቢ ከመፍጠር አኳያ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

> **ባለስልጣኑ ከሚሰራቸው የልማት ሥራዎች አንዱ ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ተጣጥመው መሄዳቸውን እየተከታተለ እና እየተቆጣጠረ ማረጋገጥ ነው**

ከስነ ምህዳር እና ከብዝሃ ሕይወት ጋር በተያያዘ በተሠራው ሥራ የመጣውን ለውጥ ምክትል ስራ አስኪጁ ሲገልጹ፤ "የሚሠሩ የልማት ሥራዎች ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ተጣጥመው መሄዳቸውን እየተከታተለ እና እየተቆጣጠረ ማረጋገጥ ችሏል፡፡ ለምሳሌ ቀደም ሲል ካዛንችስ አካባቢ ከፍተኛ የድምጽ ብክለት እንደነበር እናስታውሳለን፡፡ የፍሳሽ ብክለቱም ከፍተኛ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት በካዛንቺስ አካባቢ የድምጽም ሆነ የፍሳሽ ብክለቱ ጠፍቷል፡፡ ፒያሳም በተመሳሳይ ችግር ውስጥ የነበረችበት ሁኔታ አሁን ላይ ችግሩ ተቀርፏል። ወንዞችም ከመልማታቸው በፊት ከኢንዱስትሪዎች፣ ከአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እና ከግለሰቦች በሚወጡ መርዛማ ኬሚካሎች እና ፍሳሾች የተበከሉ ነበሩ፡፡ እነዚህን ወንዞች እና የወንዝ ዳርቻዎችን ከማልማት ጎን ለጎን በካይ አካላትን የመቆጣጠርና የመከላከል ሥራ ተሰርቷል፤ እየተሰራም ነው፡፡ ባለፉት ወራት ከ2 ሺህ 600 በላይ በኢንዱስትሪ የተሰማሩ፣ አገልግሎት ሰጪዎች እና ግለሰቦች ፍሳሻቸውን ከወንዞች ጋር አገናኝተው በመልቀቅ ይበክሉ እንደነበር በተጨባጭ በተደረገው የልየታ ስራ ለማወቅ ተችሏል፡፡ እነዚህን አካላት ከችግራቸው እንዲወጡ በቅድሚያ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ተሰርቷል፡፡ በሂደት መታረም ባልቻሉ አካላት ላይ ደግሞ ከደንብ ማስከበር ባለስልጣን ጋር በመሆን ተጠያቂ ተደርገዋል፡፡ በዚህም በሩብ ዓመቱ ከ40 ሚሊየን ብር በላይ ቅጣት ተጥሎ ለመንግስት ገቢ ተደርጓል፡፡

ምክትል ስራ አስኪያጁ አቶ አሰግደው አንዳሉት፤ ተቋሙ ስራዎችን ከሌሎች ባለድርሻና አጋር ተቋማት ጋር በጋራ የሚሰራ እንደመሆኑ መጠን የሚመለከታቸው ተቋማት እኩል መንቀሳቀስና መፈጸም ላይ ወጣገባነት መኖር ለባለስልጣኑ የሥራ ዕቅድ ስኬታማነት ተግዳሮት ሆኗል፡፡ ይህም ችግር ከአቅም፣ ከክህሎትና ከመረጃ ጋር የተያያዘ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍም ጥረት መደረጉን በማንሳት፤ አሁን ላይ ለውጥ መምጣቱን ተናግረዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፤ ከአካባቢ ብክለት ጋር ያሉ ችግሮች (በተለይም በመጠጥ ቤቶች አካባቢ የሚሰሙ የሙዚቃ ድምፆች) አሁንም ችግር ሆነው መቀጠላቸውን አልሸሸጉም። ለምሳሌ ብዙ ነዋሪ በሚኖርባቸው በጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ ከሚከሰተው የድምጽ ብክለት አንዱ በመጠጥ ቤቶች የሚከፈቱ ሙዚቃዎች ናቸው፡፡ ሙዚቃ ወደውጭ በማውጣት ረብሻ ይፈጠራል። ሌላው አንዳንድ የኮንስትራክሽን ማዕድን የወጣባቸው አካባቢዎች መልሶ የሚያለማ ባለቤት በማጣታቸው ስጋት ሆነው መቀመጣቸው ነው፡፡ ህገ ወጥ አፈር መድፋትም ሌላው ትልቁ ነው፡፡ ህገ ወጥ የአፈር መድፋት የተዛባ የስነ ምህዳርና ብዝሀ ህይወት ችግር የሚፈጥር በመሆኑ በዚህ ዙሪያ እርምጃ ለመውሰድ ችግር ፈጥሯል፡፡ በቅርቡ ችግሩ የሚፈታበት ደረጃ ላይ መደረሱንም አንስተዋል፡፡

በቀጣይ ባለስልጣኑ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራባቸውን ጉዳዮችን ምክትል ስራ አስኪያጁ አስቀምጠዋል፡፡ የመጀመሪያው ብክለትን መከላከል ነው፡፡ ብክለትን ለመከላከልም ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ መስራት እንዳለበት አጽንኦት ሰጥተዋል፡፡ ሁለተኛው ከቅሬታ ጋር በየደረጃው የሚነሱ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ህብረተሰቡንና ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ መፍታት ነው፡፡ ሦስተኛው የኮንስትራክሽን ማዕድን ከተማው ከሚፈልገው ልማት አኳያ ሰፊ ምርት ስለሚያስፈልግ የበለጠ አጠናክሮ መሥራት ነው፡፡


ፎቶ- ከገፀ ድር
ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የሩብ ዓመት አፈፃፀሙን በገመገመበት ወቅት

# የጤና ስንቅ

በፋንታነሽ ተፈራ

የዝግጅት ክፍላችን ከማለዳው 2፡00 ሰዓት ላይ ነበር በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 ማይጨው ጤና ጣቢያ የሚሰጠውን የቅድመ ጤና መከላከል ትምህርት ለመቃኘት የተገኘው፡፡ በእናታቸው ጀርባ ከታዘሉ ህፃናት እስከ አረጋውያን በጠዋቱ ጤናን ፍለጋ ተሰባስበዋል፡፡ ለህክምና በመጡበትም አጋጣሚ በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንዲሉ ከጤና አጠባበቅ እስከ መድኃኒት አጠቃቀም በዘርፉ እውቀት ባላቸው ባለሙያዎች ይማራሉ። የሚሰጠውን ቅድመ የጤና ትምህርት ሁሉም ጆሮውን ሰጥቶ ያዳምጣል፤ ጥያቄ ያለውም ይጠይቃል፡፡ የህክምና ባለሙያዎቹም ለተነሱላቸው ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ በመስጠት ሙያዊ ኃላፊነታቸውን ሲወጡ ለማየት ችለናል፡፡



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

በማይጨው ጤና ጣቢያ በጠዋቱ መርኃ ግብር የቅድመ ጤና መከላከል ትምህርት ሲሰጥ

የጤና አጠባበቅ ትምህርቱን ከሚከታተሉት ውስጥ ለህክምና ወደ ጤና ጣቢያው ከመጡት መካከል መምህርት አብነት ተሾመ አንዷ ናቸው። እንደ እሳቸው አስተያየት ጠዋት ጠዋት የሚሰጠው የጤና አጠባበቅ ትምህርት በቦታው ተገኝተን ለተማርነው ብቻ ሳይሆን ለቤተሰብ፣ ለጎረቤት እንዲሁም እንደ እኔ መምህር ለሆነ ደግሞ ለተማሪዎቹም ጭምር የሚተርፍ ነው ሲሉ ጠቀሜታውን ገልፀውታል፡፡

“ዛሬ በተማርኩት የማህፀን በር ካንሰር እድሜያቸው ለአቅመ ሄዋን ሳይደርስ የግብረ ስጋ ግንኙነት ለሚያደርጉ ወጣት ተማሪዎቼ እንዴት መከላከል እንዳለባቸው ለማሳወቅ ዝግጁ ነኝ። ራሳቸውን ከእርግዝና ብቻ ሳይሆን ከበሽታም እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው የተማርኩትን አስተምራቸዋለሁ” ይላሉ፡፡

“ታምሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ” እንዲሉ የህክምና ባለሙያዎች የሚያስተላልፉልንን የጤና ትምህርት እና የመድኃኒት አጠቃቀም ጭምር በአግባቡ ተግባራዊ ካደረግን በሽታን መከላከል እንዲሁም ከታመምንም በቶሎ ታክመን መዳን የምንችልበት እድል ሰፊ ነው ሲሉ የጤና ትምህርቱን ፋይዳ ነግረውናል፡፡

የመምህርቷን ሃሳብ የሚጋሩት ወይዘሮ በላይነሽ ዳዲም ልጆቻቸውን ወልደው ያሳደጉት በዚሁ ጤና ጣቢያ ነው፡፡ ለክትትልም ይሁን ለህክምና ሲመጡ ጤናቸውን እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው ግንዛቤ አግኝተው እንደሚሄዱም ይናገራሉ፡፡ የሚሰጠው የጤና ትምህርት አንድ ሰው ራሱን ከበሽታ ለመከላከል፣ ሲያመው መቼ ወደ ጤና ጣቢያ መሄድ እና መድኃኒቶችን እንዴት መጠቀም እንዳለበት ሙሉ መረጃ የሚሰጥ ነው ያሉት ወይዘሮዋ፤ ከዚህ በፊት በተሰጣቸው የማህፀን በር ካንሰር ትምህርት ቅድመ ምርመራ አድርገው ራሳቸውን እንዳወቁ ያስታውሳሉ፡፡ ከዚህም አልፈው አንድ ጎረቤታቸውን ምርመራ እንድታደርግ እንዳደረጓት ገልፀዋል፡፡

ሌላኛው በጤና ጣቢያው የሚሰጠው የጤና ትምህርት ለእሳቸውና ለቤተሰባቸው እንደጠቀማቸው የተናገሩት ደግሞ በልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ጤና ፅህፈት ቤት በተክለ ኃይማኖት ጤና ጣቢያ ተገልጋይ የሆኑት አቶ ካህሳይ ሃይሌ ናቸው፡፡ በጤና ጣቢያው ብዙ ጊዜ ለምርመራና ለህክምና በሚመጡበት ወቅት የጤና አጠባበቅ ትምህርት ይከታተላሉ። “የተማርኩትን የጤና አጠባበቅ ትምህርት ለባለቤቴ እና ለልጆቼ ማታ ላይ እነግራቸዋለሁ፡፡ ቤተሰቦቼ ጨው አብዝተው እንዳይጠቀሙ አደርጋለሁ፣ ንፅህናዬን እጠብቃለሁ፣ ጠዋት እና ማታም እንቅስቃሴ አደርጋለሁ” ሲሉ ነው የተማሩትን በተግባር እየኖሩት እንደሆነ የተናገሩት፡፡

በጤና ጣቢያው የጤና ትምህርት ከሚሰጡ ባለሙያዎች ውስጥ ሲስተር ስንታየሁ ታደሰ አንዷ ናቸው፡፡ “በሽታን ከማከም ይልቅ አስቀድሞ መከላከል ላይ መስራቱ የበለጠ ጠቀሜታ አለው። ለዚህም በጤና ጣቢያችን ሁልጊዜም ጠዋት ለህክምና የሚመጡ የማህበረሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ይፈጠርላቸዋል፡፡ ዓላማውም ማህበረሰቡ ራሱን ከበሽታ እንዲከላከል እና ጤናማ ኑሮ እንዲኖር ነው” ይላሉ፡፡

በማይጨው ጤና ጣቢያ ሲያስተምሩ ያገኘናቸው የፋርማሲ ኃላፊ ወይዘሮ ትዕግስት ሰለሞን በበኩላቸው፤ ታካሚዎችም ሆነ አስታማሚዎች ወደ ጤና ጣቢያው ሲመጡ ህክምና አግኝቶ ብቻ መሄድ ሳይሆን የመድኃኒት አጠቃቀምና የሚያስከትለውን የጎንዮሽ ጉዳት በጠዋቱ የጤና አጠባበቅ ትምህርት ላይ ይማራሉ፡፡ ለህክምናም ሆነ ታካሚን ይዘው የሚመጡ ጤና እና ጤና አጠባበቅ ጉዳዮች ላይ የተማሩ እና ሙሉ በሙሉ የሚያውቁ ባለመሆናቸው ለህክምና በመጡበት ወቅት ጤናቸውን እንዲጠብቁ እና ቀድመው በሽታን መከላከል እንዲችሉ የጠዋት ትምህርቱ ያግዛቸዋል፡፡ በጤና ጣቢያው ከሰኞ እስከ አርብ በሚሰጠው የጤና አጠባበቅ ትምህርት የተለያዩ ሰዎች ስለሚስተናገዱ ከራሳቸው አልፈው ለቤተሰቦቻቸው፣ ለጎረቤቶቻቸው እና ለአካባቢው ሰዎች ሳይቀር ያወቁትን እንዲያሳውቁ እንደሚረዳቸው ተናግረዋል፡፡

በጤና ጣቢያው የጤና አጠባበቅ ትምህርት ክፍል ኃላፊ ሲስተር ራሄል ታምሩ እንደሚናገሩት የጤና አጠባበቅ ትምህርት በሽታ በመከላከል ረገድ አስተዋፅኦው የጎላ ነው፡፡ ትምህርቱ ከጠዋቱ 2፡05 ሰዓት አንስቶ እስከ 2፡30 ሰዓት ድረስ ይሰጣል፡፡ በዋናነት ለህክምና የሚመጡ የማህበረሰብ ክፍሎችን በተለያየ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶች በተለይም በክትባት ጥቅሞች፣ የማህፀን በር ካንሰር፣ የስኳር በሽታ ምንነትና መቆጣጠሪያ መንገዶቹ፣ የደም ግፊት፣ የኤች አይ ቪ ኤድስ መተላለፊያና መከላከያ መንገዶች፣ የመድኃኒት አጠቃቀም እና የጎንዮሽ ጉዳት፣ የንፅህና አጠባበቅ፣ የእርግዝና መከላከያ መንገዶች እንዲሁም ወቅታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ይሰጣሉ፡፡

ጤና ጣቢያው በዓመት ቁጥራቸው 32 ሺህ የሚሆኑ ተጠቃሚዎችን የሚያስተናግድ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ እያንዳንዱ ሰው በዓመት ከሁለት እስከ ሦስት ጊዜ ይመጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህም በቀን ከ150 እስከ 200 የሚሆኑ ታካሚዎች አገልግሎቱን ያገኛሉ፡፡

እንደ ሲስተር ራሄል ገለፃ፣ የጤና አጠባበቅ ትምህርት ማህበረሰቡ በሽታ መከላከል ላይ ያለውን ንቃተ ህሊና በማሳደግ ለውጥ አምጥቷል፡፡ ከዚህ በፊት መድኃኒት የሚያቋርጡ በአግባቡ መድኃኒታቸውን መውሰዳቸው፣ የግልና አካባቢ ንፅህናቸውን መጠበቃቸው እንዲሁም ማህበረሰቡ ጥያቄዎች በመጠየቅ ግብረ መልሶችን መቀበሉ ለማሳያነት መጥቀስ እንደሚቻል አንስተዋል፡፡

የተክለ ኃይማኖት ጤና ጣቢያ ለሁለት ወረዳ የማህበረሰብ ክፍሎች አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን በዓመት 107 ሺህ የማህበረሰብ ክፍሎች ይስተናገዳሉ ያሉት የጤና ጣቢያው ሜዲካል ዳይሬክተር አቶ ከተማ አለሙ ናቸው፡፡

የጤና ትምህርት የጤና ሁሉ መሰረት ነው፡፡ ምክንያቱም የጤና ትምህርት ሲሰጥ ሰዎች ሊደርስባቸው ከሚችለው የጤና ችግር ራሳቸውን የሚከላከሉበት ነው፡፡ የሀገራችንም የጤና ፖሊሲ መከላከልና አክሞ ማዳን ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ለዚህም ጤና ጣቢያችን ከሰኞ እስከ አርብ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ደም ግፊት፣ ስኳር፣ ካንሰር እና ተላላፊ በሆኑ በሽታዎች እና የንፅህና አጠባበቅ ላይ ትምህርቶችን ይሰጣል፡፡

ጤና ጣቢያው የማህበረሰቡን ጤና ለመጠበቅ እየተጋ እንዳለ የሚናገሩት አቶ አለሙ፤ ከጠዋቱ ትምህርት በተጨማሪ ማንኛውም አገልግሎት ፈልጎ የመጣ ታካሚ መጀመሪያ እንደገባ የደም ግፊት ልኬት እንደሚደረግለት እና እራሱን የሚያውቅበት ሁኔታ እንዳለ ነው የነገሩን። ባለሙያዎችም እቅድ ከማውጣት ጀምሮ ተዘጋጅተው በማስተማር ሙያዊ ኃላፊነታቸውን ይወጣሉ፡፡ የተማሩትም ትምህርት ላልተማሩት ቤተሰብና ጎረቤቶቻቸው ለማስገንዘብም በራሪ ወረቀቶች ያድላሉ። ጤና ጣቢያው በየቀኑ ምን ያህል በራሪ ወረቀቶች እንደተበተኑም ክትትል በማድረግ ይመዘገባል ብለዋል፡፡

መንግስት የዜጎችን ጤና ለማስጠበቅ ሲታትር የማህበረሰቡን ኃላፊነት በተመለከተ በቅድሚያ የራሱን ጤና መጠበቅ፣ ከጤና ባለሙያዎች የሚያገኘውን መረጃ ለሌላው ማካፈል፣ የተሰጠውን ትምህርት በአግባቡ መተግበር ያስፈልጋል ሲሉም ይመክራሉ።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ በሽታ መከላከል እና ጤና ማጎልበት ዳይሬክቶሬት የጤና አጠባበቅ ትምህርት ባለሙያ መርሻ ወልደገብርኤል እንደገለፁት እንደ ሀገር የምንከተለው የጤና ፖሊሲ ቅድመ የጤና መከላከል ፖሊሲ ነው፡፡ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና አጠባበቅ ትምህርቱም የተጀመረው የጤና ኮሌጆች ከተጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡

አዲስ አበባ ከተማም ይህንኑ የጤና ፖሊሲ ለማሳካት እየሰራች ትገኛለች። በከተማዋ በሁሉም ጤና ጣቢያዎች መከላከልን መሰረት ያደረጉ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ጠዋት የሚሰጠው የጤና ትምህርት አንዱ ነው። አሁን ላይ ሚዛኑን እየደፋ የመጣው ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ስርጭት እንደ ስኳር፣ ካንሰር፣ የደም ግፊት፣ የጡትና የማህፀን በር ካንሰር የመሳሰሉት እና ተላላፊ የሆኑ በሽታዎች ላይ እንዴት መቆጣጠር እና መከላከል እንደሚቻል ትምህርቱ እየተሰጠ ይገኛል፡፡

የጤና ትምህርቱን ወደ ማህበረሰቡ ተደራሽ ለማድረግ በከተማዋ ባሉ ሁሉም ጤና ጣቢያዎች ትምህርቱ እንደሚሰጥ የገለፁት አቶ መርሻ፤ ማህበረሰቡ ጤና ላይ ያለው ግንዛቤ እየጨመረ በሄደ ቁጥር ጤናውን ሊጎዱ ከሚችሉ ችግሮች ራሱን እንዲጠብቅ ማድረግ ዋናው ዓላማችን ነው፡፡ ይህም ጤናማ ማህበረሰብን ከመፍጠር በተጨማሪ ለህክምና የሚወጡ ወጭዎችንም የሚቀንስ ነው፡፡

እንደ ጤና ቢሮ ለጤና ተቋማት ሁለት አይነት ክትትል እና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ ይህም የድንገተኛ ክትትል አንዱ ሲሆን፤ ጤና ጣቢያዎች በጠዋቱ የጤና አጠባበቅ ትምህርት ላይ እቅድ መያዛቸውን፣ ተጨባጭ በሆኑ መርጃ መሳሪያዎች መጠቀማቸውን፣ በሰዓቱ ማስተማራቸውን እና በሚገባቸው ቋንቋ መልዕክት ማስተላለፋቸውን ሙሉ ክትትል ይደረጋል፡፡ ሁለተኛው ክትትል ደግሞ በየሩብ ዓመቱ ክትትል በማድረግ ግብረ መልስ ይሰጣል። በእነዚህ መነሻነትም ሁሉም የክፍለ ከተማ ኃላፊዎች በተገኙበት የተሻለ ስራ የሰሩ እና ያልሰሩ ባለሙያዎችን በመለየት መሻሻል ያለባቸውን ጉዳዮች እንዲያሻሽሉ ይደረጋል፡፡

የጤና አጠባበቅ ግንዛቤ ፈጠራው በጥናት የተደገፈ ባይሆንም ከበፊቱ በተሻለ ለውጥ እያመጣ መሆኑን የተናገሩት አቶ መርሻ፤ ለዚህም በምሳሌነት የጠቀሱት፤ ማህበረሰቡ የራሱን እና የአካባቢውን ንፅህና እየጠበቀ መሆኑ፣ የእያንዳንዱን በሽታዎች ምንነት እና ምን ማድረግ እንዳለበት እንደሚመልስ እና የኤች. አይ.ቪ ኤድስ ስርጭት መቀነሱን በማሳያነት ይጠቅሳሉ፡፡

የባህሪ ለውጥ የሚያመጣው የግንዛቤ ፈጠራ ውጤት ነው የሚሉት አቶ መርሻ ለወደፊትም የማህበረሰቡን የባህሪ ለውጥ ለማምጣት የግንዛቤ ፈጠራው ላይ በሰፊው ይሰራል፡፡ የባህሪ ለውጥ ለማምጣት የረጅም ጊዜ ስራ የሚፈልግ በመሆኑ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በጤና ትምህርቱ የመጣውን የባህሪ ለውጡን ለማወቅም ወደፊት ጥናት እንደሚደረግም ጠቁመዋል፡፡

## ፓርላማው... ከገጽ 6 የዞረ

ጤናን በተመለከተ በአሁኑ ወቅት 63 ሚሊዮን ዜጎች በጤና መድህን ታቅፈዋል፡፡ መድኃኒቶችን በሀገር ውስጥ ለማምረት ከመስራት ባሻገር 60 ቢሊዮን ብር ድጎማ በማድረግ እየቀረቡ ይገኛሉ። የካንሰር ህክምና ወጪ 60 በመቶ በመንግስት እየተሸፈነ ነው፡፡ የውጭ ባለሀብቶች መጥተው እንዲሰሩ ጥረት እየተደረገ ሲሆን አሁንም የጤና መሰረተ ልማቶችን በማልማት ረገድ ሰፊ ስራዎች እንደሚጠበቁ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) አብራርተዋል፡፡

### ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች

ከምክር ቤት አባላት በኢኮኖሚ ዘርፍ የሀገር በቀል ማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ውጤታማነት ምን ይመስላል? የሚል ጥያቄ ተነስቷል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሰጡት ማብራሪያ፣ ከአንድ ዘርፍ ይልቅ ብዝሃ ዘርፍና ብዝሃ ተዋናይ የኢኮኖሚ አቅጣጫ መከተል ያስፈልጋል የሚል እምነት ተይዞ የተነደፈው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲው በእጅጉ ውጤታማ እየሆነ ይገኛል ብለዋል፡፡

በመንግስትና የህዝብ አጋርነት በርካታ ውጤት ተገኝቷል፡፡ ለዚህ ማሳያ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርን ማንሳት የሚቻል ሲሆን ባለፉት ዓመታት ኢትዮጵያ 48 ቢሊዮን ችግኝ መትከል ችላለች፡፡ እያንዳንዱ ችግኝ ከጅምሩ አንስቶ እስከሚተከልበት ድረስ ባለው ሂደት አንድ ዶላር ያዋጣል ተብሎ ቢታሰብ 48 ቢሊዮን ዶላር የአየር ንብረት ለውጥ ለመከላከል አውጥታለች ማለት ነው። ይህንን ማሳካት የተቻለውም ከ25 ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያንን በማሳተፍ እንደሆነ አንስተዋል፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚው አንደኛው ስብራት የገቢ አሰባሰብን ማሳደግ እንደሆነ ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) በሪፎርሙም ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት እንደተቻለ ጠቁመዋል፡፡ ሀገራዊ ለወጡ የመጣ አካባቢ መንግስት የሚሰበስበው ገቢ 170 ቢሊዮን ብር የነበረ ሲሆን በተያዘው ዓመት አንድ ትሪሊዮን ብር እንደሚጠበቅ ተናግረዋል፡፡

ሌላኛው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ዓላማ የወጪ ንግድ ገቢን ማሳደግ ሲሆን፤ በ2016 ዓ.ም ዓመቱን ሙሉ ከወጪ ንግድ የተገኘውን ገቢ በተያዘው ዓመት በአራት ወራት ብቻ ማሳካት እንደተቻለና ይህም ውጤት እየመጣ መሆኑን እንደሚያሳይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ገልፀዋል፡፡

የውጭ ዕዳንም በተመለከተ ኢትዮጵያ ከፍተኛ እዳ እንዳለባት ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በአፍሪካ ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ ደረጃ የሚቀመጥ ኢኮኖሚ ያላቸው ሀገራት ግን ከኢትዮጵያ በብዙ እጥፍ እዳ ያለባቸው ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ የወሰደችው ብድር በአጭር ጊዜ ብዙ መክፈል የሚጠይቅ የብድር ስርዓት ነው። ይህ ዕዳ እንዲሸጋሸግ ከአበዳሪዎች ጋር ድርድር በማድረግ በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ከ4 እስከ 4 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር በረጅም ጊዜ እንዲከፈል ስምምነት ላይ ተደርሷል። "ኢትዮጵያ አሁን ዕዳ ለመክፈል ችግር የለባትም፡፡" ብለዋል ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፡፡

የብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሬ ክምችትም ከሀገራዊ ለውጡ በፊት ከነበረው ጋር ሲነጻፀር የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ከተደረገ በኋላ ከአስር እጥፍ በላይ አድጓል፡፡ የቢዝነስ ከባቢን (Ease of Doing Bussiness) ለማሻሻል በተወሰዱ እርምጃዎችም ለረጅም ጊዜ ቆሞ የነበረው ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል እንድትሆን የማድረግ ጥረት በጥሩ ሁኔታ እየሄደ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡

የኢኮኖሚ እድገቱን በተመለከተም በየዘርፉ ብንመለከት ግብርና ባለፈው ዓመት 7 ነጥብ 3 በመቶ እድገት አስመዝግቧል፡፡ ለማሳያነትም በ2010 ዓ.ም ኢትዮጵያ 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ኩንታል ሩዝ ታመርት ነበር፡፡ ባለፈው ዓመት 63 ሚሊዮን ኩንታል ተመርቷል። የስንዴ ምርትን ብንመለከት በሀገራዊ ለውጡ ማግስት 47 ሚሊዮን ኩንታል ይመረት የነበረ ሲሆን ባለፈው ዓመት ከ280 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡ በለውጡ ማግስት ይመረት ከነበረው ቡና የሚገኘውን ገቢም ባለፉት ዓመታት በተሰራው ስራ በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ እንደተቻለ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡

ባለፈው ዓመት የኢንዱስትሪ ዘርፍ እድገት 13 በመቶ ሲሆን በተለይ በማዕድን፣ በማኑፋክቸሪንግና ሀይል ላይ ተስፋ ሰጪ ውጤት መታየቱን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ገልጸዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) እንደገለፁት የኢትዮጵያ ሪፎርም ስኬታማ፣ ለብዙ ሀገሮችም ምሳሌ የሚሆንና በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት የተወደሰ ነው፡፡ በውጭ ምንዛሪ ግኝት ረገድም በኢትዮጵያ ታሪክ ከፍተኛ ገቢ የተገኘበት ዓመት ነው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ 8 ነጥብ 3 ቢሊዮን ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ አገልግሎትን በመሸጥ (Export of Service) 8 ነጥብ 1 ቢሊዮን ዶላር ተገኝቷል። በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገር ቤት ከሚልኩት ወይም ከሪሚታንስ 7 ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር ተገኝቷል፡፡ ከውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ደግሞ ከ4 ቢሊዮን ዶላር በላይ ተገኝቷል። "የኢትዮጵያ እድገት ጥሩ አፍንጫ ያለው ሰው በ'ሽታ' ያውቀዋል፤ ጥሩ ዓይን ያለው ሰው ያየዋል፤ ጥሩ ጆሮ ያለው ሰው በመስማት ይረዳዋል፤ ለመላ አፍሪካ ምሳሌ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡" ሲሉ ነው የገለፁት።

የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበትን ለማቃለል ምን እየተሰራ ነው? የሚለው ሌላኛው ከምክር ቤት አባላት የተነሳ ጥያቄ ሲሆን፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) በሰጡት ማብራሪያ፣ የዋጋ ግሽበት ከባለፉት 20 ዓመታት ወዲህ ያለፈው ዓመት ረግቦ የታየበት ነው። ይህም የሆነበት የምርት አቅርቦትን በማሳደግ፣ የገበያ ትስስርን በማጠናከር፣ ድጎማ (440 ቢሊዮን ብር ለሴፍቲኔት፣ ማዳበሪያ፣ ነዳጅ፣ ደመወዝና የተለያዩ ነገሮች) በማድረግ በተሰራው ስራ ነው፡፡ ይህ የድጎማ ወጪ ሀገራዊ ለውጡ ሲመጣ ከነበረው ዓመታዊ የኢትዮጵያ በጀት የሚበልጥ ነው፡፡ የጥቅምት ወር የዋጋ ግሽበትም 11 ነጥብ 7 በመቶ ማውረድ ተችሏል፡፡ ይህም አመርቂ ውጤት ነው፡፡ በተያዘው ዓመት ወደ ነጠላ አሃዝ ለማውረድ ርብርብ እንደሚደረግ አብራርተዋል።

የጋዝ ምርትን በተመለከተም በሶማሌ ክልል ጋዝ ማምረት በተጀመረበት አካባቢ ብቻ 21 ትሪሊዮን ኪዩቢክ ፊት መጠን ያለው የጋዝ ክምችት እንዳላት ተረጋግጧል። የድፍድፍ ነዳጅ ክምችትም እንዲሁ ከፍተኛ እንደሆነ መረጋገጡን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡ የነዳጅ ማጣሪያ ግንባታም ልክ በቅርቡ እንደተጀመረው ሁለተኛው ምዕራፍ የጋዝ ምርት በተጨማሪ በ24 ወራት ለማጠናቀቅ እንደሚሰራ ጠቁመዋል። አንድ ሺህ ሜጋ ዋት የሚያመነጭ ሀይልና ሌሎች ፕሮጀክቶች ከፍተኛ ትርጉም ያላቸው ናቸው። ኢትዮጵያ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የምታወጣው ለነዳጅና ማዳበሪያ ግዢ ነው፡፡ ሁለቱን በሀገር ውስጥ መተካት ከተቻለ ለልማት የሚሆን ከፍተኛ ሀብት ማዳን እንደሚቻል አብራርተዋል፡፡

በዳንጎቴ ኩባንያ የሚለማው የማዳበሪያ ፋብሪካ በዓመት 30 ሚሊዮን ኩንታል የዩሪያ ማዳበሪያ የማምረት አቅም ያለው መሆኑን ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፣ የጋዝ ማስተላለፊያ መስመር ዝርጋታ፣ የማዳበሪያ ፋብሪካ፣ ምዕራፍ ሁለት የጋዝ ፋብሪካ፣ አንድ ሺህ ሜጋ ዋት ሀይል ማመንጨት፣ የነዳጅ ማጣሪያና መሰል መሰረተ ልማቶች ግንባታ 10 ቢሊዮን ዶላር መመደቡን ተናግረዋል፡፡

የቢሾፍቱ ዓለምአቀፍ አየር ማረፊያ ፕሮጀክትም በዓመት ከ100 ሚሊዮን በላይ መንገደኞችን ማስተናገድ የሚችል አቅም ያለውና በአስር ቢሊዮን ዶላር ወጪ የሚገነባ ነው፡፡ ሲጠናቀቅም በአፍሪካ ትልቁ የአየር ማረፊያ እንደሚሆን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡

ሌላው ከምክር ቤት አባላት የቤት አቅርቦትን ተደራሽ ለማድረግ ምን እየተሰራ እንደሆነ የተነሳ ሲሆን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) በሰጡት ማብራሪያ፤ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ የቤት ባለቤት ማድረግ ስለማይቻል ቢያንስ በአቅሙ ተከራይቶ መኖር የሚችልበትን አማራጭ ለመፍጠር እንደሚሰራ ጠቁመዋል፡፡

ፕሮጀክቶችን ጀምሮ ከማጠናቀቅ አኳያም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንደገለፁት በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት መንገድን ብቻ ብናነሳ በፌዴራል መንግስት የሚገነቡ 1 ነጥብ 5 ትሪሊዮን ብር ወጪ የሚጠይቁ 346 የመንገድ ፕሮጀክቶች እየተገነቡ ይገኛሉ። በሀይል ማመንጨትና የመብራት ማስተላለፊያ ስራዎች በርካታ ቢሊዮን ብር የሚጠይቁ ስራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኙና ከስራው ስፋት አኳያ ያሉ ክፍተቶችን በማረም እንደሚሰራም ጠቁመዋል፡፡

ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንደገለፁት በ2032 ዓ.ም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ቢያንስ ከአፍሪካ ሁለተኛው ግዙፉ ኢኮኖሚ ይሆናል። በ2036 ዓ.ም ደግሞ ከአፍሪካ ቀዳሚነቱን ይይዛል፡፡

## ጤናማ ኑሮ ለመኖር ልንከተላቸው የሚገቡ ነገሮች

**ማንኛውም ሰው ጤናማ ኑሮ ለመኖር የረጅም ጊዜ ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ ነገር ነው። ይህንንም ለመኖር የሚከተሉትን ጠቃሚ ምክሮች ተግባር ላይ ማዋል ያስፈልጋል።**

*** የጤና ሁኔታን መገምገም**

*ወደ ጤናማ ኑሮ ለመሸጋገር የሚረዳን የመጀመሪያው እርምጃ አሁን የሚገኙበትን የጤና ሁኔታ መገምገምና ማወቅ ነው፡፡ ወደ ጤና ተቋማት በመሄድ የጤናዎን ሁኔታ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡*

*** ከሱስ መራቅ**

*ሥር የሰደደ የጤና ችግር ማለትም የልብ በሽታ፣ የስኳር በሽታ፣ ጭንቀት፣ ወይም ሌሎች ህመሞች እንዳሉ ከተረዱ ሲጋራ ማጨስን ጨምሮ ከማንኛውም ዓይነት አደገኛ ሱሶች ራስን ማራቅ አስፈላጊ ነው፡፡*

*** አካላዊ እንቅስቃሴ ማድረግ**

*በየጊዜው እንቅስቃሴን አዝናኝ በሆነ መንገድ ከጓደኞች ጋር በመሆን የእግር ጉዞ መጓዝ፤ ተራራ መውጣትን ባህል በማድረግ፤ የዳንስ ወይም የካራቴ ትምህርት መውሰድ የመሳሰሉትን ነገሮች በማድረግ እየተዝናኑ ጤናማ ሆኖ መኖር ይቻላል፡፡*

*** አመጋገብን ማስተካከል**

*የተሻለና ጤናማ ኑሮ ለመኖር ቀጣዩ እርምጃ አመጋገብን ማስተካከል ነው፡፡ አመጋገብን ለማስተካከል በመጀመሪያ አስተሳሰባችንን ማስተካከል ተገቢ ነው፡፡ ከዚያም አቅም በፈቀደው መጠን በየዕለቱ የተለያዩ ፍራፍሬዎችንና አትክልቶችን መመገብ ተገቢ ነው፡፡ ይህም ሰውነት የሚያስፈልገውን ንጥረ ነገር ለማግኘት ይረዳዋል፡፡*

*** ጭንቀትን ማስወገድ**

*የተሻለ ህይወት እንዲኖረን ከውጥረት የጸዳ ኑሮን መምራት ይኖርብናል፡፡ የሚያስጨንቅ ነገር ሲያጋጥም ይህ ነገር ከጥቂት ጊዜ በኋላም የኔው ጉዳይ ሆኖ ይቆያል ወይ?" በማለት ራስን መጠየቅ፡፡ ጭንቀት ከሚያመጡ ሃሳቦች ይልቅ ቀና ስለሆኑ ነገሮች በማሰብ ራስን ጭንቀት ውስጥ እንዳይገቡ ማድረግ ይቻላል፡፡*

*** በቂ እንቅልፍ መተኛት**

*እንቅልፍ አለመተኛት በጤና ላይ ችግር ስለሚፈጥር ለመተኛት የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን በማመቻቸት በቂ እንቅልፍ ማግኘት አስፈላጊ ነው፡፡*

*** ጥሩ የሆነ ማህበራዊ ግንኙነትን ማዳበር**

*አንድ ሰው ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለው ግንኙነት ጥሩ መሆን፤ ከእኛ ተመሳሳይ የሆነ አስተሳሰብ ካላቸው ሰዎች ጋር የቅርብ ወዳጅነት መመስረት፣ ሰዎች ጋር ጥሩ ጊዜ ማሳለፍ አስፈላጊ ነው፡፡*

*** አእምሮን ዘወትር ማሰራት**

*ሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን አእምሮን የሚያነቃቁ እንቅስቃሴዎች ላይ በመሳተፍ የመርሳት በሽታ የመጋለጥ እድልን ይቀንሳል፡፡*

**ምንጭ፡-** Ethiopia Today የማህበራዊ ትስስር ገፅ

SIKET BANK

# የስኬት ባንክ አ.ማ.
## የባለአክሲዮኖች 3ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የስብሰባ ጥሪ

**የተከበራችሁ የስኬት ባንክ አ.ማ. ባለ አክሲዮኖች**

በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 ዓ/ም አንቀጽ 366/1፤ 367/1 እና 370 እንዲሁም በአክሲዮን ማህበሩ የመመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 17/3 እና 18 (1,2) መሰረት የስኬት ባንክ አ.ማ. የባለአክሲዮኖች 3ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ህዳር 20ቀን 2018ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ጀምሮ **አዲስ አበባ በሚገኘዉ ሸራተን አዲስ ሆቴል** ስለሚካሄድ በዕለቱ ባለ አክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተጠቀሰው ቀን፣ ሰዓትና ቦታ በጉባኤው ላይ እንድትገኙ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

### 1. ማህበሩን የሚመለከቱ ዋናዋና መረጃዎች

1.1. የአክሲዮን ማህበሩ ስም፡- ስኬት ባንክ አክሲዮን ማህበር

1.2. የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት አድራሻ፡- አዲስ አበባ፡ አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01፡ የቤ/ቁ አዲስ

1.3. የባንኩ ድህረ ገጽ፡- https://www.siketbank.com/

1.4. የአክሲዮን ማህበሩ የንግድ ምዝገባ ቁጥር፡- LBB/TM/033/2023

1.5. የአክሲዮን ማህበሩ ዓይነት፡- በባንክ ሥራ የተሰማራ

1.6. የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ካፒታል፡- 10,000,000,000.00

1.7. የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ካፒታል፡- 6,920,992,522.00

### 2. የባለ አክሲዮኖች 3ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

2.1. እስከ መስከረም 30 ቀን 2018 ዓ/ም ድረስ የተደረጉ የአክሲዮን ዝውውሮችን መቀበል፤

2.2. እ.ኤ.አ. የ2024/2025 የሒሳብ ዓመት የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥና በቀረበው ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ለመወሰን፤

2.3. እ.ኤ.አ. የ2024/2025 የሒሳብ ዓመት የውጪ ኦዲተሮችን ሪፖርት ማዳመጥና በቀረበው ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ለመወሰን፤

2.4. እ.ኤ.አ. የ2024/2025 የሒሳብ ዓመት የተገኘ የተጣራ ትርፍ አደላደልና አከፋፈል ሁኔታ ላይ በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ ለመወሰን፤

2.5. እ.ኤ.አ. የ2024/2025 የሒሳብ ዓመት ለዳይሬክተሮች ቦርድ ከተጣራ ትርፍ ላይ የሚታሰብ ዓመታዊ የስራ ዋጋ ክፍያ መወሰን፤

2.6. እ.ኤ.አ. የ2025/2026 የሒሳብ ዓመት ለሚያገለግሉ የውጭ ኦዲተሮች የሥራ ዋጋ ክፍያ ላይ ተወያይቶ ለመወሰን፤

2.7. እ.ኤ.አ የ2025/2026 የሒሳብ ዓመት የዳይሬክተሮች ቦርድ ወርሃዊ አበል መወሰን፡፡

### 3. ማሳሰቢያ

3.1. በጉባኤው ላይ በአካል መገኘት የማይችሉ ባለ አክሲዮኖች ተወካዮቻችሁ ሥልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውንና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም ንግድ ሕግ አንቀጽ 377 መሰረት ጉባኤው ከመካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት በባንኩ ዋና መ/ቤት 4ኛ ፎቅ በሚገኘው ኢንቨስትመንትና የሶስተኛ ወገን ፈንድ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በባንኩ በተዘጋጀው የውክልና መስጫ ቅጽ ላይ በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባኤው ተካፋይ ለመሆንና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡ ሆኖም አንድ ባለ አክሲዮን በባንኩ ጠቅላላ ጉባኤ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ መሆኑን እናሳውቃለን። በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 አንቀጽ 20/3 መሰረት የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትና ሠራተኞች በማናቸውም የባለአክሲዮኖች ጉባኤ ላይ ማንኛውንም ባለአክሲዮን ወክለው መገኘት አይችሉም፡፡

3.2. የባንኩ ባለአክሲዮኖች ወይም ህጋዊ ወክሎቻቸው በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ዜግነታቸው ኢትዮጵያዊ መሆኑን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ ዋናዉንና ፎቶ ኮፒ በመያዝ በጉባኤው ላይ መሳተፍ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት ወታወቂያ (ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው እናሳውቃለን፡፡

3.3. ለተጨማሪ መረጃ ፒያሳ ቸርችል ጎዳና በሚገኘው የባንኩ ዋና መ/ቤት 4ኛ ፎቅ በሚገኘው የኢንቨስትመንትና የሶስተኛ ወገን ፈንድ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በአካል በመቅረብ ወይም በስልክ ቁጥር +251111274338 በመደወል መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**የዳይሬክተሮች ቦርድ**

**ስኬት ባንክ አክሲዮን ማህበር**

በአድማሱ ሀይሌ ብሩ እና ገነት ዘውዴ ፍቅሬ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 05 የሚገኘው በይዞታ ካርታ ቁጥር AA000080503778 በሴሪ ቁጥሩ 091572 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በታረቀኝ ቀነአ ዲሳሳ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 የሚገኘው በይዞታ ካርታ ቁጥር AA000080110155640321 በሴሪ ቁጥሩ 209162 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ።**

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማናጅመንት ቢሮ በካርታ ቁጥር የካ/202578/09 በሴሪ ቁጥር 0117676 በራሄል ተክለሀይማኖት አበበ ስም የተመዘገበ የሙብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር የካፖ/ለ/ቀ/15/3458/18 በቀን 14/02/2018 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም ሙብት አለኝ ባይ በ90 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ምትክ ሰርተፍኬት የሚሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ጥረት የጋ/ህ/ስ/ማህበር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር አቃ/ቃ/ክ/ከ/ሊዝ0500 የሴሪ ቁጥር 191345 የይዞታ ስፋት 1135.68 ካ.ሜትር የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸውን በቁጥር ወ/መ/10/6982/18 በቀን 05/02/18 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅላቸው እየገለፅን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ እስከ 30 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ሄራን ተካ ቢሊ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 15 ካርታ ቁጥር ቦሌ/15/59/1/1/42637/00 በሴሪ ቁጥር 1493113 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ/ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር የካ/182707/06 ሴሪ ቁጥር 010461 በአቶ አስፋው ገ/መድህን ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ደብሊው ኤፍ ኮንስትራክሽን እና ሪል እስቴት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000060502196 ሴሪ ቁጥር L 0106684 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ የመሬት ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ።**

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማናጅመንት ቢሮ በካርታ ቁጥር የካ/202579/09 በሴሪ ቁጥር 0117677 በራሄል ተክለሀይማኖት አበበ ስም የተመዘገበ የሙብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር የካፖ/ለ/ቀ/15/3458/18 በቀን 14/02/2018 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም ሙብት አለኝ ባይ በ90 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ምትክ ሰርተፊኬት የሚሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 አስተዳደር ውስጥ በብሎክ 237 የቤት ቁ 237/01 በካርታ ቁጥር አ/ቃ/4/3/1099/00 በሴ.ቁጥር 1563381 የተመዘገበ ይዞታ ማህደራቸው ከማህደር ክፍላችን መገኘት የነበረበት የጠፋባቸው ስለሆነ ማህደሩን የያዘ ግለሰብ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ መጥተው ካላሳወቁ ማህደር በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 03 የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/03/82069/00 ሴሪ ቁጥር 1540322 የሆነው አቶ ገረመው አዱኛ መንግስቴ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 17/02/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ30 (ሰላሳ)ቀናት ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 09 የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ቁጥር ወ9/ውዝ01/105/2833/00 በዶ/ር ተስፋዬ አካሉ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት /ካርታ/ የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 14/02/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ሰርተፍኬት/ካርታ/ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በወ/ሮ ሰሎሜ ሀይሉ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የዞታ በልደታ ክ/ከ በአዲሱ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር 183 የካርታ ቁጥር ዴ12/840/2128/00 ሴሪ ቁጥር 003983 በቀን 01/03/2004 ዓ.ም፣ የተሰጣቸው ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ ታውጆ አገልግሎት እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሰው የባለይዞታው ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጅናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ ሙብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ ሙብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አደይ አበባ ሪልስቴት ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ለ/ኩራ2/51/3/64329/0204/7/00 የሴሪ ቁጥር 1645718 የተሰጠበት ቀን 24/9/2015 ዓ/ም የቦታው ስፋት በሰነድ 65.05 ሜ.ካ የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ እንዲጻፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት በወረዳ 03 የሆነው መኖሪያ ቤት በአደይ አበባ ሪልስቴት ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ለ/ኩራ2/51/3/64329/0204/7/00 የሴሪ ቁጥር 1645718 የተሰጠበት ቀን 24/9/2015 ዓ/ም የቦታው ስፋት በሰነድ 65.05 ሜ.ካ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ኦርጅናል የጠፋ ስለሆነ ይዞታ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ካርታውን የምናዘጋጅ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# ስኬታማዎቹ የጎዳና ላይ ሩጫ አትሌቶች




ፎቶ- ከገፀ ድር

የ2025 የዓመቱ የጎዳና ላይ ምርጥ አትሌቶች ሽልማት እጩዎች

**በሳህሉ ብርሃኑ**

ዓለም አቀፉ የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን ዓለም አቀፍ የባለሙያዎች ፓናል በዓመቱ ውስጥ አስደናቂ ብቃት ያሳዩ አትሌቶችን ለይቶ በትራክ፣ በሜዳ እና ከስታዲየም ውጭ የሚደረጉ ዋና ዋና ውድድሮች በሶስቱ የሽልማት ምድቦች እጩዎችን አወዳድሮ ይሸልማል፡፡ ይህ ሽልማት ቀደም ሲል በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት አሸናፊ ይሰጥ የነበረ ሲሆን፣ ከ2023 ዓ.ም ጀምሮ በሦስት ምድቦች (የትራክ፣ የፊልድ እና ከስታዲየም ውጭ) ተከፋፍሎ ይሰጣል።

እጩዎችን ለመሸለም የዓለም አትሌቲክስ ምክር ቤት 50 በመቶ፣ የዓለም አትሌቲክስ ቤተሰብ 25 በመቶ ድምጽ እና በማህበራዊ ሚዲያ የሚሰጥ የህዝብ ድምጽ 25 በመቶ ድርሻ እንዳላቸው የፌዴሬሽኑ መረጃ ያሳያል፡፡

የዓመቱ የዓለም አትሌት (World Athlete of the Year) ሽልማት በዓለም አቀፉ የአትሌቲክስ ፌዴሬሽኖች ማኅበር (World Athletics) የሚዘጋጅ ዓመታዊ ሥነ-ስርዓት ሲሆን፣ ለሯጮች ትልቁን ዓመታዊ እውቅና ይሰጣል። በውስጡም የዓመቱ የጎዳና ላይ ምርጥ አትሌት (Out of Stadium Athlete of the Year) የሚባል የተለየ ምድብ ያካተተ ሲሆን፣ ይህ ሽልማት በተለይ በመንገድ ላይ ለሚደረጉ ውድድሮች (ማራቶን፣ ግማሽ ማራቶን፣ 10 ኪሎ ሜትር የመንገድ ሩጫ) እና የእግር ጉዞ ውድድር የላቀ ውጤት ላመጡ ሯጮች ይበረከታል። እንደ ኢትዮጵያ እና ኬንያ ያሉ የረጅም ርቀት ተወዳዳሪ አትሌቶች በዚህ ምድብ ተደጋጋሚ አሸናፊዎች ናቸው።

ዓለም አቀፉ የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን የ2025 የዓመቱ የጎዳና ላይ ምርጥ አትሌት ዕጩዎችን ይፋ አድርጓል። እነዚህ ዕጩዎች የተመረጡት በዓመቱ ውስጥ በጎዳና ላይ ሩጫዎች ማለትም በማራቶን፣ በግማሽ ማራቶን፣ በ5 ኪሎ ሜትር፣ 10 ኪሎ ሜትር እና የእርምጃ ውድድሮች ባስመዘገቡት ስኬት ነው፡፡

**የ2025 የዓመቱ የጎዳና ላይ ምርጥ አትሌት ዕጩዎች ውስጥ አትሌት ትዕግሥት አሰፋ እና አትሌት ዮሚፍ ቀጄልቻ በሁለቱም ፆታ ምርጥ ብቃት ካሳዩ አምስት አትሌቶች መካከል ሆነዋል**

የ2025 የዓመቱ የጎዳና ላይ ምርጥ አትሌት ዕጩዎች ውስጥ አትሌት ትዕግሥት አሰፋ እና አትሌት ዮሚፍ ቀጄልቻ በሁለቱም ፆታ ምርጥ ብቃት ካሳዩ አምስት አትሌቶች መካከል ሆነዋል። የሴቶች ዕጩዎች ዝርዝር አምስት ሲሆኑ፣ ከእነዚህም መካከል ሦስቱ አፍሪካውያን ናቸው። ከእጩዎቹ መካከል አንዷ የ2025 የለንደን ማራቶን አሸናፊዋ ትዕግስት አሰፋ ናት፡፡ አትሌቷ ከሁሉም ተወዳዳሪዎች የተለየች የሚያደርጋት በዚሁ ውድድር በሴቶች ብቻ በተደረገ ሩጫ የዓለም ክብረወሰን ማስመዝገቧ ነው።

ከዚህ ታሪካዊ ስኬት በተጨማሪም በቶኪዮ 2025 የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና የብር ሜዳሊያ አግኝታለች። በሜዳሊያ ብዛት ብታንስም፣ በለንደን ያስመዘገበችው ክብረወሰን ለሽልማቱ የላቀ ዕድል ሰጥቷል። አትሌት ትዕግሥት አሰፋ በውድድር ዓመቱ በተካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና 2ኛ ደረጃን ይዛ ያጠናቀቀች ሲሆን፤ የለንደን ማራቶን አሸናፊ መሆኗም ይታወሳል። በተጨማሪም በሴቶች ብቻ (በሴት አሯሯጮች ብቻ) በተደረገው ማራቶን የዓለም ክብረ ወሰንን በእጇ ያስገባችበት ዓመት ሆኖ አልፏል።

ከአትሌት ትዕግሥት አሰፋ በተጨማሪ ከኬንያውያኑ አትሌቶች ፔሬስ ጄፕቺርቺር እና አግኔስ ንጌቲች፣ ለኔዘርላንድስ ከምትሮጠው ትውልደ ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ሲፈን ሀሰን እና ስፔናዊቷ ማሪያ ፔሬዝ ምርጥ አምስት ውስጥ የተካተቱ አትሌቶች ናቸው።

ኬንያዊቷ አትሌት ፔሬስ ጄፕቸርቸር በቶኪዮ 2025 የዓለም ማራቶን ሻምፒዮን በመሆን የወርቅ ሜዳሊያ የወሰደች ሲሆን፣ ይህም ለአሸናፊነት ግምት እንድታገኝ አድርጓታል፡፡ ሌላኛዋ ኬንያዊት አግነስ ንጌቲች በ10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ሩጫ የዓለም ክብረወሰን አስመዝግባለች። እንደዚሁም ትውልደ ኢትዮጵያዊቷ ሲፈን ሀሰን በሲድኒ ማራቶን አሸናፊነት እና በለንደን ማራቶን ሦስተኛ በመሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላትን የብቃት ደረጃ አሳይታለች። በዘንድሮው የውድድር ዓመት ያልተሸነፈችው ስፔናዊቷ ማሪያ ፔሬዝ በ20 ኪሎ ሜትር እና በ35 ኪሎ ሜትር የእርምጃ ውድድር ድርብ የዓለም ሻምፒዮን ውድድሮች ውስጥ ትልቅ የበላይነት አሳይታለች።

በወንዶቹ ምድብ እንደዚሁ አፍሪካውያን አትሌቶች ቀዳሚ ሲሆኑ፣ ከ5ቱ እጩዎች ሦስቱ ምሥራቅ አፍሪካን የወከሉ አትሌቶች ናቸው። አትሌት ዮሚፍ ቀጄልቻ ከብራዚላዊው አትሌት ካይኦ ቦንፊን፣ ካናዳዊው አትሌት ኢቫን ዱንፊ፣ ኬንያዊው አትሌት ሳባስቲያን ሳዌ እና ከታንዛኒያዊው አልፎንስ ሲምቡ ጋር ምርጥ አምቱ ውስጥ ገብቷል። አትሌት ዮሚፍ ቀጄልቻ በዓመቱ በ5 ኪሎ ሜትር 6ኛውን የምንጊዜም ፈጣን ሰዓት ያስመዘገበ ሲሆን በ10 ኪሎ ሜትርም ምርጥ ሰዓት ማስመዝገብ ችሏል።

አትሌት ዮሚፍ በ2025 በጎዳና ላይ አጭር ርቀቶች (5 ኪሎ ሜትር እና 10 ኪሎ ሜትር) የዓመቱን ፈጣን ሰዓቶች ማስመዝገቡ በዓመቱ ውስጥ ባለው የፍጥነት ብቃት የበላይነቱን አሳይቷል። ሌላኛው እጩ ዝርዝር ውስጥ የገባው ኬንያዊ ሰባስቲያን ሳዌ ሁለቱንም የለንደንና የበርሊን ማራቶን በማሸነፍ በዓለም የጎዳና ላይ ውድድሮች ታላላቅ ማራቶኖችን የመቆጣጠር ብቃት አሳይቷል። በዓመቱ ውስጥ የተመዘገቡት ፈጣን የማራቶን ሰዓቶችም የእርሱ መሆናቸው የአሸናፊነት ክብደቱን ይጨምረዋል።

ታንዛኒያዊው አትሌት አልፎንስ ሲምቡ በበኩሉ በቶኪዮ 2025 የዓለም ማራቶን ሻምፒዮና የወርቅ ሜዳሊያ መውሰዱ ከፍተኛ ስኬት ሲሆን፣ በተጨማሪም የቦስተን ማራቶንን በሁለተኛነት ጨርሷል። እንደዚሁም ብራዚላዊው ካዮ ቦንፊም በ20 ኪሎ ሜትር የእርምጃ ውድድር የዓለም ሻምፒዮን መሆኑ በእርምጃ ውድድር ያለውን ብቃት በማሳየቱ በእጩነት ቀርቧል። ሌላኛው የእርምጃ ውድድር ባለድል ካናዳዊ አትሌት ኢቫን ደንፌ በ35 ኪሎ ሜትር የእርምጃ ውድድር የዓለም ክብረወሰንና የዓለም ሻምፒዮንነትን በማስመዝገብ በዘርፉ ታላቅ ስኬት አስመዝግቧል።

በወንዶች አትሌት ታምራት ቶላ በሴቶች አትሌት ሲፈን ሀሰን በ2024 ዓ.ም የዓለም አትሌቲክስ የዓመቱ ምርጥ ከስታዲየም ውጭ የሚደረጉ ውድድሮች አትሌት አሸናፊዎች መሆናቸው ይታወሳል፡፡

ከእጩዎች መካከል የዓመቱ ምርጥ አትሌትን ለመምረጥ በዓለም አትሌቲክስ ማኅበራዊ ትስስር ገጾች ማለትም (በፌስቡክ፣ ኢንስታግራም እና ኤክስ) ገጾች ድምፅ የመስጠት ሂደቱ ክፍት መሆኑ ተገልጿል። ድምፅ የመስጠት ሂደቱም የሚጠናቀቀው ጥቅምት 23 ቀን 2018 ዓ.ም መሆኑን እና አሸናፊዎች ይፋ የሚደረጉትም ህዳር 21 ቀን 2018 ዓ.ም ስለመሆኑ ተመላክቷል።

በዓለም አትሌቲክስ በየዓመቱ ከሚሰጠው “የዓመቱ ምርጥ አትሌት” ዋና ሽልማት እስካሁን ድረስ አምስት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ያሸነፉ ሲሆን፣ በወንዶች ኃይሌ ገብረሥላሴ እና ቀነኒሳ በቀለ ሲያሸንፉ በሴቶች መሰረት ደፋር፣ ገንዘቤ ዲባባ እና አልማዝ አያና የዓመቱ ምርጥ አትሌት ሽልማትን ያሸነፉ አትሌቶች ናቸው፡፡